## ምዕራፍ አሥራ ሦስት
## የሽማግሌው ታሪክ



ሉሲየን በዚያን ምሽት ከአጨዳው ስፍራ ወደ ቤቱ የተመለሰው ደስ እያለው ነበር።ብዙ ስለ ሠራ ደክሞታል። ቢሆንም ትንሹ ፈረሱ ይጠብቀዋል። ነገ ወደ ትምህርት ቤት ይዞት ስለሚሄድ ልጆች ሁሉ ያን አይተው ሉሲየን ቅርጻ ቅርጽ ሊሠራ የሚችል መሆኑን ይረዳሉ።

የቤቱን ፎቅ እንደ ወጣ በድንጋጤ እንደ በድን ፀጥ ብሎ ቀረ። ፈረሱ የለም! ጠረጴዛው ላይ የቀረው የቅርጻ ቅርጽ መሥሪያ ዕቃዎቹና የእንጨት ፍቅፋቂው ብቻ ነበር።

ምናልባት ቀድማ ከአጨዳው ስፍራ የመጡት እናቱ ወደ ቤት አግብተውት ይሆናል። በቤቱ ውስጥ ግራ ተጋብቶ እየተዋከበ፥

«እማዬ! እማዬ! ትንሹን ፈረሴን የት አደረግሽው?» አለ ድምጹን ከፍ አድርጎ።

እናቱ ምግብ እሚያዘጋጁበት ወጥ ቤት ውስጥ እንደ ሆኑ፥ «እኔ አላየሁትም። ምናልባት ሌላ ቦታ አስቀምጠኸው ይሆናል» አሉት።

ሉሲየን በጣም ደነገጠ።



«ጠረጴዛው ላይ ነበር ያስቀመጥኩት! እርግጠኛ ነኝ። ወይኔ እማዬ ወዴት ሄደብኝ? እባክሽ አፋልጊኝ!»

እናቱ ወዲያውኑ አብረው መፈለግ ጀመሩ። እንደ ሉሲየን እርሳቸውም ልጃቸው እንዲያሸንፍ ጓግተዋል። ሁለቱ እየተዘዋወሩ በበረንዳው ሥርቻና ከፍታ ውስጥ ሁሉ ፈለጉ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እናቱ አንድ አሳብ መጣላቸው፥ «ምናልባት ወደ መሬት ወድቆ ይሆናል፥ እስቲ ወደ ታች ውረድና ፈልገው» አሉት።

ሉሲየን ከፎቅ ወርዶ መሬት ላይ ይፈልግ ጀመር። ብዙም ሳይቆይ አገኘው። ያገኘው ግን በጭቃ የተለወሰና የተበታተነ የእንጨት ስብርባሪ ነበር። ያ ስብርባሪ ቀደም ሲል የእርሱ ፈረስ ነበር።

ስብርባሪውን ሰብስቦ ወደ እናቱ ወሰደው። የእናቱን የድንጋጤ ጩኸት የሰማችው የሉሲየን እኅት ሮጣ መጣች። ሁለቱ በድንጋጤ ተፋጠጡ።

እኅቱ የሆነውን ነገር ከተመለከተች በኋላ፥ «ድመቷ መሆን አለባት እንዲህ ያደረገችው። በጣም አዝናለሁ ሉሲየን። ለውድድሩ የምታቀርበው ሌላ ነገር የለህም?» አለች።

እናቱ «አይ ሉሲየን» ከማለት በቀር ሌላ ነገር አልተናገሩትም። የተናገሩበት ድምፅ ግን ብዙ ትርጉም ነበረው።

ሉሲየን ምንም አልተናገረም። ወደ ቤት ገባና ግድግዳ ላይ ያለውን ሰዓት ተመለከተ።

«ወደ ተራራው መውጣት አለብኝ። እስከ እራት ሰዓት ላልመጣ እችላለሁ።» አለ።

ይህን ተናግሮ በፎቁ ደረጃዎች ቁልቁል ተንደረደረ! የድርቆሽ ሣር ነዶዎች አረንጓዴ ባሕር ላይ ያሉ ሞገዶች የመሰሉበትን ሜዳ አቋርጦ ወደ ከፍታው ቦታ ገሠገሠ። ጫካው ውስጥ ገብቶ እስኪሰወር ድረስ እናቱ ቆመው ይመለከቱት ነበር። ከዚያ በኋላ መለስ ብለው በመቀመጥ ጥቂት አለቃቀሱ።

«ነገር ሁሉ የተሰነካከለበት ልጅ! የሚሳካለት ነገር ከቶ ይኖር ይሆን?» እያሉ በኀዘን አጉረመረሙ።

ሉሲየን ጫካው ውስጥ ያለውን እንቅስቃሴ ሁሉ ልብ አድርጎ ሳይመለከት በፀጥታ ተጓዘ። ከዛፍ ዛፍ የምትዘልለውን አረንጓዴ ሽኮኮ አላያትም። ስለ አጣው ሽልማትና በዚህ ሳቢያ ስለ ደረሰበት ከባድ

ብስጭት እንጂ ስለ ሌላ ነገር ለማሰብ አልቻለም። ለእርሱ የሚገባውን ክብር እንዴት ሌላ ሰው ይወስድበታል? እንደ ተጠላና እንደ ተናቀ ሊኖር ነው። የቅርጻ ቅርጽ ችሎታውን ለልጆች የሚያሳይበት ሌላ ዕድል አያገኝ ይሆናል። ያን ውድድር ካላሸነፈ ስለ እርሱ ማንም ግድ አይኖረውም።

«ማንም ወደማያውቀኝ ስፍራ፥ ወይም ምን ሠርቼ እንደ ነበር ወደ አልሰማ አካባቢ አሁኑኑ ሄጄ አዲስ ሕይወት ልጀምር በቻልኩ። እዚህ እንዳለኝ ሰውን ሁሉ የመፍራት ስሜት ወደሌለበት ሌላ አካባቢ ሄጄ በኖርኩ» እያለ አሰበ።

እንዲህ እያሰበ ሲጓዝ ዐይኖቹ በሁለት ተራራዎች መሀል በሚያልፈው መንገድ ላይ አረፉ። መንገዱ የሚወስደው ታላቅ እኀቱ ማሪዬ ወደምትሠራበትና ቀጥሎ ባለው ሸለቆ ውስጥ ወደሚገኘው ትልቅ ከተማ ነው። ያ መንገድ ሁልጊዜ ደስ ይለዋል። ሰላም ወደ ሰፈነበትና በቀላሉ ወደሚለመድ ሌላ ዓለም የሚወስድ ጎዳና ይመስለዋል። ፀሐይ ሙሉ ብርሃንዋን በምትሰጥበትና ምድር በአበቦች በምትሸፈንበት የበጋ ወቅት ሁለት ጊዜ ያን መተላለፊያ እያቋረጠ ተመልሷል። አሁን ትኩር ብሎ ሲመለከተው ከእሥር ቤት የማምለጫ በር መስሎ ታየው።

ጫካውን አቋርጦ እንዳለፈ ነው ሉሲየን የተራራው ላዩን ሽማግሌ ያያቸው። ሽማግሌው ሳያዩት ቀድሞ ተመለከታቸው። በራፋቸው ላይ ተቀምጠዋል። አገጫቸውን እጆቻቸው ላይ አስደግፈው ከሸለቆው ባሻገር ወደ አሉት ተራራዎች ይመለከታሉ። ሉሲየን በጣም እስኪጠጋቸው ድረስ ዘወር አላሉም።

«እ፥ እንደገና መጣህ?» አሉ ሽማግሌው በሚያጉተመትም ድምፅ። «የቅርጻ ቅርጽ ሥራህ የት ደርሷል? ውድድሩን አሸንፈህ ሽልማቱን የምታገኘውስ መቼ ነው?»

«ውድድሩን አላሸንፍም። ፈረሴ ተሰባብሯል። ድመቷ ሳትሆን አትቀርም ከፎቅ ላይ የጣለችው፤ ከዚያ በኋላ ሰው ረጋግጦታል» አለ ሉሲየን እያዘነ።

«አዝናለሁ፤ ቢሆንም ለውድድሩ ሌላ ነገር ልታቀርብ ትችላለህ። አንተ የሠራሃትን የድኩላ ቅርጽ ለምን አታቀርብም? በጣም ጥሩ ሥራ ነው» አሉ ሽማግሌው።



ሉሲየን የቆመበትን ድንጋይ በቁጭት አኳኋን ረገጠና፥ «በጥሩ የቅርጻ ቅርጽ መሥሪያ ዕቃ አልሠራሁትም። ከዚያ የበለጠ ልሠራ የምችል አይመስላቸውም። አይሆንም የፈረስ ቅርጼን ለውድድር ማቅረብ ካልቻልኩ፥ ሌላ ምንም አላቀርብም»

«ሌሎች ሰዎች ስለሚያስቡት ነገር ምን የሚያሳስብ ነገር አለ?» ሲሉ ጠየቁት ሽማግሌው።

«አዎ፥ አለ» ሉሲየን በቅሬታ አነጋገር።

«ለምን?»

ሉሲየን አቀርቅሮ መሬት መሬቱን ተመለከተ። ለሽማግሌው ጥያቄ የሚሰጠው መልስ አጣ። ሽማግሌው ከማንም ይልቅ የሚቀርቡት ጓደኛው ነበሩ። በመሆኑም እውነቱን ለመናገር ቢሞክር ይሻላል።

«አዎ፥ የሚያስኝ ነገር አለ። ምክንያቱም ሰዎቹ አይወዱኝም፤ የማልረባና መጥፎ ልጅ አድርገው ያስቡኛል። ውድድሩን አሸንፌ ብሸለምና በአካባቢው ካሉት ልጆች ሁሉ የተሻሉ ቅርጻ ቅርጾችን ልሠራ የምችል መሆኑን ሲያውቁ፥ ምናልባት ይወዱኝ ይሆናል»

«አይወዱህም። ችሎታህ ወይም ክህሎትህ ፍቅርን ሊገዛልህ አይችልም። ምናልባት አድናቆትና ምቀኝነትን ያስገኝልህ ይሆናል፤ ፍቅርን ግን በፍጹም አያመጣልህም። ጥረትህ ሁሉ ፍቅርን ለማግኛ ከሆነ፥ ጊዜህን በከንቱ ነው ያባከንከው።»

ሉሲየን መሬት መሬቱን ሲመለከት ቆይቶ ቀና በማለት እንባ ባቀረሩ ዐይኖቹ ሽማግሌውን እየተመለከተ፥

«ስለዚህ ምንም ዋጋ የለውማ። መልካም ነገር ለመሥራትና ሰዎች እንዲወዱኝ ለማድረግ አልችልም። ምንጊዜም የሚወዱኝ አይመስለኝም» አለ።

«እንዲወዱህ ከፈለግህ፥ ራስህን የሚወደድ ሰው አድርገህ ማቅረብ አለብህ። ቅርጻ ቅርጽ የመሥራት ችሎታህንም እነርሱን ለመውደጃና ለማገልገያ ልታውለው ይገባሃል። ይህ በአንድ ጊዜ የሚሆን ነገር አይደለም። ዓመታት የሚፈጅ ተግባር ይሆን ይሆናል። ሙከራህን ግን አታቋርጥ» አሉ ሽማግሌው ጠንከር ባለ አነጋገር።

ሉሲየን ሽማግሌውን ትኩር ብሎ ተመለከታቸው። ለምንድን ነው እኚህ ስለ ፍቅር ብዙ ነገር የሚያውቁ ሽማግሌ ከሰው ተለይተው እዚህ ተራራ ላይ የሚኖሩት? ሲልም አሰበ።

ሉሲየን የሚያስበውን ያወቁ ይመስል ፈገግ አሉና፥

«ስለ ፍቅርና ሰዎችን ስለማገልገል መናገሬ ይገርምሃል? እንዲህ ባለው ነገር መገረምህ ተገቢ ነው። እንዲህ የመሆኔ ምክንያትም ብዙ ታሪክ አለው» አሉ ሽማግሌው።

«ከሰው ርቀው እዚህ እየኖሩና ከእኔ ጋር ብቻ እየተነጋገሩ ሰውን ለማፍቀር፥ እንዲሁም ለማገልገል አይቻሉትም እያልኩ ነበር የማስበው» አለ ሉሲዬን ሽማግሌው ያሉትን በማመን።

ሽማግሌው በሩቁ የሚታዩትን ተራራዎች ጫፍ እየተመለከቱ ለጥቂት ጊዜ ዝም ካሉ በኋላ፥ «ታሪኬን እነግርሃለሁ፤ ምሥጢር መሆኑን ግን አትርሳ። ይህን ምሥጢር ለማንም አልነገርኩም። አንተ ስለ አመንከኝና እኔም ስለ አመንኩህ ነው የምነግርህ» አሉ።

ሉሲየን በሰማው ነገር ስሜቱ ስለ ተነካ ፊቱ ቀላ። የሽማግሌው ንግግር ደስ ይላል። ለሽልማት ባለመወዳደሩ የተሰማው ብስጭት እንኳን ቀለል አለለት። በውድድር ከማሸነፍ መታመን ይበልጣል።

«ከመነሻው ልጀምርልህ። አባቴ ከእኔ ሌላ ልጅ አልነበረውም። በመሆኑም እኔ ጠይቄው የማይሰጠኝ ነገር በዓለም ላይ አልነበረም። በጣም ሞልቃቃ ልጅ ነበርኩ።

በአንጻሩ ደግሞ ጎበዝ ስለነበርኩ ሳድግ አንድ ባንክ ውስጥ ጥሩ ሥራ ያዝኩ። ብርቱና ጥሩ ሠራተኛም ሆንኩ። ወዲያው አንዲት ልጅ ወደድኩና አገባኋት። እግዚአብሔር ባረከንና ሁለት ወንድ ልጆች ወለድን። በመጀመሪያዎቹ የጋብቻችን ዓመታት ጥሩ ባልና ጥሩ አባት እንደ ነበርኩ አምናለሁ።

በኋላ ግን መጥፎ ጓደኞች አፈራሁ። እነርሱም ቤታቸው እንድሄድ ይጋብዙኝ ጀመር። ቁማር መጫወትና ብዙ የአልኮል መጠጥ መጠጣት ይወዳሉ። አደነቅኋቸውና እነርሱ የሚያደርጉትን ማድረግ ጀመርኩ። ቀስ በቀስ በሚያሰክር መጠጥና በቁማር ገንዘቤን አባክን ጀመር።

ስለ እነዚያ ዓመታት ብዙ እንድነግርህ አያስፈልገኝም። ብዙ ጊዜ የማድረው ውጭ ሆነ። ብመጣም ሰክሬ ነው። በዚህ ምክንያት ልጆቼ ይጠሉኝና ይፈሩኝ ጀመር። ሚስቴ ጥሩ ሴት ስለሆነች ትጸልይልኝ ነበር። መጠጥ እንድተውም ጠየቀችኝ። እኔ ግን አልቻልኩም።

ያለን ገንዘብ ያልቅ ጀመር። ሰዎች ስለ እኔና ስለ መጥፎ ድርጊቶቼ አወሩ። የምሠራበት ባንክ ሥራ አስኪያጅ ሁለት ጊዜ አስጠነቀቀኝ።



ለሦስተኛ ጊዜ ሰክሬ መንገድ ላይ ስወላገድ አየኝና ከሥራ አሰናበተኝ። ያን ዕለት ማታ እንደ ሰከርኩ ወደ ቤቴ ሄድኩና ከሥራ መሰናበቴን ለሚስቴ ነገርኳት። «እንዲያ ከሆነ እኔ ሥራ ፈልጌ መሥራት አለብኝ። በዚህ ምክንያት ልጆቻችን መበተን የለባቸውም» አለች።

ሌላ ሥራ ፈለግሁ፤ ሰዎች ሁሉ ስለ እኔ መጥፎ ባህርይ ስለ አወቁ፥ ማንም ሊቀጥረኝ አልፈለገም። በቁማር ጨዋታ ገንዘብ ለማግኘት ሞከርኩ፥ ዕድለቢስ ስለሆንኩ አልተሳካልኝም። በመሆኑም ያለችኝን ጥቂት ገንዘብ አጠፋኋት።

ሚስቴ ከቤት ውስጥ ኃላፊነትና ሁለት ልጆቻችንን ከማሳደግ ጋር ሥራ ፈልጋ ሁልጊዜ ውጭ ስትሠራ የምትውል ሆነች። የምታገኘው ደመወዝ ግን ሁላችንን ለማስተዳደር የሚችል አልነበረም። አንድ ቀን ከሰው የተበደርነው ገንዘብ እንዳለብንና ልንከፍል እንደማንችል ነገረችኝ።

ለዕዳችን የምከፍለውና የምጠጣበት ገንዘብ በጣም አስፈለገኝ። ባንክ ቤት ውስጥ መሥራቴ በከንቱ አልነበረም። መግቢያና መውጫውን በደንብ አውቄዋለሁ፤ በመሆኑም የዝርፊያ ወንጀል ለመፈጸም ወሰንኩ።

በብልሃት የተወጠነው ዕቅዱ የተሳካልኝ መሰሎ ነበር፤ ነገር ግን ብልህነቴ ያን ያህል የዘለቀ ባለመሆኑ ተያዝኩ። ለባንኩ የምከፍለው ገንዘብ ስለአልነበረኝ ለረጅም ጊዜ ታሠርኩ።

ሚስቴ በጣም ታመመች። እጅግ አድካሚ ሥራ ትሠራ ነበር። ልጆቻችን በቂ ምግብ እንዲያገኙ ለማድረግ ስትል የሚያስፈልጋትን ያህል አትበላም። እኔን ለመጎብኘት በቀን ሦስት ጊዜ ወደ እሥር ቤት ትመጣለች። በርሃብና በችግር ምክንያት ከሣች፥ ገረጣች። አንድ ቀን ትልቁ ልጃችን በጻፈልኝ ደብዳቤ በጣም ስለ ታመመች ልትመጣ የማትችል መሆኗን ገለጠልኝ። ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ደግሞ በመሞቻዋ ሰዓት እንድሰናበታት በአንድ ፖሊስ ታጅቤ ሄድኩ። በማጣጣር ላይ ነበረች። የሞተችው በሳንባ ነቀርሳ በሽታ ምክንያት መሆኑን ነገሩኝ። እኔ ግን የሞቷ ምክንያት ኀዘን መሆኑንና የኀዘኗ ምክንያት ሆኜ የገደልኳትም እኔ መሆኔን ተረድቻለሁ።

ከዚያ ወዲህ ስለነበሩት ወራት ብዙም አላስታውስም። ደነዘዝኩ፥ እራሴን እረሳሁ። አንድ ተስፋ ብቻ ይዤ ቀረሁ። ከእንጨት ቅርጻ ቅርጽን መሥራት በሕይወቴ ሁሉ የምወደው ተግባር ነበር። እሥር

ቤት ውስጥ ሳለሁ በትርፍ ጊዜዬ የቅርጻ ቅርጽ መሥሪያው እንዲመጣልኝና የእንጨት ቁርጥራጮችን እየፋቅሁ እንድሠራ ፈቀዱልኝ። በሠራሁ መጠን ችሎታዬን አሻሻልኩ። አንድ ደግ የእሥር ቤቱ ዘበኛ የሠራሁትን ወደ ከተማ እየወሰደ ይሸጥልኝ ጀመር። በዚያ ሁኔታ ትንሽ ገንዘብ እያገኘሁ አጠራቀምኩ። እንዲህ በማድረግም አንድ ቀን ኑሮን እንደገና ለመጀመር የሚያስችለኝ በቂ ገንዘብ ሊኖረኝ ይገባል ብዬ አሰብኩ።

ያ ቀን እኔ ከጠበቅኩት ቀድሞ መጣ። ወደ አስተዳዳሪው ተጠራሁና እሥር ቤት ውስጥ በቆየሁባቸው ጊዜያት መልካም ጸባይ ስለአሳየሁ የመፈቻ ጊዜዬ ከመድረሱ በፊት እንደምለቀቅ ተነገረኝ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና ነፃ ሰው እሆናለሁ።

ወደ እሥር ክፍሌ የተመለስኩት በሰማሁት ነገር ደስተኛ ወይስ ኀዘንተኛ መሆኔን በትክክል ሳልረዳ ነበር። ከእሥር ቤት ስወጣ ደስተኛ መሆን እንደሚገባኝ አሰብኩ። ነገር ግን፥ ወዴት ነው የምሄደው? ኑሮንስ እንደገና የምጀምረው እንዴት ነው? እርግጠኛ የሆንኩበት አንድ ነገር ግን ነበር። ልጆቼ እንደገና ሊያዩኝ ወይም የት እንደነበርኩ ሊያውቁ አይገባም። አያቶቻቸው ዘንድ እንደሆኑና በጥሩ ሁኔታ በማደግ ላይ መሆናቸውን ተረድቻለሁ። በእውቀት እየተኮተኮቱ ለወደፊት መልካም ሕይወት በመዘጋጀት ላይ ናቸው። ከመጥፎ ስሜ ጋር እንዲቀራረቡ አልፈለግኩም። እንደሞትኩ ሊቆጥሩኝ ይገባል።

ከእሥር ቤት በተፈታሁ ዕለት ያጠራቀምኳትን ገንዘብ ኪሴ ከተትኩና ወደ ተራራማው አካባቢ በሚያመራው የመጀመሪያ ባቡር ተሳፈርኩ።

እዚህ አሁን አለሁበት መንደር ስደርስ፥ በፈረስ አጥር በኩል ለመሹለክ ከሚሞክሩ ላሞች ጋር የሚታገል አንድ ሰውዬ አየሁና ከነበርኩበት ባቡር ላይ ወረድኩ። ላሞቹ ወደ መንደር እንዲመለሱ በማድረግ ከረዳሁት በኋላ ሥራ እንዲሰጠኝ ጠየቅሁት።

እርሱ እንደማይፈልገኝ ነገረኝና ራቅ አለ ቦታ የነበረ ቤት እያሳየኝ፥ ልጁ የእጅ ሙያ ለመማር ሐይቁ ዳር ወደአሉት ከተሞች የሄደበት አንድ ገበሬ መኖሩን ገለጠልኝ። ሰውዬው ልጁን ተክቶ የሚያገለግለው ሰው እንደሚፈልግም አስረዳኝ።

ያን ዕለት ፍጹም አልረሳውም! ወደ ተጠቆምኩበት ቤት ሄድኩ። ሰውዬው በሩ ላይ እንጨት ሲፈልጥ አገኘሁት። ተጠጋሁትና ፊት



ለፊቱ ቆምኩ። ደከሞኛል፥ ርቦኛል፥ ልቤ አዝኗል። ጊዜ ሳላጠፋ ለእኔ የሚሆን ሥራ እንደአለው ጠየቅሁት።

ትኩር ብሎ ሽቅብ ቁልቁል ተመለከተኝ። ፊቱም ሆነ ዐይኖቹ ጥሩ ሰው መሆኑን ይገልጻሉ።

«አንተ የመንደራችን ነዋሪ አይደለህም። ማን ነህ? ከየት ነው የመጣኸው?» አለኝ ሰውዬው።

«ከጄኔቫ ነው የመጣሁት።»

«ሥራህ ምንድን ነው?»

«ሥራ የለኝም።»

«እስከ አሁን ምን ትሠራ ነበር?»

ስለ ጥሩ ውሸት ለማሰብ ሞከርኩ፥ ሰውዬው ግን ትኩር ብሎ ተመለከተኝ። አስተያየቱ ቅንነት ያለበት ስለሆነ እውነቱን ልነግረው የሚገባኝ መሆኑን ተረዳሁ። ስለ ማንነቴ በግልጽ ልነግረው ፈለግሁ፤ ካልሆነ ባያውቀኝ ይሻላል።

«ገና ከእሥር ቤት መፈታቴ ነው» አልኩ።

«ለምን ነበር የታሠርከው?»

«ገንዘብ በመስረቄ።»

«የእኔንስ ገንዘብ እንደማትሠርቅ በምን አውቃለሁ?»

«እንደገና በታማኝነት ለመኖር እፈልጋለሁ። ይመኑኝ፤ ካላመኑኝ እሄዳለሁ።»

እንደገና ከላይ እስከ ታች በደንብ ተመለከተኝ። ከዚያም ሊያምነኝና ሊቀጥረኝ መወሰኑን በሚገልጥ ሁኔታ እጁን ዘረጋና ጨበጠኝ። ጎኑ ቆሞ አልኩና አለቀስኩ።

ለዚያ ሰው አምስት ዓመት ሠራሁ። ኀደኛ ለማፍራት እንኳን ጊዜ በማይኖረኝ ሁኔታ ያለ እረፍት ነበር ያገለገልኩት። ደስታ የሚሰጠኝ ነገር የወደድኩትንና ማንም ባራቀኝ ጊዜ የተቀበለኝን ሰው ማገልገል ነበር። ለምንድን ነው ያመነኝና ያቀረበኝ እያልኩ እገረም ነበር። አንድ ቀን ምሽት ላይ ለእረፍት ከመጣ ልጁ ጋር ሲያወራ ነው ምሥጢሩ የገባኝ።

«ለምንድን ነው ስለ ማንነቱ የማታውቀውን እስረኛ ቤትህ ያኖርከው አባዬ? ብልህነት ያለበት ውሳኔ አይደለም ድርጊትህ» አለ ልጁ።

«ክርስቶስ ጥሩ ወይም መጥፎ ሳይል ሰውን ሁሉ ነው የተቀበለ። እኛም ተከታዮቹ እንደ መሆናችን እርሱ ያደረገውን ልናደርግ ይገባል።» አለ አባትየው።

በጋ ሲመጣ ከብቶችን ወደ ተራራማው አካባቢ እናመጣቸውና እዚህ አሁን አለሁበት ጎጆ ውስጥ እንኖር ነበር። ተራራው ላይ ያለው ሰላም ውስጤን ይፈውሰው ጀመር። ቀስ በቀስ እኔም በእግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት ማመን ጀመርኩ።

ከአራት ዓመት በኋላ የቀጠረኝ ሰውዬ ደካማና በሽተኛ ሆነ። ወደ ሐኪም ቤት ቢሄድም፥ ምንም ሊያደርጉለት አልቻሉም። ለአንድ ዓመት አስታመምኩት፥ ልጁም እየመጣ ይጎበኘው ነበር። በመጨረሻ ሞተ፥ እኔም እዚህ ብቻዬን ቀረሁ። በመሞቻው ዋዜማ፥ ልክ ሚስቱ እንዳደረገችው፥ ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት፥ እንዲሁም በደላችንን እንዴት ይቅር እንደሚለን ነገረኝ።

ምንም እንኳን ልጁ ለእኔ በጣም ደግ ሰው ቢሆንም፥ ብቸኛ ጓደኛዬ የሆነውን አባቱን አጣሁት። ልጁ የአባቱን ከብቶች ስለ ሸጠ ሀብታም ሆኗል። ይህን ጎጆ ለእኔ ሰጠኝ። እኔም አንድ ፍየል፥ እንዲሁም ጥቂት ዶሮዎች ገዛሁና ያለኝን ንብረት ጠቅልዬ እዚህ መጣሁ። ከዚያ ወዲህ እዚህ እኖራለሁ።

አንድ ጓደኛ ብቻ አለኝ፥ የምሠራቸውን ቅርጻ ቅርጾች የሚሸጥልኝና ከተማይቱ ውስጥ የሚኖረው ሰውዬ። አንዳንድ ጊዜ ስለ ልጆቹ ይነግረኛል። አድገው መልካም ሰዎች ሆነዋል። ጥሩ ኑሮ አላቸው። አንዱ ዶክተር፥ ሌላው ደግሞ ነጋዴ ሆነዋል። በሕይወት መኖሬን አያውቁም! አለማወቃቸው ጥሩ ነው። ምንም አላደርግላቸውም፥ ታሪኬ ያሳፍራቸዋል።

አሁን በእግዚአብሔር ስለማምን፥ ፍቅርና ምሕረትም ስላገኘሁ ስሕተቶቼን ለማረም እፈልጋለሁ። ከባንክ የሰረቅሁትን ገንዘብ ለመክፈል አልችልም። ነገር ግን ከሠረቅሁት ብዙም የማይተናነስ ገንዘብ አጠራቅሜአለሁ። እንዲሁ ቀጥዬ ገንዘቡ የሠረቅሁትን ሲያክልልኝ ያ ገንዘብ ለሚያስፈልገው ሰው ወይም መልካም ዓላማ እሰጠዋለሁ። በዚህ ሁኔታ ያለብኝን ዕዳ ሁሉ እከፍልና በደሌን እክሳለሁ።



ስሕተትን ለማረም አይቻልም ብለሃል፥ ትክክል አይደለህም። አንተ ካደረግከው እጅግ እጅግ የሚበልጥ በደል ፈጽሜአለሁ፤ በዚያ የተነሣም ተሠቃይቻለሁ። ነገር ግን እግዚአብሔር ለበደሌ ይቅርታ እንዳደረገልኝ አምናለሁ። ዕዳዬን ለመክፈልም በመሥራት ላይ ነኝ። እንዲህ በማድረግም እግዚአብሔር እንድሆንለት በፈለገኝ ዓይነት ለመኖር እሞክራለሁ። ይህን ነው ማድረግ የምችለው። ሌላውም ሰው የሚችለው ይህን ማድረግ ነው። ያለፈን ነገር ለእግዚአብሔር መተው ነው ያለብን።»

ይህን በመነጋገር ላይ እንዳሉ የሽማግሌው ሴት ፍየል መጣችና እራሷን ጉልበታቸው ላይ አንተርሣ ቆመች። የመታለቢያዋ ሰዓት መድረሱን ማስታወሷ ነበር። ይህን ሲመለከት ሉሲየን ወደ ቤቱ ለመመለስ ተነሣ።

ከሽማግሌው ተለይቶ በቀስታ እየተጓዘ፥ «ጊዜዬን የማሳልፈው ወደነበርኩበት መልካም ሁኔታ ለመመለስ በመጣር ነው... እግዚአብሔር እንድሆንለት በፈለገኝ ዓይነት ለመኖር በመሞከር» በማለት ሽማግሌው ስለተናገሩት ቃል በጣም አሰበ። ከዚህ አሳብ አንጻር ሲታይ የውድድሩና የሽልማቱ ጉዳይ ኢምንት ሆነበት፤ ስለ ጉዳዩ በጣም መጨነቅ እንዳልነበረበት ተገነዘበ። መቼም የዳኒን እግር እንደ ነበረ ለማድረግ አይችልም። ነገር ግን አንድ ቀን ከዚያ የሚበልጥ ነገር ሊያደርግለት የሚያስችለው ዕድል ያገኝ ይሆናል። እስከዚያው ድረስ ግን ከምን ጊዜም የተሻለ ጥሩ ልጅ ለመሆን ይሞክራል። ለውድድር ሊያቀርብ ያዘጋጀው ቅርጽ በመሰበሩ እናቱ በጣም አዝነዋል። በተፈጠረው ነገር አለማዘኑን በማሳየት ጠንካራ ልጅ መሆኑን መግለጥ አለበት። ይህን ሲያዩ እንደገና ደስ ይላቸዋል።

ጫካውን አቋርጦ እንዳለፈ የቤቱን ውስጥ ሙቀት የሚገልጥ ብርትኳንማ ብርሃን በመስኮት ይታየዋል። በፍጥነት እቤቱ በመድረስ ደስ እያለው ወደ ፎቅ ወጣና እናቱን ሳማቸው። ፎቁ በረንዳ ላይ ቆመው ይመለከቱት ነበር።

«እርቦኛል እማዬ፥ ምሳዬን አስቀምጠሽልኛል? አለ ሳቅ ብሎ የቀረበለትን ምግብ እየበላ እናቱን በፈገግታ ተመለከታቸው። ሁኔታውን ሲያዩ ኀዘናቸው ጠፋና እራሳቸውም ፈገግ አሉ።

## ምዕራፍ አሥራ አራት
## የእጅ ሥራው ውድድር



የፀሐይዋ ብርሃን ነው ዳኒን ከእንቅልፉ ያነቃው። ያን ዕለት የሚከናወነውን ጠቃሚ ነገር ለማስታወስ እየሞከረ ለጥቂት ደቂቃዎች መኝታው ውስጥ ቆየ። ጠቃሚው ነገር ትዝ እንዳለው ቀና ብሎ አልጋው ላይ ተቀመጠና፥ «አኔት ቶሎ ነይ! ሽልማትሽን ስትቀበዪ ለመመልከት እመጣለሁ። ጠቆር ያለውን ሙሉ ልብሴን አምጪልኝ፥ ቶሎ በይ!» አለ።

አራት ጊዜ ደጋግሞ እስኪናገር ድረስ አኔት ያልሰማች መስላ ዝም ብላ ከቆየች በኋላ ቀና ብላ መኝታዋ ላይ ተቀመጠችና፥ «ዝም በል ዳኒ። ሽልማቱን አገኛለሁ ብዬ በፍጹም አልገምትም። ያም ሆነ ይህ ገና ማለዳ ነው፥ ከመኝታ የመነሻ ሰዓት አይደለም። አባዬ ገና መነሣቱ ነው» አለች ቆጣ ብላ።

በረጅሙ ተንፍሶ እንደገና ጋደም አለ። ነገር ግን በጣም ደስ ስለአለው ዝም ማለቱ አልሆነለትም። ድመቱን ወደ አልጋው ሳብ አድርጎ ነጭ ሐር በመሰለው ጆሮዋ በሹክሹክታ ያወራላት ጀመር።

«በጋሪው እሄድና ተወዳዳሪዎቹ ልጆች የሠሯቸውን ቅርጻ ቅርጾች አያለሁ። አኔት የሠራችው ግን ከሁሉም ይበልጣል። በውድድሩ አሸንፋ የሚያምረውን ሽልማት ስትቀበል ለማየት እፈልጋለሁ። ያን ጊዜ በጣም አጨበጭብላታለሁ...»



ድመቲቱ አዛጋች፥ ዳኒም እንዲሁ። ገና ማለዳ እኮ ነው። በኋላ አኔት መጥታ ስትመለከታቸው ሁለቱም እንደ ኳስ ጥቅልል ብለው ተኝተዋል፥ እንቅልፍ ጭልጥ አድርጎ ወስዷቸዋል።

ከአንድ አዓት ተኩል በኋላ ጉዞ ጀመሩ። ዳኒ ከሁሉ የሚያምር ልብሱን ለብሷል። የአኔት አባት ዳኒ የተቀመጠበትን ጋሪ ይስባሉ። እርሷም በአባቷ ጎን ትራመዳለች። ነገር ግን ፈዝዛለች። ኀዘንና ብስጭት ይታይባታል።

ምን ይሆን አኔትን በዚያ ማለዳ ደስተኛ እንዳትሆን ያደረጋት? ፀሐይ ታበራለች፥ ወንዙ ያብረቀርቃል፥ አኔትም ውድድሩን ልታሸንፍ ነው። እነርሱን የሚያስደስት ብዙ ነገር አለ። ዳኒ ኀዘን ወይም ብስጭት አይታይበትም። የእግሩ ሕመም ሲሰማው ብቻ ነበር የደስታ ስሜቱ የሚለወጠው።

«ሆድሽን አመመሽ እንዴ፥ አኔት?» አለ ዳኒ በድንገት። «አላመመኝም ዳኒ፥ ለምንድን ነው ሆዴን የሚያመኝ» አለች አኔት ኮስተር ብላ።

«የአመመሽ ስለመሰለኝ ነው። ውይ አኔት፥ አየሽ ጫማዬ ላይ ሰማያዊ ቢራቢሮ ተቀምጣለች» አለ ዳኒ ቢራቢሮይቱን እያየ።

አኔት ዘወር ብላ እንኳን ሰማያዊዋን ቢራቢሮ አላየቻትም። መሬት መሬቱን እያየች መንገዱን ቀጠለች። ምን ሆና ይሆን?

እነ አኔት ትምህርት ቤት ሲደርሱ ክፍሉ በሰዎች በመሙላት ላይ ነበር። የተማሪዎቹ መቀመጫዎች ወደ አንድ ጥግ ተሰብስበው፥ ልጆቹ ለውድድር ያዘጋጇቸው ሥራዎች በአንድ ረጅም ጠረጴዛ ላይ ተደርድረዋል። የቀረቡትም ሹራቦች፥ ጥልፎች፥ ዳንቴሎችና ልዩ ልዩ የእጅ ሥራዎች ሲሆኑ፥ በጣም የሚያምር ትርዒት ሆኗል። ወላጆች እየተዘዋወሩ ትርዒቱን በአድናቆት ይመለከታሉ። ልጆቹ ደግሞ እየተጎነታተሉ፥ እየተንሾካሾኩና እርስ በርሳቸው እየተጠቋቆሙ ሰብሰብ እንዳሉ ወፎች ይንጫጫሉ።

የፖስታ አመላላሹ ልጅ ፔሬ ከእንጨት የተሠሩ ቅርጻ ቅርጾች አጠገብ እርሱ ለውድድር ወደ አቀረበው ቅርጽ ተጠግቶ ቆሟል። ያቀረበው፥ ከእንጨት የተሠራ የቀለም ብልቃጥና ማስቀመጫውን ሲሆን፥ ቀለም ብልቃጡ ላይ አንድ ድብ ቆሟል። ከዕድሜው ጋር ሲነጻጸር በጣም ጥሩ ሥራ ነው ያቀረበው። ልጆች መጥተው ትከሻውን

መታ እያደረጉ ስለ ሥራው የተሰማቸውን አድናቆት ሲገልጡለት ያፍርና ወደ ሌላ አቅጣጫ ይመለከታል። እርሱም ቢሆን በሥራው በተለይ በትንሹ የድብ ቅርጽ ተደስቷል። እናቱ ወደ እርሱ ስትመጣ አያትና በኩራት ፈገግ ብሎ ተመለከታት።

ሉሲየንም ትርዒቱ ስፍራ ነበር። እንደተለመደው ብቻውን እየተዘዋወረ የእናቱን ከቤት መምጣት ይጠባበቃል። ፊቱን ጭፍግግ እንዳደረገ ፔሬ ያቀረበውን የቀለም ማስቀመጫ ተመለከተና ኮስታራውን ድብ እርሱ ካቀረበው በደስታ የሚቧርቅ ፈረስ ጋር አነጻጸረ። ቀድሞ ያዘጋጀው ቅርጽ ባይሰባበርበት ኖሮ ልጆቹ የሚሰበሰቡት ፔሬ ባቀረበው ሳይሆን፥ እርሱ ባቀረበው ቅርጽ ዙሪያ ይሆን ነበር። በፔሬ ላይ በቁጣ የተሞላ ቅናት ቀናበት። ፔሬ ብልህና መልከ መልካም ሲሆን፥ በጫወታዎችም ጥሩ ተፎካካሪ ነው። አሁን ደግሞ ለሉሲየን የሚገባውን ሽልማት ሊያሸንፍ ነው። ወደ ክፍሉ ጥግ ሄዶ በመቆም ኀዘን በተሞላበት ሁኔታ ሕዝቡን ይመለከት ጀመር።

አኔት በሚንጫጩ ጓደኞቿ ብትከበብም፥ ባልተለመደ ሁኔታ ዝም ብላለች። አንዳንድ ሰዎች የውድድሩ አሸናፊ ትሆናለች ሲሉ፥ ሌሎች ደግሞ ጃኔ የተባለች ልጅ ናት የምታሸንፈው ይላሉ። ሰዎች ከስፍራ ስፍራ እየሮጡና ለውድድር የቀረቡ ሥራዎችን እየተመለከቱ አሸናፊ ስለሚሆነው ሥራ ግምታቸውን ይገልጣሉ። ሰብሰብ እያሉም ከፊሎቹ አንድ ነገር ሌሎቹ ሌላ ይላሉ። ለወትሮው ፈገግተኛና ለፍላፊ የነበረችው አኔት ብቻ ናት ምንም የማትናገር።

ዳኒ የአባቱን እጅ ጥብቅ አድርጎ በመያዝ እየተዟዟረ ለውድድር የቀረቡትን ሥራዎች ይመለከታል። የሚያዩት ሰዎች ገለል እያሉ መንገድ ይለቅቁለታል! የመልካም ምኞት መግለጫ ሰላምታም ያቀርቡለታል። ለመመልከት የፈለገውን ሁሉ ካየ በኋላ፥ ወደ ረጅሙ ጠረጴዛ ጫፍ በመሄድ አኔት ባቀረበችው የመወዳደሪያ ሥራ አጠገብ ቆመ። የውድድሩ አሸናፊ ስም በሚጠራበት ጊዜ ትክክለኛው ቦታ ላይ ለመገኘት ፈልጓል።

በሩ ተከፈተና የተሰበሰበው ሕዝብ በቅጽበት ፀጥ አለ። ከተማው ውስጥ ሐይቁ አጠገብ ያለው ሰውዬ ለውድድር የቀረቡትን ሥራዎች እየተመለከተ አሸናፊዎቹን ለመግለጽ መጣ። ረጅሙ ሰውዬ በቀስታ እየተራመደ ለውድድር የቀረቡትን ሥራዎች አንድ በአንድ እያነጣ በጥንቃቄ ሲመለከት፥ ልጆችና ወላጆቻቸው ጥጉን እየያዙ ቆሙ።



በመጨረሻም ለውድድሩ ብዙ ሥራዎች በመቅረባቸው አመስግኖ ንግግር አደረገ። ስለ ሁሉም ጥሩ አስተያየት ሰጠ። ጥሩ ትርዒት ለመመልከት እንደ መጣና በተመለከተው ደስ እንዳለው ተናገረ። ራቅ ብሎ ባለ ጠረጴዛ ላይ የተቆለሉ የተማሪዎች ደብተሮችን እያገላበጠ ተመለከተና ስለ እነርሱም አስተያየቱን ሰጠ። ደግና ትዕግሥተኛ ሰው ቢሆንም፥ በጣም ዝግተኛ ነበር። ልጆቹ የተሸላሚውን ማንነት ቶሎ ለማወቅ ጓግተዋል።

በመጀመሪያ ሴቶቹ ልጆች ያቀረቡትን ሥራ ተመልክቶ አሸናፊዋን ለመግለጽ ወሰነ። ቀስ እያለ ማርሴል የተባለች ልጅ ወደ ሠራችው ዳንቴል ሄዶ በጥንቃቄ መረመረው። ከዚያም አኔት ወደ ሠራችው ሹራብ ሄዶ ዘርግቶ ያዘውና ቆመ። መርፌ ቢወድቅ እንኳን በሚሰማበት ሁኔታ ክፍሉ ፀጥታ ሰፈነበት።

ወዲያው ፀጥታው ተጣሰና፥ «እኅቴ ናት እርሱን የሠራችው» የሚል የአንድ ልጅ ድምጽ በግልጽ ተሰማ።

ሰውዬው ዘወር ብሎ ወደ ጠረጴዛው ጫፍ አቅጣጫ ቢመለከት፥ ክብ ሰማያዊ ዐይኖች ያሉት አንድ ትንሽ ቀይ ፊት አየ። እነዚያ ዐይኖች በተስፋና በጉጉት ይመለከቱታል።

«እኅትህ ብልህ ልጅ መሆን አለባት» አለ ሰውዬው። በመናገር ላይ ሳለ ነው የዳኒን ክራንች የተመለከተው።

«ከሁሉ የሚበልጥ ሥራ ይመስለኛል፥ አይመስልህም?» አለ ዳኒ በጉጉት፥ በስፍራው የነበሩት ሰዎች ሁሉ የሚሰሙት መሆኑን ልብ አላለም። የፈለገው አኔት እንድታሸንፍለት ብቻ ነበር።

ዳኒ በተናገረ ጊዜ ሰውዬው ገና አሸናፊውን አልወሰነም ነበር።

አሁን ግን በጣም እርግጠኛ ሆነ።

«ይመስለኛል፥ ይህ ሥራ ከሁሉ ይበልጣል» አለ ሰውዬው። ዳኒ በፍጥነት ዘወር ብሎ እኅቱን አያት። በመጥፎ ባህርዩ በጣም አፍራለች። ዳኒ፥ «ሽልማቱ የአንቺ ሆነ እኮ አኔት!» እያለ ሲናገር ሰው ሁሉ ይስቅና ያጨበጭብ ጀመር። ባልተጠበቀና ባልተለመደ ሁኔታ የሴት ተወዳዳሪዎች አሸናፊ ተገለጠች።

ከወንድ ተወዳዳሪዎች አሸናፊ የሆነው ፔሬ ነበር። ልጆች ሁሉ ባይሰሙትም ተገቢው ንግግር ከተደረገ በኋላ ነበር አሸናፊነቱ

የተገለጠው። ከዚያም የሻይ ብስኩቶች ግብዣ ተደረገ። ፔሬም በአድናቂው ጓደኞቹ ታጅቦ ወደ ቤቱ ሄደ። ሁሉም በማሸነፉ የተሰማቸውን ደስታ ለመግለጽ ችኮላት ገዝተውለታል።

ሉሲየን ዳቦ ለመግዛት ወደ ከተማ የሄደው ብቻውን ነበር። በሚመለስበት ጊዜ ልጆች ሁሉ ወደየቤታቸው ስለሄዱ የትምህርት ቤቱ ሜዳ ባዶ ሆነ። ቀስ እያለ ዳገቱን ወጣ። ትከሻውን ያጎበጠውና መሬት መሬት እንዲያይ ያደረገው የዳቦው ቅርጫት ክብደት ሳይሆን፥ ኀዘን ነበር።

ለምንድን ነው አንድ ቀን ጠንካራና ደስተኛ ለመሆን ቀላል የሚሆነውና፥ በሚቀጥለው ዕለት ቁጡና ምቀኛ ከመሆን በቀር ሌላ ነገር ለመሆን የማይቻለው? ትላንት ከሽማግሌው ቤት ሲመለስ ፔሬ በውድድሩ ቢያሸንፍና ቢሸለም ግድ እንደማይኖረው አስቦ ነበር። ዛሬ ግን ፔሬን ጠላው። እግዚአብሔር እንደሚፈልገን ሆነን ለመገኘት ስለ መሞከር ሽማግሌው ተናግሯል። ነገር ግን የቱንም ያህል ቢሞከር ራስን ለረጅም ጊዜ ለመለወጥ የሚቻል አይመስልም።

ሽማግሌው ግን የተለየ ሰው ነው። እንዲያ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ የሉሲየንን አእምሮ ያዘው። ሽማግሌው ስለ እግዚአብሔር ተናግሯል። ምናልባት ከጠየቁት እግዚአብሔር መጥፎ ሰዎችን መልካም ያደርጋቸዋል። ሉሲየን ስለ እግዚአብሔር ብዙ የማያውቅ ሆኖ ተሰማው። ምናልባት በዳኒ ላይ በፈጸመው መጥፎ ነገር የተነሣ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ይሆናል።

ይሁንና እግዚአብሔር ሉሲየንን ሊወድደው ይችል ይሆን? በጣም አስከፊ የሆነን ኃጢአት እግዚአብሔር ቶሎ ይቅር አይልም? እርሱ ይቅር ቢል እንኳን ሰዎች ይቅርታ አያደርጉም። ሉሲየን ይህን ሲያሰላስል፥ እንደገና ኀዘን ተጫነው፥ በአጭሩ ተነፈሰና መንገዱ ላይ ያሉትን ድንጋዮች በንዴት እንደ ኳስ መታቸው።

በዚህ ጊዜ አኔት ቤት አቅራቢያ ካለው መንታ መንገድ ላይ ደርሷል። ወደ እርሱ ቤት የሚያመራውን መንገድ ተከትሎ ጥቂት እንደ ተጓዘ፥ የትንሽ ልጅ ዝማሬ ሰማና ዘወር ብሎ ተመለከተ።

ዳኒና ድመቱ አዲስ የሣር ክምር ላይ ተቀምጠዋል። ክምሩ ከላይ ጎድጎድ ያለ ስለሆነ እዚያ ውስጥ ተቀምጠው ሲታዩ ጎጆቸው ውስጥ



የተቀመጡ ሁለት ወፎች ይመስላሉ። ዳኒ አቀርቅሮ አንድ ነገር ይመለከታል። ክራንቹን አጠገቡ መሬት ላይ አጋድሞታል።

ሉሲየን ብቸኝነት በጣም ይሰማው ስለነበር፥ ወደ እነዳኒ ጠጋ ብሎ ይመለከታቸው ጀመር። ወዲያው ጉንጩ እስኪቀላ ድረስ ደስ ያሰኘውን ነገር ተመለከተና የአድናቆት ትንፋሹን በአጭሩ ወደ ውስጥ ሳበ። ዳኒ ሣሩ ክምር ውስጥ ዋሻ የመሰለ ጉድጓድ ስፍራ አዘጋጅቶ ሉሲየን ቀደም ሲል ያዘጋጀውንና አኔት የበተነቻቸውን ከእንጨት የተሠሩ ጥቃቅን እንስሳት አከማችቶበታል።

«ለእርሱ ሰጥታዋለች ማለት ነው። እርሱም ወዷቸዋል» አለ ሉሲየን በአሳቡ። የደስታ ሙቀት ተሰማው። ድምጹን ከፍ አደረገና «በምንድን ነው የምትጫወተው ዳኒ?» አለ።

ዳኒ ብድግ ብሎ ቢመለከት ድመቱን ሊገድልበት የሞከረውን ልጅ አየ። የመጀመሪያ አሳቡ ድመቱን እቅፍ አድርጎ፥ «አንተ መጥፎ ልጅ፥ ሂድ ከዚህ!» ሊለው ነበር።

ይህን ሲያስብ፥ ምንም እንኳን የአምስት ዓመት ልጅ ቢሆን፥ ሉሲየን ኀዘንተኛ መሆኑን ተረዳ። ኀዘን ደግሞ ትንሿ ልቡ ልትሸከመው የሚቻላት ነገር አልነበረም። ከእቅፉ ለመውጣት የምትታገል ድመቱን ጠበቅ አድርጎ እንደ ያዘ ሲያስብ ቆየና፥

«በኖኅ እንስሳዎች በመጫወት ላይ ነኝ። ግን አኔት አታናግረው ብላኛለች» አለ።

«አልጎዳህም፤ በእግርህ ላይ ስለደረሰው አደጋ አዝናለሁ። ለዚያ ነበር እንስሳቶቹን የሠራሁልህ» አለ ሉሲየን በትሕትና።

«አንተ አይደለህም የሠራሃቸው» አለ ዳኒ እየሳቀ፤ «ከእንጨቱ ክምር ኋላ ነው ያገኘኋቸው። በተረት ዓለም የሚኖሩት ትንንሽ ሰዎች ናቸው እዚያ ያስቀመጡልኝ።»

ሉሲየን ሊናገር ሲል ነበር ቀጭኑና ኩልል ያለው የአኔት ድምፅ ከቤት የተሰማው።

«ዳኒ፥ ቶሎ ና፤ እራት ደርሷል» ብላ ተጣራች።

ሉሲየን፥ «እውነተኛውን ነገር አልነገረችውም ማለት ነው» እያለ ለመሄድ መለስ አለ። ቢሆንም ቅርጾቹን ዳኒ እንደ ወደዳቸውና የሚጫወትባቸው መሆኑን ማወቅ መልካም ነው። አንድ ቀን ስለ

ቅርጾቹ ለዳኒ የሚገልጥበት ዕድል ይገጥመው ይሆናል። ከዚያም ሁለቱ ጓደኛሞች ይሆናሉ። ሜዳውን ያቋረጠው ትንሽ ደስ እያለው ነው። ዳኒም ወደ ቤቱ ተመልሶ ወጥ ቤት ውስጥ አለው ወንበሩ ላይ ተቀመጠ። ሴት አያቱ የሚሠሩት ምግብ ጥሩ መዓዛ የአፍንጫውን ጫፍ እንደ ጥንቸል አፍንጫ ሽቅብ ቁልቁል እንዲያነቃንቅ አደረገው።

«አኔት፥ ይሄ ሉሲየን ትንንሾቹን የኖኅ እንስሳዎቹን የሠራሁት እኔ ነኝ አለ። እርሱ አይደለም! ነው እንዴ? የተረት ዓለም ትንንሽ ሰዎች ናቸው ያስቀመጡልኝ! እነርሱ አይደሉም? ውሸታም ነው! አይደል?» አለ ዳኒ አኔትን እያየ።

«ሉሲየንን አታናግረው ብዬሃለሁ ዳኒ። እንደገና የሚጎዳ ነገር ያደርግብሃል። መጥፎ ልጅ ነው» አለች አኔት ቆጣ ብላ።

«በጣም ትንሽ ነው ያነጋገርኩት። ትንንሾቹን እንስሳት የሠራቸው ግን እርሱ አይደለም። ነው እንዴ? ንገሪኝ አኔት።» አለ ዳኒ።

አኔት አመነታች። እውነተኛ ልጅ ስለሆነች ለመዋሸት አልፈለገችም። ዳኒ እውነቱን ካወቀ ግን ወዲያውኑ ለሉሲየን ይቅርታ ያደርግለታል። ሄዶም ያመሰግነዋል። ከዚያም በኋላ ስለሚሆነው ነገር ለመናገር አይቻልም። በትንሽ ደቂቃዎች ውስጥ ነው ጓደኛሞች የሚሆኑት። ዳኒ ሰዎችን እንዳይወድ ማድረጉ ያስቸግራል። የእንስሳዎቹን እውነተኛ ታሪክ ካወቀማ፥ ሉሲየንን እንዳይወደው ለማድረግ በፍጹም አይቻልም።

«እንስሳዎቹን ያገኘሀቸው እንጨት ክምር ውስጥ መሆኑን ታውቃለህ፤ ታዲያ እንዴት እርሱ ሊሠራቸው ይችላል? ሞኝ አትሁን ዳኒ» አለች ፊቷን ወደ ሌላ አቅጣጫ መልሳ።

«እኔ ነኝ የሠራኋቸው አለ። እርሱ እንዳልሆነ ግን አውቄአለሁ። ያመጧቸው ግን ትንንሾቹ ሰዎች መሆን አለባቸው። አይመስልሽም አኔት?» ሲል ጠየቃት ዳኒ።

«እኔ እንጃ ዳኒ! እንዴት ነው ወሬኛ የሆንከው! ምግብህን ቶሎ ብላ! ቅዝቃዜው በመምጣት ላይ ነው።»

ዳኒ ለአኔት በመታዘዝ አቀርቅሮ ቶሎ ቶሎ ይመገብ ጀመር። የሴት አያታቸው ደካማ ዓይኖች ደግሞ ማንም ሊያየው በማይቻለው ሁኔታ አኔትን ትኩር ብለው ይመለከቱ ነበር። እንጨቱ ክምር ውስጥ ስለ ተገኙት የእንስሳት ቅርጾች ሰምተው እርሳቸውም ተደንቀዋል።



ሴት አያቷ ትኩር ብለው እንደሚመለከቷት የተረዳችው አኔት፥ ፊቷ ቀላ። ተጨማሪ ምግብ የፈለገች በማስመሰል ወደ ምድጃው አመራች። ስለአልራባት የወሰደችው ተጨማሪ ምግብ ትንሽ ነበር። መልካም ይሆናል ብላ ያሰበችው ዕለት እስከ አሁን እንደ ገመተችው አልሆነላትም። የጓጓችለትን ሽልማት ብታገኝም፥ ምንም የደስታ ስሜት አልፈጠረላትም። እንዲያውም ኀዘንተኛ ሆናለች።

የተመገቡባቸውን ዕቃዎች በፀጥታ ካጣጠበችና በማንቀላፋት ላይ የነበረውን ዳኒን ከሳመችው በኋላ ወደ ውጭ ወጣች። በበጋ ምሽት ብቻዋን፥ ፀጥ ካሉት ሰማያዊ ተራራዎች ጋር መሆንን ትወዳለች። እንዲያ ማድረጉ ያስደስታታል።

የዛሬው ሁኔታዋ ግን ከሁልጊዜውም ይለያል! የተደሰተችበት ነገር የለም። ተረጋግጦ መሬት ላይ ከወደቀው ትንሽ የፈረስ ቅርጽ ሌላ በአሳቧ የሚመጣ ነገር አልነበረም። በቁጣ በተናገረችው ጊዜ ፈገግታው የጠፋበት የዳኒ ፊትም ከአሳቧ አልጠፋም።

«ለብቻ መሆንን ሁለተኛ መውደድ አይኖርብኝም። ይህን ለአንድ ሰው ብነግር ደስ ይለኛል። ከዚያ በኋላ ነገሩ መልካም ይሆንልኛል። ምን ነው እናቴ በሕይወት በኖረችልኝ። ምን ነው ባላደረግኩት!» እያለች ወደ ቤት ተመለሰች።

# ምዕራፍ አሥራ አምስት
# ሌላ ገና እና ጣፋጭ ብስኩቶች



የመከር ወቅት ደረሰ፥ ከብቶችም ከተራራማው አካባቢ ተመለሱ፥ ዳኒም በየቀኑ እየረዘመ ይሄዳል። በመስከረም ወር የመንደሪቱ ጫማ ሠሪ ጫማ ሠራለት። ሕፃናት ትምህርት ቤት ገባና በየዕለቱ ወደዚያው ይመላለስ ጀመር። ገንዘብ እየተከፈላቸው ተራ በተራ በየሳምንቱ ከትምህርት ቤት ወደ ቤቱ በጋሪ የሚያመላልሱት ሁለት ትልልቅ ልጆችን አባቱ አዘጋጁለት።

እንደገና የገና ወቅት መጣ፤ በረዶውም በየሰው ቤት ጣራ ላይ ይከመር ጀመር። በመሆኑም የዳኒ አባት ከቤታቸው ዋና በር እስከ የበረዶው መንሸራተቻ ጋሪ መንደር ድረስ የሚወስደውን መተላለፊያ ቆፍረው አስተካከሉት። በአቅራቢያው ያለው ወንዝ በረዶ ስለ ረጋበት ጸጥ ብሏል። አኔትና ዳኒ በጣም በማለዳ እየተነሡ በበረዶው መንሸራተቻ ወደ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። ወደ ቤት የሚመለሱት ግን ሰማዩ እንደ ጠራ፥ ፀሐይዋ እያበራችና በረዶውም እንደ እንቁ እያብረቀረቀ ነው።

ታላላቅ ሁኔታዎች በሕይወቱ የተከናወኑት ያኔ ስለሆነ፥ ገና ለዳኒ ልዩ ወቅት ነው። እናቱ የሞተችው በገና ዕለት ዋዜማ ነበር። ምንም እንኳን ስለ እናቱ ሞት የሚያውቀው ነገር ባይኖርም፥ አባቱ ፊት ላይ የኀዘን ስሜት ስለሚመለከት እርሱንና አኔትን በጣም ነው የሚወዳቸው። ከእናት የሚፈልገውን የፍቅር እንክብካቤ ሁሉ ከሴት



አያቱና ከአኔት ያገኛል። ስለ ወላጅ እናቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሰበው፥ ሴት አያቱ ስለ መንግሥተ ሰማያት ከመጽሐፍ ቅዱስ ባነበቡለት ጊዜ ነበር። ያኔ መለስ ብሎ የእናቱን ፎቶ ግራፍ ግድግዳው ላይ ትኩር ብሎ እየተመለከተ ጊዜው ደርሶ ወደ መንግሥተ ሰማያት በሚሄድበት ወቅት እንደ አኔት ሁሉ ገርነት የተሞላበት ፊቷን በደስታ እንደሚመለከት፥ እርሷም፥ አኔትም ጭምር፥ በፈገግታ እንደሚቀበሉት አሰበ።

የገና ዕለት የልደት ቀኑም ነው፥ ዘንድሮ ስድስት ዓመት ይሞላዋል። ስለ ስድስተኛ ዓመቱ ለረጅም ጊዜ ሲያስብ ነበር የቆየው። በገና በዓል ዋዜማ ማለዳ በጣም አዲስ ልጅ ሆኖ ለመንቃት ወስኗል። ሌሊት በጭለማ ተኝቶ ባሰበው ቁጥር ትልቅ፥ ጠንካራ ወይም ከበፊቱ የሚሻልና ጠቃሚ ልጅ ያለመሆኑ ስሜት በጣም ያበሳጨው ነበር። ወዲያው አሳቡ ወደ ሌላ ሁኔታ ተመለሰ። በልዩ ልዩ ጌጣጌጥና መብራቶች ያሸበረቀውን የገና ዛፍ ለማየት ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል። ሴት አያቱም ለልደት በዓሉ በጣም ልዩ ኬክ ጋግረውለታል። ከዚያ በኋላ የሚያበሳጭ አሳብ በእርሱ ዘንድ ስፍራ አይኖረውም።

በዳኒ መረዳት፥ ገና የድመቱ፥ የከላውስ ልደት ዕለትም ነው። ድመቲቱ የተወለደችው ግን በገና ዕለት አልነበረም። ዳኒ ውጭ ባሳደረው ነጠላ ጫማ ላይ ስትቀመጥ ያኔ ቢያንስ የሁለት ሳምንት ዕድሜ ነበራት። ዳኒ ግን ስለዚያ አስቦ አያውቅም።

ከሁሉም ይልቅ፥ ገና ጌታ ኢየሱስ የተወለደበት ዕለት ነው። ምንም እንኳን ዳኒ ስለ ጌታ ልደት ብዙ ባይናገርም፥ ብዙ አስቦበታል። ፍጹም የሆነው ሕፃን በተወለደበት ዕለት መወለዱ በጣም አስደስቶታል።

«ለትንሹ ጌታ ኢየሱስ ለልደቱ ምን ልስጠው?» አለና ሴት አያቱን ጠየቃቸው፥ ክርኑን ጉልበታቸው ላይ በማስደገፍ ትኩር ብሎ እያያቸው። «ራስህን ልትሰጠው ትችላለህ» አሉ አያቱ የጥልፍ ሥራቸውን ቆም አድርገው ትንሽ ካሰቡ በኋላ። ቀጠል አደረጉና ደግሞ፥ «ሰው ወዳድና ታዛዥ እንዲያደርግህ ልትጠይቀውም ትችላለህ። ከምንም ይልቅ ያ ነው የሚያስደስተው» አሉ።

ስለዚህ ዳኒ እርሱ በተወለደበት ዕለት የተወለደውን ሕፃን ለማስደሰት ሲል ዓመቱን በሙሉ ሰው ወዳድ፥ ታዛዥና ሰውን ሁሉ አፍቃሪ ልጅ ሆነ። የሴት አያቱን የሥራ ሳጥን ያፀዳል፥ ሳህኖችን

በማጠብም እኔትን ይረዳታል። በገና ዕለት ከቀትር በኋላ ከብቶች ወዳሉበት በረት በመሄድ ተራ በተራ በጆሮአቸው እንኳን ለገና በዓል አደረሳችሁ አላቸው። በዕለቱ ማብቂያ በሚጸልይበት ጊዜ፥ «ትንሹ ጌታ ኢየሱስ ሆይ! አስደሳች የልደት በዓል እንዲሆንልህ ጥረት በማድረግ ላይ እንደሆንኩ ተስፋ አደርጋለሁ» አለ።

ዳኒ በዚህ ሁኔታ ጥሩ የልደት በዓል አሳለፈ። ደስታው ፍጹም ይሆን ዘንድም ሲመሽ ሞቃት ልብስ ደርቦ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደ።

በአባቱና በእኔት መሀል ተቀምጦ በበረዶ መንሸራተቻ ጋሪ ጉዞውን ጀመረ። ቀዝቃዛው አየር የዳኒን አፍንጫ በማደንዘዝ በስፍራው የሌለ እንዲመስለው አደረገው። ጨረቃይቱ ሙሉ ስለ ነበረች ነጫጮቹን ተራራዎች በብርሃንዋ ብርማ አስመስላዋለች። ዛፎች በረዶው እየከበዳቸው አጎንብሰዋል። እኔት እቅፍ ስለ አደረገችው ዳኒ ሙቀትና ምቾት ተሰምቶታል።

ጫካውን አቋርጠው ጎርበጥባጣውን ትንሽ ድልድይ በመሻገር ነፋሻው ሜዳ ላይ ሲደርሱ፥ ትንሹ ቤተ ክርስቲያን ታያቸው። በመቶ ከሚቆጠሩ ሻማዎች የሚወጣው ብርትኳንማ ብርሃን በበሩና በመስኮቶቹ እየዘለቀ ይታያል። ለበዓሉ የመጡት የመንደሪቱ ሰዎች ቤተ ክርስቲያኒቱ በረንዳ ላይ ሰላምታ ይለዋወጣሉ። እነእኔት ስፍራው እንደ ደረሱ፥ አባታቸው ዳኒን ተሸክመው ወደ መተላለፊያው ወሰዱትና ከሕፃናት ትምህርት ቤት ከመጡት ልጆች ጋር ፊት ለፊት አለው አግዳሚ ላይ አስቀመጡት። ሠላሳ የሚሆኑትና ከሱፍ የተሠራ ቆብ የደፉት ትንንሽ ልጆች የገና ዛፉን በመደነቅ ይመለከቱታል። ከምስት ቀን በፊት ነበር ዛፉ እነዳኒ ቤት አጠገብ እሚገኘው ቀዝቃዛ ጫካ ውስጥ በረዶ ከብዶት የወደቀው። ዛሬ ግን አጊጦ ያበራል። ብርትኳን፥ ቸኮሌት ከረሜላዎችና ከአንጸባራቂ ብስኩት የተሠሩ የአራዊት ቅርጻ ቅርጾች ተንጠልጥለውበታል።

ዳኒ ከፊት በመቀመጡ ደስ ብሎታል። የገና ዛፉን በደንብ ይመለከታል! በጣም የሚወደው ሥዕልም ይታየዋል። ሥዕሉ ከመድረኩ ጀርባ ባለው ግድግዳ ላይ ነው የተሰቀለው። መልካሙን ሳምራዊ የሚያሳይ ትልቅ ሥዕል ነው። በአንድ ታዋቂ ስዊዛዊ ሠዓሊ ተሠርቶ ከእንጨት በተዘጋጀ ክፍል ውስጥ በመደረግ ነበር የተሰቀለው። የመልካሙን ሳምራዊ ደግ ፊትና ትንሹን አህያ ዳኒ ይወዳቸዋል። ከሁሉም ይበልጥ የሚወደው፥ ሥዕሉ ላይ ሳምራዊውና አህያው



አጠገብ የሚታየውን ውሻ ነበር። ውሻው ሩዶልፍ በመባል የሚታወቀውንና የወተት መጫኛ ጋሪ እየሳበ መንደሩ ውስጥ የሚመላለሰውን ውሻ ይመስላል። ወተት ሻጩ ሰውዬ ነው የውሻው ባለቤት። የመንደሩ ትንንሽ ልጆች ግን የእኛ ነው ብለው ያስቡ ነበር። ላይ ላዩ እየተቀመጡ በትንንሽ እጆቻቸው የውሻውን ፀጉራም አንገት እቅፍ ያደርጉታል። ውሻው ደግሞ ይልሳቸዋል፥ ይተሻሻቸዋል! ምንም ቢያደርጉት ይታገሣቸዋል። እንዳልሠለጠኑ ቡችላዎች ነው የሚቆጥራቸው። ለዚህ ነበር ትንንሽ ልጆች አጠገቡ ውሻው ሮጥሮጥ የሚለውን መልካም ሳምራዊ ለመመልከት ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚመጡት።

ትልልቅ ልጆች በቅድሚያ የገና መዝሙር ዘመሩ። እኔት ከሌሎቹ ልጆች ጋር መዝሙሩን ስትዘምር መጀመሪያ ዳኒን ወደ አቀፈችበት የገና ምሽት በአሳብ ሄደች። የተቀበሉትም በደስታ እንደሆነ አስታወሰች። ሕፃኑ ኢየሱስ ሲወለድ ግን ከእናቱ በቀር ማንም አልተቀበለውም ነበር። «በእንግዶች ማደሪያ ስፍራ ስላልነበራቸው፥ በግርግም አስተኛችው።»

የገናው መዝሙር አበቃና ትልልቆቹ ልጆች ወደ ወንበራቸው ተመለሱ። የሕፃናት ትምህርት ቤት ልጆች ወደፊት ወጡ። ዳኒ ብቻ ነበር ክራንቹ እንደ እግር ስለማይፈጥንለት ወደ ኋላ የቀረው። ልጆቹ ግን ጠበቁት። በክራንቹ ዘለል ዘለል አለና መጥቶ ከልጆቹ በመቀላቀል ደስተኛ ፊቱን ወደ ሕዝቡ ሲያዞር ሰው ሁሉ ፈገግ አለ።

ዳኒ በገና ዛፉ አናት ላይ ያለውን ብሩህ ኮከብ ተመለከተ። ኮከቡ ከበታቹ ዛፉ ላይ ባሉትና ከብስኩት በተሠሩ ልዩ ልዩ እንስሳት ላይ ያንጸባርቃል። ያን እያየና የትኛው የእንስሳት ቅርጽ ያለው ብስኩት እንደሚሰጠው እያሰበ መዝሙሩን ረሳው። የሚስቅ የሚመስል እንስሳ አለ። ብስኩት ጋጋሪው ሳያስበው የእንስሳውን አፍንጫ ጠመም አድርጎታል። ዳኒ ያን እንስሳ ማግኘት ያለበት መሆኑን ወሰነ።

ሕፃናቱ ወደ መቀመጫቸው እንደ ተመለሱ፥ ሽማግሌው የቤተ ክርስቲያኒቷ መጋቢ ወደ መናገሪያው ስፍራ ወጡ። በመጋቢነት ለአርባ አምስት ዓመት ያገለገሉ ሲሆን፥ የመንደሪቱ ሰዎች ይወዷቸዋል። በዕድሜ ብዛት ትከሻቸው ጎብጧል፥ የፊታቸው ቆዳ ተሸብሽቧል። ያም ሆኖ የቤተ ክርስቲያኒቱን አባላት ለመጎብኘት ብዙ ጊዜ ወደ

ተራራማው አካባቢ ይመላለሳሉ። ጺማቸው ረጅምና ነጭ ስለሆነ አንዳንዴ ለዳኒ የገና አባትን ይመስሉታል።

መጋቢው መናገሪያው ስፍራ ላይ ከቆሙ በኋላ በስፍራው ያሉትን፥ ማለት የሚያውቋቸውንና የሚወዷቸውን ሁሉ ተመለከቷቸው። በጣም ስለ አረጁ፥ ምናልባት ይህ የመጨረሻው የገና ዕለት መልዕክታቸው ይሆን ይሆናል። ሲታሰብ የሚኖር ቃል ለመናገር እንዲችሉ እግዚአብሔር ይረዳቸው ዘንድ ጸለዩ።

አኔት ብዙ ጊዜ የሰማችውን ታሪክ ያደመጠችው የሚያልም ሰው እየመሰለችና ስለሌላ ነገር እያሰላሰለች ነው። የነቃችው ሽማግሌው፥ «ለእርሱ የሚሰጡት ማደሪያ ስፍራ አልነበራቸውም፥ ለእርሱ ስፍራ አልነበረም» የሚለውን ቃል በደገሙት ጊዜ ነበር።

ዝግ ባለ የሽማግሌ አነጋገር ይህንኑ ቃል ሦስት ጊዜ ደጋገሙት። አኔት በእያንዳንዱ ጊዜ ቃላቱ ይበልጥ በኀዘን የተሞሉ መሰላት። ምንኛ በፍጥነት በሯን ትከፍት ነበር!

«ይሁን እንጂ ሽማግሌው ንግግራቸውን ቀጠሉ፥ በዚህ ምሽት መድኃኒዓለም ከተዘጋ በር አጠገብ ቆሟል። ስፍራ ያልሰጡት ልቦች አሁንም አሉ። እንዲህ ይላል ጌታ፥ «እነሆ፥ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ። ማንም ድምፄን ሰምቶ ቢከፍትልኝ እገባለሁ. . .»

«በዚህ የገና በዓል ወቅት ስለ ክርስቶስ ምን ታደርጋላችሁ? የልባችሁን በር ትከፍታላችሁ፥ ወይስ ከውጭ እንደ ቆመ ትተዉታላችሁ? እነዚያ ‹ስፍራ አልነበራቸውም› የሚሉት አሳዛኝ ቃላት ስለ እናንተ የሚነገሩ ይሆኑ?

«እንዲገባ መጠየቅ አለብኝ። ምን ማለት እንደሆነ በግልጽ አልገባኝም። ሽማግሌው የነገሩን ወደ ልባችን ይገባ ዘንድ እንድንጠይቀው ነው። ወደ ልቤ እንዲገባ ልጠይቀው እችል ይሆን?» አለች አኔት።

አሳቡ ጥሩ መሆኑን ተገነዘበችና፥ እንደ እርሷ የተረዱ ሰዎች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ዘወር ብላ ተመለከተች። ያን ጊዜ ነው ሉሲየንን ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ በሌላ መደዳ ተቀምጦ ያየችው፤ እናቱና እኅቱም አብረውት አሉ።

አኔት ሉሲየንን እንዳየችው ያሰበችውን ለማድረግ እንደማትችል ተረዳች። ልቧ በሉሲየን ጥላቻ ስለ ተሞላ ኢየሱስ ወደ ልቧ እንዲገባ



ልትጠይቀው አትችልም። ኢየሱስም ቢሆን በቁጣ ወደ ተሞላና ይቅርታ ወደማያደርግ ልብ ሊገባ አይፈልግም። ወይ ይቅርታ ማድረግና ጥሩ ሰው መሆን አለባት፥ ያለዚያ ኢየሱስ ከውጭ መቆየት ይኖርበታል።

ይቅርታ ለማድረግና ደግ ልጅ ለመሆን አትፈልግም። ገና ነው።

ሌላም ነገር አለ። የሉሲየንን የቅርጽ ሥራ ሰብራበት ድመት የሰበረችበት እንዲመስለው ከማድረጓም በላይ፥ ሽልማት እንዲያጣም አድርጋለች። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልቧ ቢገባ ስለዚህ ድርጊቷ የሚላት ነገር አለ፤ ያን ለመስማት አልፈለገችም።

ስብከቱ አበቃ። እርሷ ግን በአሳብ ተጠምዳ ስለነበር ብዙም አላዳመጠችም። ዳኒ አኔትን ጎሸም አደረጋትና ወደ ገና ዛፉ ሄዶ በብስኩት ከተሠሩት እንስሳዎች አንዱን የመውሰጃው ጊዜ መድረሱን አስገነዘባት።


ቤተ ክርስቲያኑ በዝግታ በሚወያዩ ሰዎች ድምጽ ተሞልቷል። ትንንሽ ልጆች ደግሞ ወደ ገና ዛፉ ለመሄድ ይጋፋሉ። ዛፍ ቆራጩ አቶ ፒሌት ከብስኩት የተሠሩ እንስሳትን ለልጆቹ ያድላሉ። ዳኒ እጅጌውን ሰብሰብ አድርጎ ቀደም ሲል ወደ ተመኘው እንስሳ እየተመለከተ፥

«እባክዎን፥ ያን ይስጡኝ፤ እርሱን ነው የምፈልገው። ያን ከላይ ያለውን። እባክዎ፥ በጣም እፈልገዋለሁ!»። አለ።

አቶ ፒሌት ክራንቼን በመመልከታቸውና የገና በዓልም በመሆኑ ዳኒ የጠየቀውን ለማድረግ ፈቀዱ። በዚሁ መሠረት መሰላሉን ይዘው ሕፃናቱን ገለል ካደረጉና ከታች ያሉትን መብራቶች ገፋ ካደረጉ በኋላ በብዙ ችግር በመሰላሉ ላይ ወጥተው ዳኒ የፈለገውን ከብስኩት የተሠራ እንስሳ ከገናው ዛፍ ላይ አወረዱት። ዳኒ የተመኘውን የእንስሳት ቅርጽ ካገኘና እቅፍ ካደረገው በኋላ በበረዶ ጋሪው ተሣፍሮ በከዋክብቱ ብርሃን እየተደሰተ ወደ ቤቱ ተጓዘ። የእንስሳውን ደስ የሚል ጠማማ አፍንጫ በተመለከተ ቁጥር ሳቅ ይላል። ያን ሲያደርግ ከእንስሳው ጋር ማንም የማያውቀው የገና ቀልድ የሚቀልድ ይመስላል።

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

## ድመቲቱ ከላውስ ጠፋች



የገና በዓል አልፎአል። ዳኒ ቀይ ፊቱን ከንዱ ላይ አንተርሶ ተኝቷል። የዳኒ አባት ጠረጴዛው አጠገብ ተቀምጠዋል። አኔትና ሴት አያቷ ደግሞ ከምድጃው ግራና ቀኝ ቁጭ ብለዋል። ሴት አያታቸው ለልጅ ልጆቻቸው ከነጭ ሱፍ የእግር ሹራብ በመሥራት ላይ ናቸው። አኔት የተቀደደ ሸርጧን ለመስፋት ስትዘጋጅ መሬት ላይ ስለ ወደቀባት ራሷን እጆቿ ላይ በማስደገፍ በመገረም አኳኋን ዝም ብላ ትመለከተዋለች።

«አኔት» አሉ ሴት አያታቸው፥ ሥራቸው ላይ እንዳቀረቀሩ፥ «ጥሩ የገና በዓል አሳለፍሽ?»

«አዎ፥ አያቴ፥ አመሰግንሻለሁ፥» አለች አኔት ቅዝቅዝ ባለ አነጋገር። ማለት ያለባት ይህን ብቻ መሆኑን ነው ያሰበችው። ወዲያው ቀጠል አደረገችና፥ «አያቴ፥ ኢየሱስ የልባችንን በር ያንኳኳል ማለት ምን ማለት ነው?» አለች።

ሴት አያቷ በእጃቸው የያዙትን ሥራ ቁጭ አድርገው አኔትን እየተመለከቱ፥ «ሕይወትሽ በተሳሳተና በመጥፎ አሳብ የተሞላ መሆኑን ኢየሱስ ይመለከታል ማለት ነው። በመሆኑም ኢየሱስ ከሰማይ በመውረድ አንቺን ተክቶ በመጥፎ ድርጊትሽ ለመቀጣት በመስቀል ላይ ሞተ። ከዚያም ወደ ሕይወትሽ ለመግባትና ውስጥሽ ለመኖር



ከሞት ተነሣ። ይህን በማድረግም እነዚያን ክፉ አሳቦች ከውስጥሽ ያወጣና በዚያ ፈንታ የራሱን መልካምና በፍቅር የተሞሉ አሳቦች በውስጥሽ ያኖራል። የማንኳኳቱ ትርጉም ልክ አንድ ሰው ቆሻሻ፥ ጨለማና አቧራ የሞላበትን ቤት በር በማንኳኳት ‹ብትከፍትልኝ ቆሻሻውንና ጨለማውን አውጥቼ ውብና ብሩህ አደርገዋለሁ› እንደሚለው ዓይነት ነው። ኢየሱስ እንዲፈቀድለት ይጠይቃል እንጂ በግድ ገፍቶ አይገባም። ይህን መዘንጋት የለብሽም። ይህ ነው የማንኳኳት ትርጉሙ። «አዎ፥ ጌታ ሆይ፥ ታስፈልገኛለህ። እውስጤ እንድትገባና እንድትኖር እፈልጋለሁ› ማለት አለብሽ። ያ ነው በርን የመክፈት ትርጉሙ» አሉ።

አኔት ሴት አያቷን ትኩር ብላ ትመለከታቸው ነበር። ለረጅም ጊዜ ዝም ብላ ቆየችና፥

«ግን አያቴ» አለች ወንበሯን አስጠግታና አያቷ ጉልበት ላይ ደገፍ ብላ፤ «አንድ ሰው ከጠላሽ ኢየሱስ እንዲገባ ለመፍቀድ አትችይም፤ ትችያለሽ?»

«አንድ ሰው የምትጠዪ መሆንሽ የሚያመለክተው፥ ኢየሱስ እንዲገባ መፍቀድሽ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ነው። ክፍሉ በጣም ጨለማ በሆነ መጠን የላቀ ብርሃን ይፈልጋል።»

«እኔ ግን ሉሲየንን መጥላቴን ልተው አልችልም፥» አለች አኔት ረጅም ጉንጉኗን በጣቶቿ እያፍተለተለች።

«እውነትሽን ነው፥ አትችዪም። ማንኛችንም ብንሆን መጥፎ አሳብ ወደ እኛ እንዳይመጣ ልናግድ አንችልም። ያን ለማድረግ መሞከሩም እምብዛም ውጤት የለውም። እስቲ ልጠይቅሽ አኔት፤ ጠዋት ወደዚህ ክፍል ስትገቢ መስኮቶቹ ተዘግተው ክፍሉ ጨለማ ቢሆን፥ ‹መጀመሪያ ጨለማውን ማስወጣት አለብኝ፤ ከዚያ መስኮቶቹን ከፍቼ የፀሐይ ብርሃን አስገባለሁ› ትያለሽ? ጨለማውን ለማስወጣት በመሞከር ብቻ ጊዜ ታጠፊያለሽ?»

«እንደዚያማ አላደርግም» አለች አኔት።

«ታዲያ እንዴት ነው ጨለማውን የምታስወግጂው?»

«መስኮቶቹን ስከፍታቸው ብርሃን ወደ ቤቱ ይገባል።»

«ጨለማው ምን ይሆናል ታዲያ?»

«እኔ እንጃ፥ ብርሃን ሲገባ እርሱ ይወጣል።»

«ኢየሱስ እንዲገባ ስትጠይቂው የሚሆነው ነገር ልክ እንዲሁ ነው። እርሱ ፍቅር ነው። ፍቅር ሲገባ፥ ጥላቻ፥ ራስ ወዳድነት እና ክፋት ይወጣሉ። ልክ መስኮቶቹን ከፍተሽ የፀሐይ ብርሃን ስታስገቢ፥ ጨለማው እንደሚወጣ ማለት ነው። ጨለማውን ለማውጣት ብቻ የሚደረገው ሙከራ ጊዜ ማባከን ይሆናል።»

አኔት ፊት ለፊቷ አለው ግድግዳ ላይ አፍጥጣ ጥቂት ከቆየች በኋላ፥ በረጅሙ ተንፍሳ ሽርጧን አነሣችና በዝምታ ትሰፋ ጀመር። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ብድግ ብላ ሴት አያቷን ደህና እደሪ በማለት ሳም አደረገቻቸውና ወደ መኝታ ክፍሏ ሄደች።

ይሁን እንጂ ለረጅም ሰዓት እንቅልፍ አልወሰዳትም። በጨለማ ውስጥ አልጋዋ ላይ ተጋድማ ስታስብና ስትገላበጥ ቆየች።

«እውነት ነው፤ እንዲገባ ከፈቀድኩለት ከሉሲየን ጋር መታረቅና ጓደኛው መሆን አለብኝ። እንደዚያ ለማድረግ ደግሞ አልፈልግም። ለውድድር ያዘጋጀውን የቅርጽ ሥራ እንዴት እንደ ሰበርኩበት ልነግረው የሚገባኝ ይመስለኛል። ነገር ግን በፍጹም አላደርገውም። ስለ ደጁ መንኳኳት ማሰቤን መተውና መርሳት አለብኝ። ግን ደግሞ በጣም ኀዘን ይሰማኛል» አለች በአሳቧ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ከውጭ ሆኖ ሲያንኳኳ ሰምቶ የማይከፍትለት ልጅ በራሱ ደስታ ላይ በሩን እንደሚዘጋ አልገባትም። ሁሉንም ነገር በመርሳት በሌላ መንገድ ደስተኛ ለመሆን የምትችል መስሏት ነበር። እንዲህ እያሰበች ትራሷን ገልብጣ በመንተራስ እንቅልፍ እስኪወስዳት ድረስ ከመቶ ጀምራ ወደ ኋላ ትቆጥር ጀመር።

እንቅልፍ ከወሰዳት በኋላ፥ ስለ አንድ መስኮቶቹ ስለ ተዘጉ፥ በሩም ስለ ተቆለፈ ጨለማ ቤት አለመች። አንድ ሰው ሌሊት በረጋ በረዶ ላይ ወደዚያ ቤት ይመጣል። የሚታየት ሰውዬው የረገጠው የጫማ ምልክት ብቻ ነው። ሰውዬው የተዘጋውን ቤት በር በቀስታና በትዕግሥት አንኳኳ። ማንም አልከፈተለትም። የበሩን እጀታ ፈለገ፥ አልነበረውም። እየደጋገመ ማንኳኳቱን ቀጠለ። አኔት እስክትነቃ ድረስ ያንኳኳ ነበር። አሁንም ማንም አልከፈተለትም፤ በመስኮቱም ብርሃን አይገባም።

«ቤቱ ውስጥ ሰው የለ ይሆናል» አለች አኔት ግማሽ እንቅልፍ ውስጥ እያለች። ነገር ግን በሩን ለመክፈት አልፈለገም እንጂ ቤቱ ውስጥ ሰው መኖሩን በአንዳች ሁኔታ አውቃለች።

ሲነጋ ለባበሰችና ቁርሷን ለመብላት ሄደች። በህልሟ የተሰማት ኀዘን ገና አልተለያትም፥ ተበሳጭታለች። ቁርስ መመገቢያው ክፍልም ግርግር



ነበር የጠበቃት። ዳኒ ድመቱ ክላውስ ስለ ጠፋች፥ እርሷ እስክትገኝ ድረስ ቁርስ አልበላም ብሏል።

«ሁልጊዜ ጠዋት ጠዋት ከእንቅልፌ ትቀሰቅሰኝ፥ ኩርር የሚለውን ድምጽዋን ታሰማኝ ነበር። ዛሬ ጠዋት ግን አልመጣችም። ትናንት ማታ ከመተኛቴ በፊት ነበር ከቤት የወጣችው፤ ከዚያ ወዲህ አልተመለሰችም» ይላል በተደናገጠ አነጋገር።

ዳኒ በጣም ስለ ተበሳጨ፥ ሰዎች ድመቱን በመፈለግ ሊረዱት በመሞከር ላይ ናቸው። አባቱ ከብቶች በረት ውስጥ፥ ሴት አያቱ ደግሞ ወጥ ቤት ውስጥ ፈለጓት። ዳኒም አስቸጋሪ በሆነ ስፍራ ሁሉ እየገባ ፈለጋት። አኔት ወደ ፎቅ ወጥታ መኝታ ቤቶቹ ሁሉ ውስጥ ፈለገቻት። ትርፉ ልፋት ብቻ ነበር። ክላውስ የትም የለችም። የዳኒ አባት ለመጨረሻ ጊዜ ያዩዋት ጅራቷን ወደ ላይ አቁማ በቁጣ ወደ በረቱ አቅጣጫ ስትራመድ ነበር። ከዚያ ወዲህ ማንም አላያት።

ደስ የሚል ቀን አልነበረም። ዳኒ ምግብ በቀረበለት ጊዜም እንደ ተናደደ ነበር። እያለቀሰ ክላውስ እየራባት እርሱ እንደማይበላ ይገልጣል። እንባው ምግቡ ላይ ይንጠባጠባል። ምንም እንኳን አባቱና ሴት አያቱ በጣም ባይጨነቁም፥ ሊያጽናኑት ሞክረዋል፤ አልቻሉም። «ትመጣለች ዳኒ! ለዛሬ ብቻ ተደብቃ ነው» አሉ አባቱ በቀስታ።

ዕለቱ ደመናማ ነው፤ ፀሐይ አትታይም። ደመናው ተራራዎችን እስኪሸፍን ድረስ ዝቅ ብሏል። የአውሮፓው በረዶ መዝነብ መጀመሩ ነው። በሚቀጥለው ዕለት በረዶው መሬት ላይ ስለሚረጋ በዚያ ላይ መራመዱ አደገኛ ይሆናል። የዳኒ አባት ባርኔጣቸውን አድርገው ከበረዶ መንሸራተቻቸው በመውረድ ጫካው ውስጥ ይጓዙ ጀመር። ሴት አያታቸው ምድጃው ዳር ባለው ባለመደገፊያ ወንበር ላይ እንደ ተቀመጡ አንቀላፉ። ዳኒ ደግሞ አኔት ላይ ደገፍ በማለት ሽቅብ ዐይን ዐይንዋን እያየ፥

«አኔት፥ ለመተኛት እፈልጋለሁ» አላት በሚያሳዝን አነጋገር።

«ለምን ዳኒ? ገና እኮ ነው፥ አልመሸም፥ ደግሞ እራትህን አልበላህም» አለች አኔት በመገረም።

«ለመተኛት፥ ደግሞም የምጸልይበት ጊዜ እንዲሆንልኝ እፈልጋለሁ።»

«ለመጸለይ መተኛት አያስፈልግህም እኮ ዳኒ፥ አሁኑኑ እዚህ ሆነህ ልትጸልይ ትችላለህ። ከዚያ እራትህን ትበላና በትክክለኛው ሰዓት ትተኛለህ» አለች ሳቅ እያለች።

«የለም፥ በዚህ ጊዜ የምጸልየው ጸሎት የሌሊት ልብሴን ለብሼ የምጸልየው ትክክለኛ ጸሎቴ እንዲሆንልኝ እፈልጋለሁ። እባክሽ አኔት፥ ወደ አልጋዬ ውሰጂኝ።»

«እሺ! የሌሊት ልብስ መልበስህ ግን ምንም ለውጥ አያመጣም» አለች የሹራቡን ቁልፎች እየፈታታችለትና እየሳመችው። ፊቱ ኀዘን አጥልቶበታል፥ የታች ከንፈሩ ተንጠልጥሏል።

ነጭ የሌሊት ልብሱን እንደ ለበሰ ተንበርክኮ እጆቹን አጠፈና እንዲህ እያለ ለድመቱ ጸለየ።

«ውድ እግዚአብሔር ሆይ! እባክህ ክላውስን ባርካት። እባክህ ፈልግና ቶሎ ወደ እኔ አምጣት። ከብርድ፥ ከርሃብና ከፍርሃት ጠብቃት። ዛሬ ወደ ቤቷ እንድትመጣ መንገዱን አሳያት። ውድ እግዚአብሔር፥ እባክህ፥ እባክህ፥ አሜን።»

«ከክላውስ ውጭ ለሌላ ሰው አትጸልይም ማለት ነው?» አለች አኔት ትንሽ ደንገጥ ብላ።

«አልጸልይም» አለ ዳኒ ከተንበረከከበት በፍጥነት እየተነሣ፥

«ዛሬ ለማንም አልጸልይም። እግዚአብሔር ለክላውስ እንጂ ስለሌላ ሰው እንዲያስብ አልፈልግም» ካለ በኋላ ትንሽ አሰብ አደረገና፥ «ለሌሎቹ ሰዎች በኋላ ልትጸልዩላቸው ትችያለሽ» አለ።

ዳኒ ክላውስን እንዲጠብቅለት እግዚአብሔርን ከጠየቀ በኋላ፥ ሰላም በተሞላ ልብ አልጋው ላይ ወጣና ፊቱን እጁ ላይ አንተርሶ ተኛ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ዐይኖቹን ገለጠና፥ «አኔት?» አለ። «ወይ፥» አለች አኔት።

«ስትመጣ ትቀሰቅሺኝ የለ?»

«ማን ስትመጣ?»

«ክላውስ ናታ» አለ። ብዙም ሳይቆይ እንቅልፍ ወሰደው።

አኔት በመጨነቅ አኳኋን ክፍሉ ውስጥ ስትንቆራጠጥ ቆየችና ጉንጭዋ ላይ ሙቀት ስለ ተሰማትና ቀኑን ሙሉ ቤት ውስጥ ስለ ዋለች በሩን ከፍታ ወደ ፎቁ ሰገነት ወጣች።

በረዶው መዝነቡን አቁሟል! ከምዕራብ አቅጣጫ የሚመጣው ንፋስ ስሱን በረዶ በቤቱ ግድግዳ ዙሪያ እየከመረ፥ ሽቅብ ወደ ሸለቆው በመንፈስ ላይ ነው። በጣም የሚቀዘቅዝ ንፋስ አይደለም። ለጋለው ጉንጭዋ ተስማምቶታል። በመሆኑም ራቅ ብላ ወደ ወንዙ አቅጣጫ ለመንሸራሸር ወሰነች። ክላውስን ታገኛት ይሆናል።



ካባ መሳይ ካፖርቷን ለበሰችና ወደ አሰበችበት ለመሄድ ወጣች። ሙሉዋ ጨረቃ ደማቅ ብርሃኗን ሰጥታለች። አኔት ሜዳው ጫፍ ከደረሰች በኋላ መለስ ብላ የረጋውን በረዶ ተመለከተች። በረዶው ላይ ያረፈው የእግሯ ኮቴ ታያት – ልክ በህልሟ ያየችውን ሰውዬ ኮቴ መስሎ። የእርሱ በጣም ረጅም ጉዞ መሆኑ ብቻ ነው ልዩነቱ። ትንሹ ጨለማ ቤት ለመድረስ ዓለምን አቋርጦ የመጣ ይመስላል – ያ ሁሉ ጉዞ ግን ከንቱ ነበር።

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት
## የተከፈተ በር



አኔት ብዙ ከተጓዘች በኋላ ወንዝ ከሚያሻግረው ትንሽ ድልድይ አጠገብ ደረሰች። ወንዙ በፀጥታ ነው የሚጓዘው። አካባቢው ጸጥታ ሰፍኖበታል። ንፋስ ስለ ቆመ ቅዝቃዜ ጀምሯል። ድልድዩ ላይ የረጋው በረዶ የሚያሙለጨልጭ መሆኑን አኔት ልብ አላለችም። ድንገት ስለ አንሸራተታት የድንጋጤ ዋይታ አሰማችና ወደ ፊት ተንደረደረች።

ቁርጭምጭሚቷ አካባቢ ከደረሰባት ጉዳት የተነሣ ለጊዜው አዞራት፤ ሕመምም ተሰማትና ለሁለት ደቂቃዎች ያህል ያለ እንቅስቃሴ በረዶው ላይ ተጋደመች። ከነበረችበት ለመነሣት ብትሞክር ሕመም ተሰማትና «ዋይ» ብላ እንደገና ተኛች። ወለም ስለ አላት ለመቆም አልቻለችም።

ለጥቂት ጊዜ በጣም ፈራች። ብቻዋን ነው በተራራማው አካባቢ ያለችው። በዚያ ምሽት በመንገዱ የሚተላለፍ ሰው መኖሩ ያጠራጥራል። አየሩ በጣም ይቀዘቅዝ ጀመር። መጠለያ አለበት ስፍራ ካልደረሰች እንደ በረዶው ቀዝቅዛ መሞቷ ነው።

ረጋ ብላ ስታስብ፥ ካለችበት ትንሽ ወደ ተራራው ከፍ ብሎ መንገዱ መታጠፊያ አጠገብ ጫካው ውስጥ አንድ ቤት መኖሩን አስታወሰች። እንጨት ቆራጭ የሆነ አንድ ልጅ እግር ሰውዬ ከነሚስቱ ይኖርበታል።



እንደ ምንም በእጆቿና በጉልበቷ እየዳኸች እዚያ ቤት ብትደርስ፥ ሰዎቹ በበረዶ ጋሪያቸው እቤቷ ያደርሷት ነበር። ቤቱ በጣም እሩቅ ስለሆነ፥ ቶሎ ጉዞ መጀመር ይኖርባታል።

የአበጠ እግሯን ከኋላዋ እየጎተተችና ሕመሙ እየተሰማት በበረዶው ላይ ትድህ ጀመር። እንቅስቃሴ ባደረገች ቁጥር በጣም ነበር የሚያማት። በመሆኑም ብዙ ሳትጓዝ በጣም ደከማት። እጆቿ ከምሩ በረዶ ውስጥ ይሰምጡባት ጀመር፥ በዐይኖቿ እንባ ግጥም አለ። በአቅራቢያው ወደ አለ ቤት ትደርስ ይሆን?

እንደ ምንም ብላ መንገዱ መታጠፊያና ጫካው መግቢያ አጠገብ ደረሰች። እዚያ ሆና ቤቱ ታያት። እሩቅ አይደለም፥ በመስኮቱ የመብራት ብርሃን ይታያል።

እቤቱ ደረጃዎች አጠገብ እስክትደርስ ቀስ እያለች ተጓዘች። አንድ ሰው መጥቶ በሸክም ወደ ቤት ያገባኛል በሚል ተስፋ ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ ተጣራች፤ ግን ማንም ብቅ አላለም። እንደ ምንም ታግላ ደረጃዎቹን ከወጣች በኋላ ቤቱ በር ሥር ደረሰች። ጥቂት አረፍ ካለች በኋላ ተንጠራርታ በሩን አንኳኳች።

ማንም ብቅ አላለም። ያ ትንሽ ቤት በዙሪያው እንደተቆለለው በረዶ ጸጥ፥ እረጭ ብሏል። እንደገና ተንጠራርታ ያላትን አቅም በማጠራቀም በኃይል አንኳኳች።

ከውስጥ ምንም ድምፅ አይሰማም፥ እንቅስቃሴም የለም። ለእርዳታ የሚደርስ እርምጃ ወደ እርሷ አልመጣም።

በጣም ስለ ፈራች እንደ ምንም በአንድ እግሯ በመቆም እጆቿን ጨብጣ በሩ መሰበር እስኪቃጣው አንኳኳች፥ የሚቻላትን ያህል እየጮኸች አንገጫገጨችው። የቤቱን አለመከፈት እውነተኛ ምክንያት ስትረዳ ደረጃዎቹ ላይ ተቀምጣ በፍርሃት አለቀሰች። ቤቱ ባዶ ነው፥ በሩ ተቆልፎአል። በመስኮት የሚታየው መብራት ሌባ ለማስፈራራት የተደረገ ነበር። ቤቱ ውስጥ ማንም የለም።

ተራራማው አካባቢ የምትኖር ልጅ ስለሆነችና በቅዝቃዜ ምክንያት ስለ ሞቱ ሰዎች ታሪክ ስለምትሰማ፥ ለጥቂት ደቂቃዎች ደነገጠች፥ ቀስ በቀስ ድንጋጤው ስለ ለቀቃት በትክክል ታስላስል ጀመር።

ባለቤቱቹ የመተላለፊያውን መብራት እንደ በራ ከተዉት በዚያው ምሽት ወደ ቤታቸው ይመለሱ ይሆናል። ርቀው ከሄዱ ግን፥ በጣም ስለሚርቅ ያመሹ ይሆናል። ብርዱ ጣቶቿን ያደነዝዛቸው ጀመር።

ትንሽ ከአረፈች በኋላ እየዳኸች ወደ ኋላ ለመመለስ ትችል ይሆናል። ነገር ግን በአቅራቢያው የምታገኘው ቤት በጣም፥ በጣም እሩቅ ነው። የበረዶው ዝናብም በቀላሉ የሚያቆም አይመስልም።

ያም ሆነ ይህ ትንሽ ጠብታ እንደ ምንም ለመንቀሳቀስ ትሞክራለች። ያ ብቻ ነው ያላት ብቸኛ ምርጫ።

ፊት ለፊት ያለውን በረዷማ አካባቢ በተስፋ መቁረጥ ተመለከተች። እስከተዘጋው በር ድረስ ስለሄደው የአንድ ሰው የእግር ኮቴ የተመለከተችውን ህልም እንደገና አስታወሰች።

ቁጭ ብላ ስትጠብቅ ስለሌላም ነገር አሰበች። ወደ አንድ ሰው ቤት ሄዶ የተዘጋ በር በማንኳኳት ጊዜ በሩ ባይከፈት የሚፈጠረውን ስሜት ለመጀመሪያ ጊዜ ተገነዘበች።

እርሷ ያንኳኳችው ለጥቂት ጊዜ ነው! ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ለብዙ ዓመታት ሲያንኳኳ ኖሯል፥ ይህን እርሷም ታውቃለች።

ቤቱ ሰው የሌለበት ባዶ መሆኑን ስለ ተረዳች ማንኳኳቷን ተወች። ምናልባት ባለቤቶቹ ቤት ውስጥ ሆነው ማንኳኳቷን እየሰሙና እየተያዩ፥ «አንድ ሰው በራችንን በማንኳኳት ላይ ነው! አሁን አንከፍትለትም። ያልሰማን መምሰል አለብን!» በማለት ላይ ቢሆኑስ?

በድርጊታቸው እንዴት ትቆጣ ነበር? እንዴትስ ትጠላቸው ነበር? ይሁን እንጂ እርሷ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የምታደርገው ልክ እንዲሁ ነው! እርሱ ግን አልጠላትም። አሁንም በጣም ይወዳታል። ማንኳኳት ባይቀጥልም አሁንም ለመግባት ይፈልጋል። ይህንን ነው ሴት አያቷ የነገሯት።

ይህን እያሰላሰለች ለጊዜው ፍርሃቷንና ብቸኛነቷን እረሳችው። አሁን ግን አንድ ድምፅ የሰማች መሰላትና እራሷን ቀና ጆሮዋን ነቃ አድርጋ አዳመጠች።

በተራራማው አካባቢ የሚኖሩ ልጆች ሁሉ የሚያውቁትና የተለመደ ድምፅ ነው። የበረዶ መንሸራተቻ ድምጽ፥ ወዲያው የአንድ ልጅ ዝማሬ ተሰማት።



አንድ ሰው በጫካው ውስጥ እየተሹለከለከ በበረዶ መንሸራተቻ በመምጣት ላይ ነው። በጥቂት ሰከንዶች ውስጥ እርሷ አለችበት ቤት በር ላይ ይደርሳል። በጣም ከፈጠነ ልብ ብሎ ሳያያት አልፎ ይሄድ ይሆናል። አንድ ትንሽ የሰው ቅርጽ ወደ ሸለቆው ውልብ ሲል ታያት።

በጉልበቷ ቀጥ ብላ በመቆም፥ «ድረስልኝ። ቁምና እርዳኝ» አለች እጆቿን በአፍዋ ዙሪያ አድርጋና ድምጽዋን በማጉላት።

በሸርተቴ የሚጓዘው ሰው አቅጣጫውን በፍጥነት ለወጠና ቆመ። ከዚያም እግሩን ከበረዶ መንሸራተቻው አላቀቀና አኔት ወደአለችበት እየሮጠ፥

«ምንድን ነው ነገሩ? ምን ነው? ተጎድተሻል?» አለ ድምጹን ከፍ አድርጎ። ሉሲየን ነበር የመጣው። ሽማግሌ ጓደኛውን ለመጎብኘት ወደ ተራራው አካባቢ ወጥቶ ወደ ቤቱ በመመለስ ላይ ነው። የአኔት ጩኸት አስደንግጦታል። የተንበረከከው ሰው ማን መሆኑን በጨረቃይቱ ብርሃን ሲመለከት፥ ጣረ ሞት ያየ ይመስል ግትር ብሎ ቀረ።

አኔት ማንም ይሁን ማን የሚረዳት ሰው ስለ አገኘች ደስ አላት። ሰው የደረሰላትና ሕይወቷ የተረፈ መሆኑን ከማሰብ በስተቀር ሌላውን ሁሉ ለጊዜው እረሳችው። ሮጦ እንዳያመልጣት የፈራች ይመስል እጆቿን ዘርግታ ካፖርቱን ያዘችና፥

«ሉሲየን ስለ ደረስክልኝ በጣም ደስ ብሎኛል። እግሬ ተጎድቷል፥ ለመራመድ አልችልም። የዚህ ቤት ባለቤቶች እስኪመጡ ድረስ እዚህ ብቆይ በቅዝቃዜው እንደ በረዶ ደርቄ እሞት መስሎኝ ነበር። ወደ ቤቴ ልትወስደኝ ትችላለህ፥ ሉሲየን? በጣም በርዶኛል» አለች በሚንቀጠቀጥ ድምፅ።

ሉሲየን በፍጥነት ትልቅ የብርድ ካፖርቱን አወለቀና አለበሳት። ከዚያም አጠገቧ ቁጢጥ በማለት የቀዘቀዙ እጆቿን እያሻሸ፥

«በበረዶ መንሸራተቻ ይዤሽ ልሄድ አልችልም፥ አኔት። እንዳልሸከምሽም በጣም ትልቅ ነሽ። ግን በአምስት ደቂቃ ውስጥ ቤት ደርሼ የበረዶ ጋሪ እና የሚሞቅ ልብስ ይዤ እመጣለሁ። በግማሽ ሰዓት ውስጥ ቤትሽ ትደርሻለች» አለ ረጋ ባለ አነጋገር።

እሩጥ፥ እሩጥ ድምፅህን ከፍ አድርገህ ዘምር የሚሰኝ የደስታ ስሜት ተሰማው! ህልሙ እውን ሆነለት። ለአኔት አንድ ቁም ነገር

ሊያደርግላት ነው። እርዳታውን ፈልጋለች። ከእንግዲህ ምናልባት ይቅርታ ታደርግለትና ያለፈ መጥፎ ፀባቸውን ትረሳ ይሆናል።

«ካፖርትህን ለእኔ ሰጥተህ ስትሄድ አይበርድህም፥ ሉሲየን?» ዝቅ ባለና ድካም በተጫነው ድምፅ።

ሉሲየን ፈጠን ብሎ ጃኬቱን በማውለቅ ራሷ ላይ ጠቀለለላት፤ የሚጠቅማት ቢሆን ሸሚዙንም ቢጨምርላት በወደደ። ብርዱ እንደ ጦር እየወጋው በበረዶ መንሸራተቻው ወደ ቤቱ ተጓዘ። ከደስታው ብዛት ብርዱ እምብዛም አልተሰማውም። እቤቱ ደርሶ በፊት በር ሲገባ፥ እናቱ እጆቹ ራቁታቸውን ሆነውና አፍንጫው በቅዝቃዜ ቀልጠው ስለአየች ደነገጡ።

አኔት በሉሲየን ሻካራ ካፖርት ጥቅልል ብላ ትጠብቀዋለች። በሃያ አምስት ደቂቃዎች ውስጥ ይመለሳል። በእነዚያ ደቂቃዎች ውስጥ የምታሰላስላቸው ብዙ ነገሮች አሉ።

አንደኛ፥ ሕይወቷ ተርፎአል። ሉሲየን በጊዜው ነው የድረሱልኝ ጩኸቷን ሰምቶ የደረሰላት። ብቻዋን የሆነች በሚመስላት ጊዜ ሁሉ የሚጠነቀቅላት እግዚአብሔር ነው ያድናት ዘንድ ሉሲየንን የላከላት።


ሁለተኛ፥ የተዘጋ በር ምሥጢር ተገልጦላታል። የልቧን በር ብትከፍት ምን እንደሚሆንና ገና ባይገባትም ስለ አንድ ነገር እርግጠኛ ናት። ከእንግዲህ ኢየሱስን ውጭ አታቆመውም። ዓይኖቿን ከድና እራሷን ወደ በረንዳው መደገፊያ በማስጠጋት፥

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ በሩን አሁን በመከፈት ላይ ነኝ። በሬን ዘግቼ ለረጅም ጊዜ ከውጭ እንድትቆም ስለአደረግሁ አዝናለሁ። እባክህ አሁን ግባ። ሉሲየንን ስለጠላሁት አዝናለሁ። እባክህ እንድወደው አድርገኝ። ስለሰበርኩበት ትንሽ ፈረሱ ልነግረው ከተገባኝ እባክህ ጠንካራ አድርገኝ። ሉሲየን እንዲደርስልኝ ስለላከከው አመሰግናለሁ። አሜን» አለች።

እንግዲህ አኔት ልብና ሕይወት በር ላይ ለረጅም ጊዜ ቆሞ ይጠብቅ የነበረው ጌታ ኢየሱስ ገብቷል። ይቅርታ ሊያደርግላትና ሕይወቷ እንዲለወጥ ሊረዳት ይወዳል። ይህ አስደናቂ ነገር በሕይወቷ ሲከናወን ሊያይ የቻለ ማንም አልነበረም። አኔት እራሷ እንኳን ለውጡን ልብ አላለችውም። ነገር ግን በዚያች ሌሊት፥ በላይ በሰማይ፥ በእግዚአብሔር የሕይወት መዝገብ ላይ የአኔት ስም ተጽፎአል። አንድ ሌላ ልጅ ልቧን ከፍታ ጌታ ኢየሱስን ስለአስገባችው መላእክት ተደሰቱ።



# ምዕራፍ አሥራ ስምንት
# ነገሮች መስተካከል ጀመሩ



«አደረግሁት! ከእንግዲህ የሚሆነውን አውቀዋለሁ» አለች አኔት በአሳቧ።

ልቧ በፍጥነት መምታት ስለ ጀመረ ራሷን ለማበረታታት ስትል ከዋክብት የሞሉበትን ሰፊ ሰማይና በዙሪያዋ ያሉ ተራሮችን ትመለከት ጀመር። እንዴት ግዙፍና ሳይለወጡ የኖሩ ነገሮች ናቸው! ግዝፈታቸው እርሷንና ፍርሃቷን ኢምንት አሳከሏቸው። ፍርሃቱ ያልፋል፥ ይረሳልም። ከዋክብቱና ተራሮቹ ግን ለዘላለም ይኖራሉ።

የበረዶ ጋሪ የሚስብ አንድ የሰው ቅርጽ ከመንገዱ መጠማዘዣ አቅጣጫ እየሮጠ መጣ! ሉሲየን ነው። ሌላ ካፖርት ይዟል፥ መናገር እስኪያቅተው ድረስ ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ እያለበት፤

«ነይ አኔት፤ እግርሽን ዘርግተሽ ለመቀመጥ እንድትችዪ፥ ትልቁን የበረዶ ጋሪ ነው ያመጣሁልሽ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ እቤትሽ አደርስሻለሁ» አለ።

ሊያነሣት እጁን ዘረጋላት። እጇን ሰብሰብ አደረገችና፥ «ለአንድ ደቂቃ ታገሠኝ። ወደ ቤት ጉዞ ከመጀመራችን በፊት አንድ ነገር ልነግርህ እፈልጋለሁ። አየህ ሉሲየን። ያን ዕለት ፈረስህን ጥላ የሰበረችው ድመቷ አልነበረችም! እኔ ነኝ። በውድድሩ አሸንፈህ

ሽልማት እንድታገኝ ስላልፈለግሁ፥ ሆን ብዬ ነው የሰባበርኩት። ያን ያደረግሁት ዳኒ ላይ አደጋ ስለ አደረስክበት ነበር። ይቅርታ አድርግልኝ ሉሲየን» በተጣደፈና ሀፍረት በተጫነው ንግግር።

ሉሲየን ብድግ ብሎ በመቆም ባልተለመደ ሁኔታ ተመለከታት። ለማለት የፈለገውን የመናገር ዕድል ማግኘቱ ግን አስደሰተው። የሰማው ነገር በማስቆጣት ፈንታ እጅግ ቀለል እንዲለው አደረገው። አኔትም እንደ እርሱ መጥፎ ነገር አድርጋለች። ይቅርታ ካደረገላት፥ እርሷም ይቅርታ ማድረጉ ይቀልላት ይሆናል። የትንሽ የፈረስ ቅርጽ መሰበር፥ ከአንድ ትንሽ ልጅ እግር ጋር ሲነጻጸር ምንም አይደለም። ያም ቢሆን፥ ያን ዕለት የተፈጠረው ሁኔታ አቀራረባቸው።

የተሰማውንና የሆነውን ነገር ሁሉ በቃላት መግለጡ አልሆነለትም። በጎርናና ድምፅ በአጭሩ ሳቀና፥ «ምንም አይደለም፥ አኔት! የሆነው ነገር ሊያስጨንቅሽ አይገባም። ጋሪው ላይ ውጪ» አላት። ከዚያም ካፖርቱን በደንብ ደረበላትና ጋሪው ላይ ከፊት ተቀመጠ። በበረዶው ጋሪ በፍጥነት እየተንሸራተቱ ተራራውን ወርደው እነ አኔት ደጅ ደረሱ። ስፍራው በበረዶ ተሸፍኗል።

አኔት በእግሮቿና በእጆቿ እየዳኸች እንደ ምንም የቤቷን ደረጃዎች ወጣችና በሩ አጠገብ በአንድ እግሯ በመቆም ዘወር ብላ ሉሲየንን አየችው። የበረዶ ጋሪውን እየሳበ በቀስታ ወደ ኋላው በመመለስ ላይ ነው።

ልቧን ለኢየሱስ ፍቅር ከፍታለች፤ ያ ለሉሲየንም ልብን መክፈት ማለት ነው፤ ምክንያቱም የክርስቶስ ፍቅር ማንንም ከውጭ አያስቀርም።

«ሉሲየን፥ ና ወዲህ» አለች ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፥ «ና ግባና ሴት አያቴን እያት። ያገኘኸኝ አንተ መሆንህን ስትሰማ በጣም ደስ ይላታል።» የፊት ለፊቱን በር እስከ መጨረሻው ከፈተችና ከሉሲየን ጋር ወደ ውስጥ ገቡ።

ሴት አያታቸው አኔትን በማየታቸው የደስታ ድምፅ አሰምተው ከወንበራቸው ብድግ አሉ። እርሳቸውና ሌሎቹ ቤተሰባቸው ተጨንቀው ነበር። አባቷ ሊፈልጓት ወደ ተራራው አካባቢ ወጥተዋል። ሴት አያቷ አኔትን ሊቆጧት አፋቸውን ቢከፍቱ የእግሯን መጎዳት አዩና ተዉት።



በዚያ ፈንታ ደግፈው ሶፋው ወንበር ላይ አስቀመጧትና ፋሻ መሳይ ማሰሪያ ነገር ለመፈለግ ሄዱ።

ሲመለሱ ነው ሉሲየን በሀፍረት አቀርቅሮ በር ላይ መቆሙን ልብ ያሉት። በመገረም ቆመው። ለጥቂት ጊዜ ሁለቱም በዝምታ ተያዩ። ሰዎች እንዲያቀርቡት ያለው ከፍተኛ ጉጉት ፊቱ ላይ ይገለጻል። ይህን በመረዳት በሁለት እጃቸው እቅፍ አድርገው ወደ ሞቃቱ ምድጃ እየወሰዱት፥ «እንኳን ደህና መጣህ ልጄ፤ ና ከእኛ ጋር ተመገብ» አሉት።

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ በሩ እንደገና ተከፈተና የአኔት አባት ገቡ። ቀደም ሲል ሁለት ልጆች በበረዶ ጋሪ ሜዳውን ሲያቋርጡ አይተዋል። አሁን ደግሞ ጋሪውን በሩ ላይ ስለ ተመለከቱ አኔት ደህና መሆኗን ነው የገመቱት። ርቃ ሄዳ እንደ ነበር ሲሰሙ በምሽት እንዲያ በማድረጓ ትንሽ ገሠጹአትና እምድጃው አጠገብ አብረዋቸው ተቀመጡ። ሴት አያታቸው ለእራት ያዘጋጁትን ልዩ ልዩ ምግብ አቀረቡና ሁሉም በዝምታ ተመገቡ።

ከምድጃው የሚወጣው ሙቀት የምሽቱን ቅዝቃዜ አባርሮ ምቾትን የፈጠረላቸው ቢሆንም፥ እንቅልፍ እንቅልፍ የሚል የድካም ስሜትና ዝምታ አሳደረባቸው። ሉሲየን ምድጃው ላይ ትርክክ ያለውን ፍም እየተመለከተ፥ ያ ሁኔታ ለዘላለም ቢኖር ተመኘ። በዝምታው መሀል በሩ በአንድ ነገር ሲጏጠጥ ተሰማ።

«ድመቲቱ ክላውስ ናት!» አለች አኔት ብድግ ለማለት እየሞከረች። አልቻለችም፤ የተጎዳው እግሯ ያዛት። ሴት አያቷ፥ አባቷና ሉሲየን ናቸው በፍጥነት ሄደው በሩን የከፈቱት።

ክላውስ ጅራቷን በኩራት ወደ ላይ ቀጥ አድርጋ ወደ ክፍሉ ገባች። ገና የተወለደና የሚያምር የድመት ግልገል በአፍዋ ይዛለች። ማንኛቸውንም አልተመለከተቻቸውም። በቀጥታ ዳኒ ወደተኛበት አመራችና ዘላ ፀጉራማው አልጋ ልብስ ላይ ወጣች። ከዚያም የከበረ ስጦታዋን ዳኒ እራስ አጠገብ አስቀመጠችና ሚያው እያለች በፍጥነት ወደ በሩ ሄደች።

«ሌላ ግልገል ይዛ ልትመጣ ነው፥» አሉ የአኔት አባት በሩን እየከፈቱላት፥ «በሩን ከፍት መተው አለብን» አሉ የአኔት ሴት አያት፥ በሩን ክፍት ትተው የምሽቱ ብርድ እያንቀጠቀጣቸው ተቀመጡ።

ክላውስ በፍጥነት እየተራመደች መጣችና በአፍዋ የያዘችውን ግራጫ ነጠብጣብ ያለበትን ነጭ ግልገል አስቀምጣ ወደ ውጭ ተመለሰች።

«ይህ የመጨረሻዋ ይሆናል ብለን ተስፋ እናድርግ፥» አሉ ሴት አያታቸው። ይህን ያሉት በሩ ክፍቱን ቢቆይ ብርዱ የሚጎዳቸው መሆኑ እና እዚያች ጠባብ ጎጆ ውስጥ ከዳኒ ጋር ከሦስት ድመቶች በላይ ማሳደጉ እየታሰባቸው ነው። ሌሎቹ ወደ በሩ አፍጥጠው ይጠባበቁ ስለነበር ምንም አልተናገሩም። የዳኒ ድመት የፈለገችውን ታደርጋለች፤ የሚከለክላት የለም።

ለሦስተኛ ጊዜ በበረቱ ጥግ መጣች። የአሁኑ አካሄዱ ቀስና ረጋ ያለ ነው። ሥራዋ አብቅቷል። ያመጣችው የመጨረሻ ግልገል ነጭና እርሷን የሚመስል ነው። ሦስቱንም ግልገሎች በፊት እግሮቿ መሀል ሰብሰብ በማድረግ ዳኒ ደረት ላይ ተኝታ በምላሷ ታፀዳቸው ጀመር።

«ሉሲየን፥ በሩን ዝጋው። አንተ ደግሞ (የአኔትን አባት)፥ ድመቶቹን የምንከትበት ቅርጫት መሳይ ነገር ፈልግ። ልጁ አየር አጥቶ ይታፈናል አሉ» የአኔት አያት በእፎይታ አነጋገር።

«ጠዋት ብናደርገው ይሻላል፥ እማማ። ዛሬ ባሉበት ይደሩ። የሚመቻቸውን ስፍራ ክላውስ ታውቃለች። ዳኒም በክላውስ ነገር አይቸገርም» አሉ የዳኒ አባት ብድግ እያሉ።

ቀስ ብለው የክላውስን የፊት ቀኝ እግር ከዳኒ ጉንጭ ላይ ዘወር አደረጉና የከብቶቹን በረት ሊዘጉ ወደ ውጭ ወጡ።

ሉሲየን ወደ ቤቱ ለመሄድ ብድግ በማለት፥ ወደ አኔት አያት ተጠግቶ ለስንብት እጁን ዘረጋና፥

«ልሂድ፤ ወደ ቤታችሁ እንድገባ ስለ ፈቀዱልኝ አመሰግናለሁ። የአኔት እግር ቶሎ እንደሚድን ተስፋ አደርጋለሁ» አለ። ሴትዮዪቱ እጁን በሁለት እጆቻቸው በመያዝ ትኩር ብለው አዩትና፥ «አዎ፥ መሄድ አለብህ። እንደገና መምጣት እንዳለብህ ግን አትርሳ። ሁልጊዜ በደስታ እንቀበልሃለን» አሉት። ተሰናብቷቸው ወጣ።

አኔት ዳኒን ከእንቅልፉ ለመቀስቀስ አሰባ፥ ሴት አያቷ ስለማይፈቅዱላት ዝም አለች። ሴት አያቷ ዕቃዎችን ማጠብ እስኪጀምሩ ጠብቃ፥ በአንድ እግሯ ዘለል፥ ዘለል በማለት ወደ አልጋው ተጠጋችና «ዳኒ» አለች። በሹክሹክታ፥ ወፍራም ፀጉሩን ከግንባሩ ወደ



ኋላ እየዳሰሰች። ዳኒ በሰፊው ተንፍሶ እጆቹን ከራሱ በላይ አወናጨፈ እንጂ አልነቃም።

«ዳኒ» አለች ድምጽዋን ከፍ አድርጋ። ትንሽ ቆንጠጥ አደረገችው። ብሩህ ዐይኖቹን ገለጠና ትኩር ብሎ አያት።

«ድመትህ መጥታለች ዳኒ። ስጦታም አምጥታልሃለች!»

ዳኒ እቅፉ ውስጥ ያሉትን ድመቶች ፀጉር ዳሰሰ። ገና በደምብ ስለአልነቃ በሰማው ወይም በተመለከተው ነገር አልተደነቀም። በእውን ወይ በሕልም ዓለም መሆኑንም አልለየም።

«ሦስት አይጦች ይዛለች፥» አለ።

«አይደሉም ዳኒ፤ አይጦች አይደሉም። የሚያማምሩ ሦስት የድመት ግልገሎች ናቸው። በረት ውስጥ ወልዳ አመጣችልህ። የአንተ ናቸው ዳኒ — ክላውስ ያመጣችልህ ስጦታዎች» አለች አኔት።

ዐይኖቹን ከድን ግልጥ እያደረገ ድመቶቹን አየና፥ «እንደምትመጣ አውቃለሁ፤ እግዚአብሔርን ለምኜው ነበር» አለ።

አኔት ዳኒ አልጋ ሥር በርከክ ብላ ክላውስን ከነግልገሎቿ ባሉበት ሁኔታ እቅፍ ካደረገቻቸው በኋላ፥

«ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልቤ እንዲገባ ጠየቅሁት፤ ገባልኝ። ሁለት ጸሎቶቼ በአንድ ምሽት ተመለሱልኝ ማለት ነው» አለች በሹክሹክታ።

ዳኒ አልሰማትም። የክላውስ ጅራት ጫፍ አፉ ላይ እንደ አረፈበት እንደገና እንቅልፍ ወሰደው።

## ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ
## አኔት አንድ ፍልሚያ ድል አደረገች



አኔት በሚቀጥለው ማለዳ ከእንቅልፍዋ ስትነቃ የተጎዳው እግሯ እብጠት ጠፍቷል፣ ሕመሙም ድኗል። ይህ የሆነው ሴት አያቷ ማታ እግሯን በጣም እቀዘቀዘ ውኃ ውስጥ በተነከረ ጨርቅ ስለ አሰሩላት ነው። ሌሊቱን ሲዘንብ ያደረው በረዶ ወደ ከብቶች በረት በሚወስደው መተላለፊያ ላይ ተከምሯል። የአኔት አባት ያን መጥረግ ስለነበረባቸው እቤት ነው የዋሉት።

አኔት፣ ዳኒ፣ ድመቲቱ ክላውስና ሦስቱ ግልገሎቿ የእነዳኒን ሴት አያት አስቸግረዋቸዋል። በመሆኑም ከሰዓት በኋላ ሁሉም ሣር ድርቆሽ ማከማቻው ቤት ውስጥ እንዲጫወቱ ነገሯቸው።

በዚሁ መሠረት ዳኒ ድመቶቹን ቅርጫት ውስጥ ከተተና ይዟቸው ሄደ። አኔትም አብራቸው በመሄድ የሴት አያቷን መጽሐፍ ቅዱስ እፊቷ ዘርግታ ሣሩ ላይ በደረቷ ተኛች።

ከመጽሐፉ ለማንበብ የፈለገችው ኢየሱስ በር ማንኳኳቱን የሚገልጸውን ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ፣ ስለዚህ ጉዳይ የሚናገረው ጥቅስ የሚገኘው በመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ መሆኑን ሲናገር ሰምታ ስለነበር ቶሎ አገኘችው። ጥቅሱ ራእይ ምዕራፍ 3 ቁጥር 20 ሲሆን፣



«እነሆ፣ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፣ ወደ እርሱ እገባለሁ፤ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል» ይላል።

አኔት ያነበበችውን በቃሏ አጠናችው። አብሮ ስለ መብላት የሚናገረው የመጨረሻ ክፍል ግን አልገባትም። ከሴት አያቷ ጋር ስትሆንና ምቹ ጊዜ ስታገኝ ትርጉሙን ልትጠይቃቸው ወሰነች። ከዚያም ጋደም ብላ ዳኒንና ግልገሎቹን ትመለከት ጀመር።

የልቧን በር ለጌታ ከፍታለታለች። እርሱም ገብቶ ልቧ ውስጥ ይኖራል። ሴት አያቷ ያለችው ነገር በአኔት ሕይወት በትክክል በመፈጸም ላይ ነው። መራራነትና ቁጣ እንደ ጥላ ጥለዋት ስለ ጠፉላት፣ አኔት ለሉሲየን ይቅርታ ማድረግ አልከበዳትም። ራስ ወዳድ፣ ግድየለሽና እምነት የማይጣልባት ልጅ መሆኗን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አሳይቷታል። አሁን አኔትን የሚያሳስባት ነገር ሉሲየን ይቅርታ ያደርግልኝ ይሆን? የሚለው ነው።

ስለ ሰበረችው የፈረስ ቅርጽ ነግራዋለች፤ የተቆጣ አይመስልም። መቼም ሽልማቱ አምልጦታል። ከሽልማቱ የበለጠና ልታደርግለት የምትችለው ነገር መኖሩን ተረዳች፤ በእርግጥ ከፈለገች።

ሉሲየን የሠራቸው የኖኅ እንስሳት እርሷ ዘንድ አሉ። ወደ ትምህርት ቤታቸው ዲሬክተር ብትወስዳቸውና ማን እንደ ሠራቸው ብትነግራቸው፣ ሉሲየን ጥሩ ቅርጻ ቅርጾችን ለመሥራት የሚችል መሆኑን ይረዳል። ቢዘገይም እንኳን ተፈጥሮ የነበረውን ነገር ከተረዳ፣ ሉሲየንን ይሸልመው ይሆናል።

እንደ አሰበችው ለዲሬክተሩ ብትነግራቸውና ሌሎች ልጆችም ቢሰሙ ስለ እርሷ ጥሩ አመለካከት አይኖራቸው ይሆናል ብላ በጣም ፈራች። ይህን እንደ ወሰነች ስለ አዲሱ መጽሐፍዋ ማሰቡ ወደፊት የማያሻት መሆኑን ተሰማት። ምክንያቱም ደስታዋን አርቆባት ነበር።

ብዙም ሳይቆይ ስለ መሸ ልጆች እራት ለመብላት ተሰባሰቡ። በመኝታ ጊዜ ዳኒ የድመቲቱ ግልገሎች አልጋው ውስጥ እንዲተኙ ስለ ፈለገና ሴት አያቱ ደግሞ ከብቶቹ በረት ውስጥ እንዲያድሩ ስለ ፈለጉ ብዙ ትርምስ ተፈጥሮ ነበር። በመጨረሻ ሁለቱም ክርክራቸውን ስለ ተዉ ድመቶቹ አልጋ ሥር እንዲያድሩ ተደረገ። ሴት አያታቸው በጣም

ስለ ደከማቸው ባለመደገፊያ ወንበራቸው ውስጥ አሸለቡ። አኔት ወንበሯን ሳብ ስታደርግ ያሉበት ቤት በር ተንኳኳ።

አኔት ብድግ ብላ ስትከፍት ሉሲየንን ቆሞ አየችው። በሀፍረት እጆቹን ያፍተለትላል። አኔትም አፈረች። አንደኛው ቀድሞ እንዲናገር በመጠባበቅ ግራ በተጋባ ሁኔታ ቆመው ቀሩ።

ሴት አያታቸው በዝምታቸው በመገረም ቀና ብለው አዩዋቸውና፥ «ሉሲየን ግባ፥ እንኳን ደህና መጣህ» አሉ።

ሁለቱም ከተቀመጡ በኋላ የመጣው አኔት እግሯን የተሻላት መሆን አለመሆኑን ለመጠየቅ እንደሆን ሉሲየን ተናገረ። «በጣም ተሽሎኛል፥ አመሰግናለሁ» አለች አኔት መሬት መሬቱን እያየች። ሴት አያቱ በመነጽራቸው አናት ሁለቱንም ትኩር ብለው አዩዋቸውና።

«አኔትና ሉሲየን፥ ፀባቻሁን ትታችሁ ጥሩ ልጆች መሆን አለባችሁ። ሉሲየን ትንሽ አጥፍተሃል፤ ሆን ብለህ ግን አይደለም። በፈጸምከው ጥፋት ምክንያት ግን ብዙ ችግር ደርሶብሃል። ያለፈን ነገር ማሰቡ ጥሩ አይደለም። ከእንግዲህ መጎበዝና ወደነበራችሁበት ሁኔታ መመለስ አለባችሁ። አኔት ይቅርታ ማድረግንና ደግ መሆንን መማር አለብሽ። ከሌሎች የተሻልኩ ነኝ እያልሽ ማሰብሽን ተዪ» አሉ።

«እኔ እንደዚያ አላስብም። ይቅርታ አድርጌለታለሁ፤ ትናንት ማታ ተራራው ላይ በነበርን ጊዜ። ይቅርታ ማድረጉ አስቸጋሪ አልነበረም። እኔም ሉሲየንን በድዬዋለሁ። ይህንኑ በደሌን ስነግረው፥ ይቅርታ እንደሚያደርግልኝ ገልጦልኛል። አይደለም እንዴ ሉሲየን? ስለዚህ ሁለታችንም እኩል ጥፋተኞች ነን» አለች።

«አዎ፥» አለ ሉሲየን ዝግ ብሎ። «የአኔቴ ጥፋት እንደ እኔ በደል የከበደ አይደለም። ሌላ ፈረስ ልሠራ እችላለሁ። ለዳኒ አዲስ እግር ልሠራለት ግን አልችልም። ሰው ሁሉ አንቺን ጥሩ ልጅ ናት ይሉሻል፥ ይወዱሻል። እኔን ግን ማንም አይወደኝም።»

«እንዳልከው ይሆን ይሆናል። ምክንያቱም ሰው ሁሉ አንተ ያደረግሽውን እንጂ እኔ የሠራሁትን ስለማያውቅ ነው። ያደረግሁትን ለትምህርት ቤታችን ዲሬክተር ልንገር አልንገር እያልኩ ዛሬ ከሰዓት በኋላ ሳስብ ነበር። ደፍሬ የማደርገው ግን አይመስለኝም» አለች አኔት።



አኔትና ሉሲየን እርስ በርሳቸው ነበር የሚያወሩት፥ የሉሲየን ሴት አያት በዝምታ ሲያዳምጧቸው ቆዩና፥

«አኔት፥ ለሉሲየን ይቅርታ ማድረግ ያለብሽ መሆኑ የተሰማሽ እንዴት ነው? ከሁለት ቀን በፊት በፍጹም ይቅርታ እንደማታደርጊለት ነግረሽኝ ነበር» አሉ።

«ለምን መሰለሽ አያቴ? እንደ ነገርሽኝ ልቤን ከፈትኩ። ሁሉም ነገር አንቺ እንዳልሽው ሆነ። ኢየሱስ ወደ ልቤ እንዲገባ ከጠየቅሁት በኋላ፥ ነገሮች ሁሉ አስቸጋሪ አልሆኑብኝም» አለች አኔት።

«የልብሽን በር ብትከፍቺ እንዳልሽው እንደሚሆን አውቄአለሁ። ኢየሱስ ከታላቅ ፍቅሩ ጋር ወደ ልባችን ሲገባ፥ ክፋትና ራስ ወዳድነት ይጠፋሉ። ኢየሱስ የሚያስወግደው ሌላም ነገር አለ። መጽሐፍ ቅዱሴን አቀብዪኝ አኔት» አሉ ሴት አያቷ።

ሴት አያቷ መጽሐፍ ቅዱሳቸውን ከአኔት ተቀብለው በቀስታ ሲያገላብጡ ቆዩና 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 18 እና 19ን ከፍተው ለአኔት ሰጧት። እርሷም ድምጽዋን ከፍ አድርጋ፦

«ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ በፍቅር ፍርሃት የለም፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና፥ የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም» የሚለውን አነበበች።

«አዎ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ፍቅሩን ይዞ ወደ ልባችን ሲገባ፥ ክፋትንና ራስ ወዳድነትን ያወጣቸዋል። ፍርሃትንም ያባርረዋል። በፍጹም ፍቅሩ ሲወደን፥ ምንም እንዲጎዳን አይፈቅድም። ስለዚህ ልንፈራ አይገባም።»

ሉሲየንና አኔት ትንሽ ካሰላሰሉ በኋላ፥ ተያዩና ፈገግታ ተለዋወጡ። አኔት ወደ ቁም ሳጥኗ ሄዳ ለገና የተሰጣትን ብስኩት በማምጣት ሁለት ላይ ሰበረችውና ግማሹን እንደ ሰላም መሥዋዕት ለሉሲየን ሰጠችው። ሉሲየን የተሰጠውን በደስታ እየበላ ሁለቱም ቁጭ አሉ። አኔት ግን አሁንም የሚያሳስባትና የሚያስጨንቃት ነገር አለ። ከመቼውም ይልቅ ትክክለኛው ነገር የቱ መሆኑን ብታውቅም፥ ልትፈጽመው አልፈለገችም።

ከዚያ በኋላ ሉሲየን ብዙ ሊቆይ ስለአልፈለገ ወደ ቤቱ ሄደ። አኔትም ወደ መኝታ ክፍሏ አመራች።

«አኔት» ብለው ተጣሩ አያቷ፥ «ኢየሱስ ወደ አንቺ ሲመጣ እንድታደርጊ የሚነግርሽን መፈጸም እንጂ፥ ሁለተኛ አንቺ የምትፈልጊውን ማድረግ የሌለብሽ መሆኑን እንዳትረሺ።» አሏት።

«እሺ፥ አያቴ፥» አለች አኔት በኀዘን ስሜት። መኝታ ክፍሏ ከገባች በኋላ አልጋዋ ሥር ተንበረከከችና፥

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ አንተ የምትለኝን ለመፈጸም እፈልጋለሁ። ለትምህርት ቤታችን ዲሬክተር መንገር ካለብኝ ፍርሃቴን ትቼ ጠንካራ እንድሆን እርዳኝ» አለች።

አኔት መኝታዋ ውስጥ የገባችው ቀለል ብሏት ነው፥ ወዲያው እንቅልፍ ወሰዳት። በነጋታው በጣም በማለዳ ነው የነቃችው። በጨለማው አልጋዋ ላይ እንደ ተጋደመች በመስኮቷ ቀዳዳ የብርሃን ጨረር ታያት። ከአልጋዋ በፍጥነት ወርዳ መስኮቷን ብትከፍተው ብርሃኑ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ የነበረበትን ትንሽ የመኝታ ክፍሏን ሞላው።

ሴት አያቷ እንዳሉት፥ ሉሲየንን መጥላትና፥ ማድረግ የሚገባትን ነገር ከማድረግ መፍራት እንደ ጨለማ፥ ኢየሱስን ማስገባት ደግሞ መስኮቱን እንደ መክፈት መሆኑን አኔት አሰበች።

ትንሽ መኝታዋ ውስጥ ከተገላበጠች በኋላ ለባበሰችና ሴት አያቷ ቡና ወደሚያፈሉበት ወጥ ቤት በመሄድ፥

«አያቴ፥ ዛሬ ጠዋት ወደ ትምህርት ቤታችን ዲሬክተር ለመሄድ እፈልጋለሁ» አለች።

«ምንድን ነው? አኔት ወደ ትምህርት ቤቷ ዲሬክተር ለመሄድ ከፈለገች፥ ከእኔ ጋር እንሄዳለን። አይብ ይዤ በጋሪ ወደ ባቡር ጣቢያው እሄዳለሁ። አኔትን ዲሬክተሩ ቤት እተዋትና ስመለስ ይዤያት እመጣለሁ» አሉ የአኔት አባት ጫማቸው ላይ የተጣበቀውን በረዶ በሩ ላይ እያራገፉ።

የአኔት ፊት በደስታ በራ። ብትቆይ ኖሮ ምናልባት የፍርሃት ስሜት ያስቸግራት ነበር።

ጋሪው ላይ አባቷ ጎን ተቀምጣ፥ በዕቃ የተደረገው አይብ ከኋላቸው እየተንገጫገጨ ጉዟቸውን ቀጠሉ። አኔት የኖኅ መርከብ እንስሳዎች ቅርጾችን በመሀረብ ቋጥራ ብትይዛቸውም በጣም ደስተኛ አይደለችም።



ለትምህርት ቤቱ ዲሬክተር የምትነግራቸውን ማሰብ አቅቷታል! በጣም ቢቆጧትስ? በቀላሉ ይቆጡ ይሆናል።

«የትምህርት ቤቱን ዲሬክተር የፈለግሽው ለምንድን ነው? የምታጠኚው ነገር የሌለሽ መሆኑ አሰለቸሽ?» አሉ አባቷ በድንገት።

አኔት እራሷን ላይ ላያቸው ደገፍ በማድረግ፥

«አይደለም። የምነግራቸው አንድ ነገር አለ። ምሥጢር ነው አባዬ» ብላ ልጓም የያዘ እጃቸውን ያዝ አደረገችው። ብልህና ጥሩ አባት ስለሆኑ ፈገግ አሉ እንጂ ሌላ ነገር አልጠየቋትም። የአኔት አባት በጣም ሥራ የሚበዛባቸው ሰው ናቸው። የእርሻ ሥራቸው ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድር ገቢ የሚያስገኝ ይሆንላቸው ዘንድ ከማለዳ እስከ ምሽት ይሠራሉ። ቁጭ ብለው ልጆቻቸውን በወጉ የሚያነጋግሩበት ጊዜ እንኳን አልነበራቸውም። ያን ለእነ አኔት ሴት አያት ትተውላቸዋል። ይሁን እንጂ ፊታቸውን እያዩና የሚነጋገሩትን እየሰሙ የሚያስቡትን ለመረዳት ይችሉ ነበር። ፀጥታ በሰፈነበት የከብቶች በረትና ጫካ ውስጥ እየሠሩ ስለ እነርሱ ያስባሉ፥ ይጸልዩላቸውማል። አኔት በአንዳች ነገር ምክንያት ታዝን እንደ ነበር ልብ ብለዋል። አሁን ግን ደስተኛና ሰላሟ የተሟላ ሆኖ ስለ ተመለከቱ ደስ ብሏቸዋል።

አኔትና አባቷ ጉዟቸውን በጸጥታ ቀጥለው እሚሄዱበት ከተማ ደረሱ። «በይ ውረጂ፤ ከግማሽ ሰዓት በኋላ እመጣልሻለሁ» አሉ አባቷ ጋሪውን አቁመው።

እርሷ ከወረደች በኋላ ጋሪው ጉዞውን ቀጠለ። አኔትም በፍርሃት ልቧ እየዘለለ ወደ ትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ቢሮ አመራች። እዚያ ደርሳ ለማንኳኳት ስለ ፈራች ለረጅም ጊዜ ቆመች። ዲሬክተሩ በመስኮት አይተዋት በሩን ባይከፍቱላት ኖሮ በሩ ላይ ቆማ ሳትውል አትቀርም ነበር።

«ግቢ፥ ግቢ፥» አሏት ዲሬክተሩ በትሕትና። ብዙ ጊዜ አብረው ቁጭ እያሉ ወደሚያስጠኗት ክፍል አስገቧት። ተማሪ ሕፃናትን ይወዷቸዋል። ትምህርት በሌለበት ዕለት ሕፃናቱ በየቤታቸው ሲውሉ ይናፍቋቸዋል። በየጊዜው እንዲጎበኟቸውም ይፈልጋሉ። አኔት በቀጥታ ወደ ጠረጴዛው በመሄድ መሀረቧን በመፍታት ትንንሾቹን የኖኅ መርከብ እንስሳት ቅርጾች በመደዳ አስቀመጠቻቸውና፥

«ሉሲየን ነው የሠራቸው፤ አያምሩም?» አለች ዲሬክተሩን እያየች።

ሰውዬው ቅርጾቹን አንሥተው በአድናቆት እየተመለከቱ፥ «በጣም አምረው ነው የተሠሩት። በሉሲየን ዕድሜ ላለ ልጅ እነዚህ አስደናቂ ሥራዎች ናቸው። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እነዚህን የመሳሰሉ ቅርጻ ቅርጾችን እየሠራ በመሸጥ ገንዘብ ሊያገኝ ይችላል። እንዲህ ሊሠራ እንደሚችል አላውቅም ነበር። በቅርጻ ቅርጽ ውድድር ለምን አልተሳተፈም?»

«ተሟትፎአል። ስለ እርሱ ልነግርዎት ነው የመጣሁት። ለውድድሩ የሠራው የፈረስ ቅርጽ ነበር። እርሱ ሳያይ ሰበርኩበት። ምክንያቱም ዳኒ ላይ ባደረሰው ጉዳት ምክንያት ተናድጄበት ነበር። አሁን ግን በድርጊቴ ተጸጽቻለሁ። አሁን የተከሰተውን ነገር ለእርስዎ ስለ ነገርሁ በዚህ ሥራው ሊሸለም ይችል ይሆን?» አለች።

ዲሬክተሩ ትኩር ብለው ተመለከቷት። ፊቷ ቀላ፥ አቀርቅራ ወለሉን ትመለከት ጀመር።

«ሌላ ሽልማት የለኝም። ሁለት ሽልማቶች ብቻ ነበሩ። አንዱ ለፔሬ፥ ሌላው ለአንቺ ተሰጠ» አሉ ዲሬክተሩ።

«እንግዲያው ፔሬ የወሰደው ሽልማት ለሉሲየን መሰጠት አለበት። ሽልማቱ የተመደበው ከሁሉ የተሻለ ሥራ ላቀረበ ልጅ ነበር። የሉሲየን ሥራ ደግሞ ከፔሬ ሥራ በጣም ይበልጣል።»

«የለም፥ እንደዚያ ልናደርግ አንችልም። ፔሬ ውድድሩን ያሸነፈው በትክክለኛው መንገድ ነው። መልሰን ልንወስድበት አንችልም። በእርግጥ ሉሲየን ሽልማት እንዲያገኝ ከፈለግሽ፥ አንቺ ያገኘሽውን ሽልማት ልትሰጪው ይገባል። በአንቺ ምክንያት ነው ሽልማቱን ያጣው፤ አይደለም?»

አኔት «አዎ፥ በእኔ ጥፋት ነው» አለችና ለአንድ ደቂቃ ያህል አሰላሰለች። ለእርሷ የተሰጣት ሽልማት የስዊዘርላንድ ተራራዎች ሁሉ ያሉበት ቆንጆ መጽሐፍ ነው። በለስላሳ ወረቀት ተጠቅልሎ መሳቢያዋ ውስጥ ተቀምጧል። ይህ መጽሐፍ ካሏት ነገሮች ሁሉ የበለጠ የምትወደው ብርቅ ዕቃ ነበር። በቀላሉ እምቢ ልትል ትችል ነበር። ዲሬክተሩም እንድትሰጥ እንደማያስገድዷት ታውቅ ነበር። ነገር ግን ሴት አያቷ ስለ ፍጹም ፍቅር ነግረዋታል። ኢየሱስ ክርስቶስም አሁን ከፍጹም ፍቅሩ ጋር ውስጧ ስለሚኖር፥ ምንም ነገር እንድትነፍግ አይፈቅድላትም።



«እሺ፥» አለች አኔት በመጨረሻ።

«በጣም ጥሩ!» አሉ ዲሬክተሩ፥ በአሸናፊነት እየተመለከቷት ቀደም ሲል አኔት ለሦስት ደቂቃዎች ለአፍታ ዝም ብላ በምታሰላስልበት ጊዜ ትልቁን ፍልሚያ ድል አድርጋ እንደ ነበር በመረዳትም። «ያሸነፍሽውን ሽልማት ትምህርት ቤቱ ሲከፈት ታመጪልኛለሽ። ክፍል ውስጥ እሸልመውና ልጆች የቅርጽ ሥራውን ያዩለታል» አሉ።

«በጣም ጥሩ፥» አለችና በጣም መጥፎ ልጅ ናት ብለው ገምተዋት እንደሆነ ለመረዳት በሀፍረት ቀና ብላ አየቻቸው። እርሳቸው ግን በፈገግታ ነበር የተመለከቷት። ዲሬክተሩ እንደ ቀድሞው እንደሚወዷት ተረድታ ከቤታቸው ወጣች።

ከአባቷ ጋር በጋሪው ተሣፍራ ወደ ቤቷ ጉዞ ቀጠለች። ቤቷ ስትደርስ ደረጃዎቹን ወጥታ በረንዳው ላይ ቆመች። ዳኒም አያትና የድመት ግልገሎቹን አቅፎ አጠገቧ ቆመ። ሴት አያታቸው ወጥ ቤት ውስጥ እራት በመሥራት ላይ ናቸው። ፀሐይቱ ሸለቆው አካባቢ ደርሳለች።

«ዛሬ ጠዋት ሸለቆው በጥላ የጠቆረ ነበር፥» አለች አኔት በአሳቧ፥ «አሁን ግን የፀሐይ ብርሃን ሞልቶበታል።» ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልቧ ገብቶ ፍቅርን፥ ብርሃንንና ድፍረትን እንደ ሞላበት ማለት ነው።

## ምዕራፍ ሃያ
## ሉሲየን አንድ አሳብ አለው



ሉሲየን ዝግ እያለ ወደ ተራራማው አካባቢ በመውጣት ላይ ነው። አኔትም አብራው ትጓዛለች። ከዚያ ቀደም ከትምህርት ቤት ወደ ቤታቸው ሲመለሱ እንኳን አብረው የተጓዙበት ጊዜ አልነበረም። ዛሬ ያ ሁኔታ ተለውጧል።

ያ ጠዋት ሉሲየን ደስ የተሰኘበት ጊዜ ነበር። የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ትምህርት ቤቱ ዝግ በነበረበት ሰሞን በጣም ጥሩ የእንጨት ቅርጽ ሥራ መመልከታቸውን ገለጡ። ያን ሥራ ለሠራ ልጅ ሌላ ሽልማት ለመስጠት መወሰናቸውንም አስታወቁ። ለሽልማቱ የተጠራው ሉሲየን መሆኑን የተመለከቱ ሁሉ ተገረሙ። አኔት የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር ታሪኩን በጠቅላላው የሚገልጡ መስሏት ነበር። ምንም አለመናገራቸውን በተረዳች ጊዜ ከሥጋቷ እፎይ አለች። ሕፃናት ሁሉ ሽልማት ያስገኙትን ትንንሽ እንስሳት ለመመልከት ሰብሰብ አሉ። ከሁሉም ይልቅ ድምፁን ከፍ አድርጎ አድናቆቱን የገለጠው ጠቃጠቆ ፊቱ ፒሬ ነው። ሥራዎቹ ዘግይተው ባይቀርቡ ኖሮ በውድድሩ አሸናፊ እንደማይሆን ተናግሮ ዕድለኛነቱን ገለጠ። በዚህ አባባሉ በስፍራው የነበሩት ሁሉ ተስማሙ። ሁሉም የተሸለመውን መጽሐፍ ለማየት ፈለጉ። ሴቶቹ ልጆች «አኔት የተሸለመችውን መጽሐፍ ይመስላል» አሉ። አኔት ሉሲየን ከአሁን አሁን «አዎ፥ የአኔት መጽሐፍ ነው» ይላል ብላ በስጋት ትጠብቀው ነበር።



እርሱ ግን፥ «እውነት? ይመስላል እንዴ?» እያለ ልጆች ሳያዩት አኔትን ይጠቅሳት ነበር።

ልጆቹ ሁሉ ሄደው ብቻቸውን ሲሆኑ፥ ሉሲየን መጽሐፉን ወደ አኔት ዘረጋና «መሸለሜ ጥሩ ነው፤ እኔ ግን መጽሐፉን የራሴ ላደርገው አልፈልግም፤ እውነቴን ነው፥ አልፈልግም አኔት። የአንቺ መጽሐፍ ስለሆነ፥ ብወስድብሽ ደስተኛ አልሆንም» አለ።

«የለም፥ አይሆንም፤ መውሰድ አለብህ። አሁን የአንተ መጽሐፍ ነው» አለች እራሷን እየነቀነቀች።

«መልካም፥ እንግዲያው መጽሐፉ የሁለታችንም ነው። በጋራ ብንጠቀምበት የሚሻል ይመስለኛል። በዚህ ወር የእኔ ቢሆን፥ በሚቀጥለው የአንቺ ይሆናል፤ ከዚያ የእኔ፥ ቀጥሎ የአንቺ። እንደዚህ ቢሆንስ?»

አኔት መጽሐፉ እንዲመለስላት ትፈልግ ስለነበር፥ ፊቷ በደስታ በራ።

«ጥሩ ነው። በየወሩ የመጀመሪያ ዕለት እንለዋወጣለን» አለች።

«እዚህ የእንጨት ክምር ላይ እንቀመጥና እንየው» አለ ሉሲየን። በረዶውን ከግንዱ ላይ ጠረግ አድርገው ቁጭ በማለት የመጽሐፉን ገጾች ያገላብጡ ጀመር። ሉሲየን ከዚያ በፊት አላየውም ነበር። ተራራዎችን ይወድዳል፤ ስለ አስጎብኝነት ሙያ የተጻፉ መጻሕፍትንም ያጠናል። በዚሁ መሠረት ወደ ተራራ ለመውጣት የሚረዱ የተለያዩ ዘዴዎችን ያስረዳት ጀመር።

ሞቃቱ የቀትር ፀሐይ እያቃጠላቸው ነጫጭ ተራራዎች በሩቁ አጅበዋቸው በነበሩበት ለረጅም ጊዜ ተቀመጡ። ምሳቸውን እስኪረሱ ድረስ በሥዕሎቹ ተመስጠው ነበር። አንድ የትንሽ ልጅ ድምፅ ከኋላቸው መጥቶ፥ «አኔት፥ አያቴ ምሳ ከተዘጋጀልሽ ቆየ፥ ነዪና ብዪ ትልሻለች። እኔ ፋንታዬን በልቻለሁ» ሲል ነው ብዙ መቀመጣቸውን የተረዱት።

ዳኒ ነበር፥ በጣም ድክም እንዳለው ክራንቹ ላይ ተደግፎ የጠራት። አኔት ከተቀመጠችበት በቅጽበት ብድግ አለችና፥

«ዳኒ፥ እዚህ ድረስ እርቀህ መምጣት አልነበረብህም። ወደ ቤት ተመልሰህ ለመሄድ አትችልም። አሁኑኑ ጉዞ መጀመር አለብን» አለች።

ወደ ቤታቸው ለመሄድ ተራራማውን መንገድ ተያያዙት። ትንሽ እንደ ሄዱ ዳኒ ደከመው።

ብቻውን ይህን ያህል መንገድ በክራንች ተጉዞ አያውቅም። ጉዞ የጀመረው እንቱን በቅርብ እንደሚያገኛት አስቦ ነበር። በኋላ ሉሲየን ተሸከመው፤ አኔት ደግሞ ክራንቹን ያዘችለት።

ሉሲየን ዳኒን ቤቱ ድረስ ነው የተሸከመው። ይህ ሁሉ ሲሆን ማናቸውም ምንም አልተናገሩም። ምክንያቱም አኔትና ሉሲየን ምንም እንኳን ፀባቸውን በእርቅ ቢፈቱም፥ ዳኒ አሁንም ሽባ ነው፤ የቀድሞ እግሮቹን የሚመልስለት የለም።

«እግሮቼን በጣም አሞኛል፥ አልጋዬ ላይ አስተኚኝ አኔት» አለ ዳኒ ተሸክማው የቤቱን ደረጃዎች ስትወጣ።

አልጋው ላይ አጋደመችውና እንዲያጫውቱት ድመቶቹን በሙሉ አመጣችለት። ከዚያም አጠገቡ ተቀመጠችና ከድንች የተሠራ ምግቧን በላች። አባታቸው ወደ ሥራቸው ሄደዋል። ሴት አያታቸው አኔትን ስለ መቆየቷ ከገሠጹአት በኋላ፥ ወደ ወጥ ቤት ሄዱ። አኔትም ምግቧን ከጨረሰች በኋላ ወደዚያው ተከተለቻቸው። አያቷ ከወተት የሚሠራ ክሬም ያዘጋጁ ስለነበር አኔቱም በሥራው ረዳቻቸው።

«ምን ሆነሻል አኔት? ያዘንሽ ትመስያለሽ» አሉ አያቷ እንደ አዩአት።

አኔት ለረጅም ጊዜ ዝም ብላ ከቆየች በኋላ፥ «አያቴ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልቤ እንዲገባ ብጠይቀው ሉሲየንን እንድወደው እንደሚያደርገኝ ነግረሽን ነበር። እንዳልሽው ባለፈው ሳምንት ሁሉም ነገር ደህና ነበር። አሁን ግን የዳኒን እግሮች መታመምና የቀድሞ ብርታቱን ሳስታውስ፥ ክፉ አሳቦች ሁሉ እንደገና ይመጡብኛል» አለች።

«አዎ፥ እንደዚያ እንደሚሆን እጠብቃለሁ። በሕይወትሽ በየቀኑ ደስ የማይሉ፥ የሚያናድዱና የራስ ወዳድነት አሳቦች ተመልሰው ወደ ልብሽ ለመግባት ያንኳኳሉ። በዚህ ጊዜ እራስሽ ልትከላከያቸው አትሞክሪ። ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅሩን በመሙላት እንዲረዳሽ



ጠይቂው። ስለ ኢየሱስ ፍቅር በየዕለቱ ከመጽሐፍ ቅዱስሽ አንብቢ። ልብሽን በእግዚአብሔር ቃል ከሞላሽው፥ መጥፎዎቹ አሳቦች የሚቆዩበት ስፍራ አያገኙም።»

«በተለይ የትኛውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ላንብብ?» ብላ ጠየቀች አኔት።»

«ሁሉንም። የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ታሪክ አንብቢና ሰዎችን ሁሉ የወደደበትን ሁኔታ አስላስዪ። እርሱ ወደ ልብሽ እንዲገባ በጠየቅሽው ጊዜ ያ ፍቅር አብሮት የገባ መሆኑን አስታውሺ።»

«እሺ፥» አለች አኔት በአሳቧ፥ «ከዛሬ ጀምሬ አደርገዋለሁ። በየጠዋቱም ኢየሱስ ሰዎችን ስለወደደበት ሁኔታ ከመጽሐፍ ቅዱስ አነብባለሁ።»

ሉሲየንም እንዲሁ እያሰበ ነው ወደ ቤቱ የሄደው። ዳኒ በጣም ደክሞ ስለአየው አዝኗል። ለአኔት ግን ሁኔታዎች ተስተካክለውላታል። ያለፉ ስሕተቶችን አርማለች። ሉሲየን ግን የዳኒን እግር ወደ ነበረበት ሊመልሰው አይችልም።

«ለምንድን ነው አኔት ይቅርታ ያደረገችልኝና እንዲህ የተለወጠችው?» አለ ሉሲዬን ለራሱ። እንዲህ ያለውን አሳብ ብዙ ጊዜ ነው ደጋግሞ ያሰላሰለው። መጀመሪያ አኔት ይቅርታ ያደረገችለት ከበረዶው ክምር ስላነሣት መስሎት ነበር። አሁን ግን ከዚያ የበለጠ ምክንያት መኖሩን ነው የተረዳው። የልብን በር ለኢየሱስ ስለ መክፈት ተናግራለች። ሴት አያቷም ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ወዳድነትንና ክፋትን የሚያስወግድ መሆኑን ገልጸዋል። ተራራ ላይ የሚኖሩት ሽማግሌም ስለ ይቅርታ ተናግረዋል።

ብቻ የአኔትን ባህርይ የለወጠው የልቧን በር ለኢየሱስ መክፈቷ ነበር። በጣም ትእቢተኛና ቂመኛ ነበረች። አሁን ግን ትሑትና ደግ ሆናለች። ይህ ሁኔታዋ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ታሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠና ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረ ብቻ ሳይሆን፥ አሁንም የሚሠራ መሆኑን ሉሲየን እንዲገነዘብ ያደረገው።

የሚራመደው በቀስታ ቢሆንም፥ ወደ ቤቱ ተቃርቧል። ከሃያ ደቂቃዎች በፊት፥ ከአኔት ጋር እንጨት ክምር ላይ ተቀምጠው በነበረ ጊዜ ሰማዩ ሰማያዊና ጸጥ ያለ ነበር። አሁን ግን ቁልል ደመና

ከተራራዎች ጀርባ በመመሰቃቀል ላይ ነው። ቀዝቃዛ ንፋስ ሽው ማለት ጀምሯል።

«የበረዶ ንፋስ ነው፤ ዛሬ ሌሊት በረዶ ይጥላል፥» አለ ሉሲየን ለራሱ።

ድንገት በመጣው ቀዝቃዛ ንፋስ የተነሣ ከብቶች በረት ውስጥ መተራመስ ጀምረዋል። ሉሲየን በሩን ከፍቶ ገባ፥ እናቱ እራታቸውን በመመገብ ላይ ናቸው።

«ና ወዲህ፥ በጣም ቆየህ። ከሰዓት በኋላ የማትማር በመሆንህ ደስ ብሎኛል። ደመናው በመከማቸት ላይ ስለሆነ በረዶ መጣል ሳይጀምር አይቀርም። የምን መጽሐፍ ነው የያዝከው?» አሉት እናቱ።

«የተሸለምኩት ነው። የትምህርት ቤቱ ዲሬክተር በእረፍት ጊዜዬ የሠራሁትን ቅርጽ አይተው ሸለሙኝ።»

«በጣም ጥሩ። ስለተሰባበረው ሥራህ አውቀዋል?» አሉ እናቱ።

«አዎ፥» አለና የሚወያዩበትን ርእስ ለወጠው። የአኔትን ምሥጢር ሊደብቅላት ስለፈለገ ነው ይህን ያደረገው።

ሉሲየን ከፊት ለፊት አለው ክፍል ውስጥ ተቀምጦ እንጨት በቢላዋ እየፋቀ ያስብ የነበረው ስለ አኔት ነበር። እናቱ ማድ ቤት ውስጥ ልብስ ስለሚተኩሱ ብቻውን ነው። አኔት፥ «ኢየሱስን ወደ ልቤ እንዲገባ ጠየቅኩት» ነበር ያለችው። ሴት አያቷም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቂት ጥቅሶችን አንብበውለታል። ምናልባት እነዚያን ቃላት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልጎ ያገኛቸው ይሆናል። እንደገና ሊያነባቸውም ይወዳል።

ወደ መጽሐፍ መደርደሪያው ሄደና አቧራ የጠገበውን የቤተሰብ መጽሐፍ ቅዱስ አወረደው። እናቱ ብዙ ጊዜ አያነቡትም፤ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያውቀው ከትምህርት ቤቱ የተማረውን ነው። የአኔት ሴት አያት ያነበቡት ጥቅስ፥ መጽሐፉ መጨረሻ ገጾች አካባቢ ሳይሆን አይቀርም ብሎ አሰበ። የመጽሐፉን ገጾች ሲያገላብጥ፥ ስለ ፈዋሹ ኢየሱስ ትምህርት ቤት የተማራቸውን ታሪኮች አገኘ። እውሮች እንዲያዩ እንዳደረገ፥ ለምፃሞችን እንዳነፃና ሙታንን እንዳስነሣ። አዎ፥ አንድ ሽባ እንዲራመድ ያደረገበትም ታሪክ ተጽፎአል!



«ኢየሱስ ክርስቶስ ዛሬም ሕያው ከሆነና የአኔትን ልብ ከለወጠ፥ ዳኒንም እንዲራመድ ሊያደርገው ይችላል» አለ ለራሱ።

ሉሲየን ከልጅነቱ ጀምሮ ጸልዮ አያውቅም፤ አንዳንዴ ብቻ ለመጸለይ መቻሉን ለማሳየት ብቻ በመጸለይ ለእናቱ ይገልጽላቸው ነበር። ብድግ ብሎ ወደ ከብቶች በረት በመሄድ ሣር ማጠራቀሚያው ቆጥ ላይ ወጣ። ያ ስፍራ ቀደም ሲል ተደብቆ ያለቀሰበት ነበር። እዚያው ስፍራ ላይ ተንበረከከ።

በርን ለኢየሱስ መክፈት ማለት ምን ማለት መሆኑን ገና አልተረዳም። ቢሆንም እግዚአብሔር ቅርቡ እንደሆነና ሲጸልይ እንደሚሰማው አውቋል። በዚሁ መሠረት ስለ መፈወሳቸው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳነበባቸው ሰዎች፥ እግዚአብሔር ዳኒንም እንዲፈውሰውና እንደ ቀድሞው እንዲራመድ እንዲያደርገው ከልቡ ጸለየ።

በዚህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ሲጸልይ ቆየና ላሞቹ ወደ አሉበት ወርዶ ወተት አለበ። ያለበውን ወተት ይዞ ለመውጣት በሩን ሲከፍት በረዶውን በወጨፎ መልክ ወደ ጎን የሚነዳው ንፋስ ገፍትሮ ሊጥለው ነበር። እናቱ መስኮታቸው አጠገብ ቆመው የበረዶውን ጭጋግ በስጋት እየተመለከቱ፥

«እውነተኛው የበረዶ ውሽንፍር ጀመረ። የበረዶ ፋኖስ ይዘህ በመሄድ እኅትህን ብታመጣት የሚሻል ይመስለኛል። ገና በጊዜ መሸ፥» አሉ።

ወዲያውኑ ያሉበት ክፍል በር ተከፈተና የሉሲየን ታላቅ እኅት ማሪዬ ገባች። በረዶው ፀጉሯ ላይ ተከምሯል፥ የለበሰችውን ካፖርት ሰውነቷ ላይ ጥብቅ አድርጋ እንደ ያዘች ትንፋሿ ቁርጥ ቁርጥ እያለና እየሳቀች፥

«ከንፋስ ጋር እየታገሉ ያን ዳገት መውጣት እውነተኛ ትግል ነበር፥» እያለች በረዶውን ከልብሷና ከሰውነቷ ላይ አራገፈች። ጫማዋንም እየለወጠች፥ «በጣም ደክሞኛል! ሉሲየን ፋኖሱን ይዘህ ለምን አልመጣህልኝም? እማዬ እራት እንደ ተዘጋጀ እርግጠኛ ነኝ፤ በጣም ርቦኛል» አለች።

መመገቢያ ጠረጴዛቸው አጠገብ ተቀመጡ። ማሪዬ ጉንጮቿ በብርዱ እንደ ቲማቲም ቢቀሉም በደስታ ትስቃለች።

«ዛሬ ለእኔ በጣም ጥሩ ቀን ነበር። ወደምሠራበት ሆቴል ብዙ ሰዎች ይገቡና ይወጡ ነበር። እግሬ ያለቀ እስኪመስለኝ ድረስ ስሯሯጥ ነው የዋልሁት። ቢሆንም በጣም ጥሩ የገንዘብ ጉርሻ ነው ያገኘሁት። ተመልከቺ እማዬ» አለች ማሪዬ።

ከዚያም ገንዘቡን ለእናቷ ሰጠቻቻው፥ በደስታና በመደነቅ ተቀበሏት። እናቷ እንደ ጎረቤቶቻቸው ለእርሻ ሥራቸው የሚያውሉት ገንዘብ ቸግሯቸው ነበር።

«ይህን ሁሉ ማን ሰጠሽ?» አሏት እናቷ።

«አንድ ደግ ሰውዬ ነው የሰጠኝ። በጣም ታዋቂ ሰው ነው። የሆቴሉ ጌታ ሚስት ነግራኛለች። ማንኛውንም አጥንቱ የተሰበረ ሰው ሊያድን የሚችል አዋቂ ዶክተር ነው። ሐይቁ አጠገብ የራሱ ሆስፒታል አለው። ከመላው ስዊዘርላንድ ሰዎች ወደ እርሱ እየሄዱ ተፈውሰዋል» አለች።

ሉሲየን ደስታ ተናነቀው። ጠረጴዛው ላይ በደረቱ ተደገፈና፦

«ዳኒን ሊያድነው ይችል ይሆን?» ብሎ ጠየቃት። ማሪዬ ሉሲየንን በመገረም ተመለከተችው። ለዳኒ እስከ ዛሬ እንደሚጨነቅለት አላወቀችም።

«እኔ እንጃ! እንዲመረምረው ከፈለጉ ወላጆቹ ዳኒን ወደ ሐይቁ መውሰድ አለባቸው። ነገር ግን ለሕክምናው የሚከፍሉት ገንዘብ አይኖራቸውም። ዶክተሮች ብዙ ገንዘብ ነው የሚያስከፍሉት ሉሲየን። የዳኒ አባት ላሞቻቸውን በሙሉ እንዲሸጡ የሚያደርግ ገንዘብ የሚጠይቃቸው ይመስለኛል» አለች።

ወደ ሐይቁ! ከሸለቋማው አካባቢ እርቆ ለማያውቀው ሉሲየን የዓለም ጫፍ መሰለው።

«ግን፥ ግን፥ ማሪዬ ቤተሰቦቹ ዳኒን አንቺ ወደምትሠሪበት ሆቴል በጠዋት ሊወስዱት አይችሉም?» አለ ሉሲየን።

«በጠዋቱ ባቡር ይሄዳል። ሻንጣዎቹ ሁሉ ዛሬ ማታ መጥተዋል።»

«ታዲያ ዛሬ ማታ ሊወስዱት አይችሉም?» እንደገና ጠየቃት። ማሪዬ የሉሲየን ሁኔታ ቢያሳዝናትም፥ «በፍጹም አይችሉም ሉሲየን። በዚህ ውሽንፍራም በረዶ ውስጥ ትንሽ ልጅ ይዞ መሄድ! ያም ሆነ ይህ፥ ወደዚያ ሊወስዳቸው የሚችለው የመጨረሻ ባቡር አልፎአል።



መተላለፊያውም እንዲህ ባለው ሌሊት ይዘጋል። ፍጹም የማይቻል ነገር ነው። ከዚህም ሌላ፥ እንደነገርኩህ ለሕክምናው የሚሆን ገንዘብ የላቸውም። ስለዚህ ስለ ዳኒ መጨነቅህን ተው ሉሲየን። ሆነ ብለህ አልጎዳኸውም። በክራንቹ አማካይነት ዘለል ዘለል እያለና በሴት አያቱ እየተሞላቀቀ በደስታ ይኖራል!» አለች ማሪዬ።

ዝም አለ፥ ሉሲየን። እኅቱ ወደምትሠራበት ሆቴል ስለመጡ ሌሎች ሰዎች መናገሯን ብትቀጥልም አላዳመጣትም። ማድረግ ስለሚገባው ነገር ያሰላስል ነበር። ያሰበውን እንዳያደርግ የሚያደርጉ ሦስት ትልልቅ ችግሮች ከፊት ለፊቱ ተደቀኑበት።

ለዶክተሩ የሚከፈለው ገንዘብ ብዙ ነው፤ ሉሲየን ምንም የለውም። በአሳቡ ተራራው ላይ ወደሚኖረው ሽማግሌ በረረ። ብዙ ገንዘብ አላቸው፥ በችግሩ ካመኑበት ይሰጣሉ።

መተላለፊያው ይዘጋ ይሆናል። ሊሞክር ይችላል። ካልሆነለት ቢያንስ የሚችለውን አንድ ነገር ለመሞከሩ እርግጠኛ ይሆናል።

ዶክተሩ ወደዚያ ይመጣ ይሆን? ሐይቁ ዳር ወደአለው ጠቃሚ ሆስፒታሉ የሚወስደውን ባቡር ትቶ፥ ከማያውቀው ልጅ ከሉሲየን ጋር በአካባቢው ባለ ሌላ በቡር ይጓዛል? ከዚያስ ወርዶ አንድ የገበሬ ልጅ ለመመርመር በዚያ ወጨፎዋማና በረዶዋማ አየር ወደ ተራራማው አገር በእግሩ ይሄዳል?

በፍጹም የሚሆን ነገር አይመስልም። ነገር ግን ደግሞ ሊሆን ይችላል የሚያሰኝ ነገር አለ። ማሪዬ ዶክተሩ ጥሩ ሰው ነው ብላለች።

«እራቴን ጨርሻለሁ እማዬ። ወደ ፎቅ መውጣቴ ነው፥» አለ ሉሲየን።

# ምዕራፍ ሃያ አንድ
# የማይረሳ ሌሊት



ሉሲየን ወደ መኝታ ክፍሉ ከገባ በኋላ ሁሉንም ነገር በፍጥነት ያደርገው ጀመር። በከንቱ የሚያልፍ አንድ ደቂቃ እንኳን የለውም።

ካፖርቱን ለበሰ። ከሱፍ የተሠራ ባርኔጣውን እስከ ጆሮዎቹ አጠለቀ፥ ካሉት ጫማዎች ጠንካራውን አደረገ። ከዚያም እስከሚቀጥለው ዕለት ጠዋት ድረስ የማይመለስ መሆኑን የሚገልጥ ማስታወሻ ለእናቱ ጻፈ።

እርምጃው እንዳይሰማ እየተጠነቀቀ ወደ ወጥ ቤት ሄደና ዳቦና ደረቅ አይብ በኪሱ ከተተ፤ ክብሪትም ያዘ። ከዚያም የጓሮውን በር በቀስታ ከፍቶ ወደ ከብቶቹ በረት ሄደና ግድግዳ ላይ የተሰቀለውን ፋኖስ አበራ። የፋኖሱ ብርሃን እንደሚፈልገው ስለሆነለት ደስ አለው። በበረዶ መንሸራተቻው ሊጓዝ አሰበና በጣም ስለ ጨለመ በዚያ መጓዙ የማይመች መሆኑን በመገመት ተወው። በስተኋላው ወደ አለው የበረቱ የኋላ በር በቀጥታ ሄዶ ከፍቶ ወጣ። የውጩ ወጨፎአማ በረዶ ገፍትሮ ሊጥለው ነበር። እንደ ምንም ብሎ ጉዞውን በሰላም ጀመረ። ታላቁ የጀብዱ ሥራ ተጀመረ።

ንፋሱ ሜዳው ላይ እንዲህ ከበረታ፥ በተራራዎች መሀል ባለው መተላለፊያ ላይ ምንኛ የከፋ ይሆን? ብሎ አሰበ። በእርግጥ በንፋሱ ኃይል ተገፍቶ በረዶ ቁልል ውስጥ መቀበሩ የማይቀር ነው! ለማንኛውም እዚያ ሲደርስ ሁኔታውን ይረዳዋል። ይህ እንዳለ ሆኖ



ተራራው ላይ አለው ሽማግሌ ዘንድ የሚደርስበትን ሁኔታም በጥብቅ ሊያስብበት ይገባል።

ሜዳውን አቋርጦ ጫካው ውስጥ ሲገባ ትንሽ ተንፈስ አለ። ኃይለኛው ንፋስና በረዶው በመጠኑም ቢሆን ይቀንስለታል። መንገዱ ላይ የተከመረው በረዶ ጥልቀትም መጠነኛ ነው። ንፋሱ በዛፎች መሀል ሲያልፍ የሚያሰማው ድምፅ ቢያስፈራውም በፍጥነት ለመጓዝ ችሏል። በሽማግሌው መስኮት የሚወጣው ብርቱካንማ ብርሃን እስኪታየው ድረስ ወደ ተራራው ተጓዘ። እንደ ምንም ታግሎ ሽማግሌው ቤት ደረሰና በሩን አንኳኳ።

«ማን ነህ?» አሉ ሽማግለው ከውስጥ።

«እኔ ሉሲየን ነኝ።»

በሩ ወዲያውኑ ተከፈተና፦ ሽማግሌው ሉሲየንን ወደ ውስጥ አስገቡት። ከዚያም በመገረም ትኩር ብለው እየተመለከቱት፥

«ልጄ ሉሲየን፥ በዚህ መጥፎ አየርና ምሽት ለምንድን ነው የመጣኸው? ምን ተፈጠረ?» አሉ ሽማግሌው በኀዘኔታ ድምፅ።

ሉሲየን የድካም አተነፋፈሱ መለስ እንዲልለት አግዳሚው ወንበር ላይ ቁጭ አለ። በጣም ስለአስፈለገው ነው እንጂ ሽማግሌውን ገንዘብ ሊጠይቃቸው አልፈለገም ነበር።

«በጣም የሚያስፈልገው ሰው ካለ የሚሰጡት ብዙ ገንዘብ እንዳለዎት አንድ ጊዜ ነግረውኝ ነበር። በጣም ገንዘብ የሚያስፈልገው ሰው አግኝቻለሁ። ገንዘቡን ቢሰጡኝ የዳኒ እግር የሚድን ይመስለኛል» አለ ሉሲየን ሽማግሌውን እያየ።

«እንዴት ነው ሊድን የሚችለው?» አሉ ሽማግሌው ወደ ሉሲየን በጣም ቀርበው እያዩት።

«እናቴ እምትሠራበት ሆቴል ውስጥ አንድ ዶክተር አሉ። ሽባ ሰዎችን ያድናሉ፥ የተሰበረ አጥንትም ሊጠግኑ ይችላሉ። መጥተው ዳኒን እንዲመረምሩት ልጠይቃቸው በመሄድ ላይ ነኝ። ዶክተሩ ብዙ ገንዘብ እንደሚጠይቁ እናቴ ነግራኛለች።»

«አሁን በመሄድ ላይ ነህ? በዚህ የአየር ሁኔታ? አብደሃል እንዴ ልጄ? በዚህ የአየር ሁኔታ በተራራዎች መካከል ያለውን መተላለፊያ ልታቋርጥ አትችልም።»

«በበረዶ መንሸራተቻዬ ከተንዝኩ ላቋርጠው የምችል ይመስለኛል። ወጨፎአማው በረዶ የጀመረው ከጥቂት ሰዓት በፊት ስለሆነ የበረዶው ክምር ጥልቅ አይሆንም፤ ቶሎ ጉዞ ከጀመርኩ። ገንዘብ ከሌለኝ ግን መሄዴ ምንም ዋጋ የለውም!»

ሽማግሌው ከሉሲየን ስለ ሰሙት ነገር በጣም እያሰላሰሉ ለጥቂት ጊዜ ዝም አሉና፥

«ስለ ዶክተሩ እርግጠኛ ብሆን ገንዘቡን እሰጥህ ነበር። ግን ገንዘቤን በከንቱ ላጠፋው ወይም ላጣው አልፈልግም። ታማኝ ሰው መሆኑን በምን አውቃለሁ? የሰውዬው ስም ማን ነው ሉሲየን?

«ስማቸው ሞንሴር ጊቬት ነው። የታወቁ ሰው ናቸው ብላ እናቴ ነግራኛለች።»

«ሞንሴር ጊቬት!» አሉ ሽማግሌው እየደጋገሙ። ፊታቸው የገረጣ መሰለ። ብድግ ብለው፥ እራሳቸው ከሠሩት አንድ የእንጨት ቅርጽ ውስጥ ቁልፍ አወጡና ከአልጋው ኋላ ያለውን ቁም ሳጥን ከፈቱ። ገንዘብ የታጨቀበት አንድ የእግር ሹራብ አወጡና፥ «ሁሉንም ውሰድና ለዶክተሩ ስጠው። ሕፃኑን ካዳነው ገንዘቡን በሙሉ ሊወስደው እንደሚችል ንገረው። ንገረው፥ ንገረው ሉሲየን፥ ገንዘቡ የብድር ክፍያ ነው በለው» አሉት።

ሲናገሩ ድምጻቸው ስለ ተንቀጠቀጠባቸው ሉሲየን ቀና ብሎ በመገረም አያቸው። ገንዘቡን በማግኘቱ እጅግ ደስ አለው። ያን ያህል ብዙ ገንዘብ አይቶ አያውቅም። የተሰጠውን ገንዘብ ሸሚዙ ውስጥ ከከተተ በኋላ የኮቱንና የካፖርቱን ቁልፎች ቆልፉ እየወጣ፥

«እግዚአብሔር ይስጥልኝ፥ በጣም አመሰግንዎታለሁ። ውጤቱን መጥቼ እነግርዎታለሁ» አለ።

ሽማግሌው በሩ ላይ ቆሙና ፋኖሱን ከፍ አድርገው ይዘውለት ሉሲየን ከዐይናቸው እስኪሰወር አዩት። ሉሲየን በጣም ሳይርቅ ሽማግሌው፥ «ሉሲየን!» ብለው ተጣሩ። ሉሲየን እየሮጠ ተመልሶ መጣና፥ «አቤት፥ ምን ነው?» አለ።

«መልእክቱ አይጠፋህም አይደል?»



«አይጠፋኝም። ገንዘቡ የብድር ክፍያ ነው የሚለውን አይደል? አልረሳውም። ደህና ሁኑ» ብሎ ጉዞውን ለመቀጠል እርምጃ ሲጀምር ሽማግሌው እንደገና፥

«ሉሲየን!» ብለው ጠሩት። ሉሲየን ትንሽ ትዕግሥቱ እያለቀበት ተመልሶ መጣ። ቶሎ ለመሄድ ነው የፈለገው።

«አቤት፥» አለ ሽማግሌው ፊት ቆሞ።

«ለዶክተሩ ስለ እኔ ምንም እንዳትነግረው፥ እሺ? ስሜን አትንገረው፤ እሺ ሉሲየን?»

«ስምዎን እኮ አላውቀውም፥» አለ ሉሲየን።

«የት እንደምኖርም አትንገረው፥ ሉሲየን»

«እሺ አልነግራቸውም። የብድር ክፍያ ነው እላቸዋለሁ። ደህና ሁኑ» አለ ሉሲየን እየተጣደፈ።

ሽማግሌው እንደገና ይጠሩኝ ይሆናል በሚል ፍርሃት በፍጥነት ሮጠ። ጫካውን እንዳቋረጠ ቆም ብሎ ወደ ሽማግሌው ቤት እያየ ፋኖሱን አወዛወዘ። ሽማግሌው የቤቱን ውስጥ ብርሃን ጋርደው በራቸው ላይ እንደ ቆሙ፥ እሸክርክሪት በሚሠራው ኃይለኛ ንፋስ ውስጥ ደብዛዛ ቅርጽ ሆነው ይታያሉ።

ሉሲየን መፍጠን አለበት። በረዶው አሁንም በመውረድ ላይ ስለሆነ፥ በተራራዎቹ መካከል ያለው መተላለፊያ ይዘጋና ለማቋረጥ የማይቻል ይሆናል፤ እስከ አሁን ካልተዘጋ ማለት ነው።

ሉሲየን መተላለፊያውን በእግር ለማቋረጥ አይቻል ይሆናል ብሎ ስለ አሰበ፥ ወደ ቤቱ ጎራ ብሎ የበረዶ መንሸራተቻውን ለመያዝ ወሰነ።

ቤት ደርሶ፥ ከብቶች በረት ውስጥ ያለውን የበረዶ መንሸራተቻ ብድግ ሲያደርግ በሩ ተከፈተና እናቱና እኅቱ ማሪዬ ፋኖስ ይዘው ገቡ። ይህን ጊዜ ሉሲየን የበረዶ መንሸራተቻውን ግድግዳው ላይ አስደገፈና ከትልቋ ላም ኋላ ወለሉ ላይ በደረቱ ተኛ።

«እውነትሽን ነው ማሪዬ! ሉሲየን እዚህ የለም። ወደ ዶክተሩ የመሄድ ክፉ አሳብ ተፀናውቶት ነበር። ይሄኔ በተራራማው መንገድ ላይ ይፍገመገማል። ጅል አይደል? የበረዶ መንሸራተቻውንም አልወሰደም። የአኔት አባት እንዲፈልጉት እንጠይቃቸው ይሆን?

በእግሩ ብዙ ርቆ ሊሄድ አይችልም፤» አሉ እናቱ የያዙትን ፋኖስ ከፍ አድርገው የበረቱን ውስጥ እየቃኙ።

«እውነትሽን ነው፤ እንደዚያ ብናደርግ ይሻላል። የአኔት አባት በበረዶ መንሸራተቻ ተከትለው አደገኛ ከሆነ ስፍራ ከመድረሱ በፊት ሊይዙት ይችላሉ። እንሂድና እንጠይቃቸው» አለች ማሪዬ።

እነርሱ በፍጥነት ወደ አኔት አባት ሲሄዱ፤ ሉሲየን ከተኛበት ብድግ አለ። መፍጠን አለበት፤ የሚያባክነው ጊዜ የለም።

እናቱና እኅቱ ካፖርት እስኪደርቡና ጫማ እስኪያደርጉ ሁለት ወይም ሦስት ደቂቃ ይወስድባቸዋል። በዚያ ውሽንፍራም አየር አኔት አባት ቤት ለመድረስ አሥራ አምስት ደቂቃ ያህል ይጓዛሉ። ሌላ አሥር ደቂቃ ደግሞ የሄዱበትን ታሪክ ለአኔት አባት ሲነግሯቸው፤ እንዲሁም እርሳቸው ፋኖሱን ሲይዙ፤ ጫማቸውን ሲያደርጉና የበረዶ መንሸራተቻን ሲያነሡ ያልፋል። ሉሲየን ይህን ሁሉ አሰላና፤ እርሱን የመፈለጉ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ግማሽ ሰዓት ያህል ጊዜ መኖሩን አረጋገጠ። ይበቃል፤ ግን ሉሲየን ገና ልጅ ነው፤ የአኔት አባት ደግሞ ወፍራምና በበረዶ መንሸራተቻ በመሄድ ከሉሲየን ይልቅ ይፈጥናሉ።

ሉሲየን በቀስታ ከከብቶች በረት ውስጥ ወጥቶ ፋኖሱን እንደገና አበራና በረዶ መንሸራተቻው ላይ ሆኖ በፍጥነት ይንሸራተት ጀመር። የበረዶው ወጨፎ ዐይኖቹን ሙሉ በሙሉ አሳስገልጥ ስለአለው አቀርቅሯል።

ሜዳውን አቋርጦ እንደ መጠለያ እሚያገለግለው ጫካ ውስጥ ገባ። የጫካው ውስጥ መንገድ ፊት ለፊቱ ተዘርግቷል። ያን አልፎ በረባዳዎቹ ሜዳዎች ላይ በፍጥነት ተጓዘ። በአካባቢው ያለው ንፋስ ቀለል ያለ ስለሆነ ቀና ብሎ ፊት ለፊት ለማየት ይችላል።

ነዋሪዎቹ በተዉት አንድ መንደር መሀል አለፈ። አንድ ሰው አይቶ ወዴት እንደሚሄድ የሚጠይቀው እየመሰለው ዙሪያውን በፍርሃት ተመለከተ። እንደው ፈራ እንጂ፤ እንዲያ ባለው ምሽት ከቤቱ የሚወጣ የለም። በበረዶ እተሸፈነው ተራራ አጠገብ ያለውን የገበያ ሜዳና ድልድዩ አጠገብ ያለውን የከብት ርቢ ጣቢያ አልፎ ትንፋሹን ሰብሰብ ለማድረግ ቆም አለ። የአኔት አባት ይከተሉት እንደሆን ለማየት በፍርሃት ወደ ኋላው ተመለከተ፤ ማንም አልተከተለውም።



አሁን እሸለቆው ረባዳ ስፍራ ደርሷል። የሚቀጥለው ጉዞው በተራራዎች መካከል ወደአለው መተላለፊያ የሚያመራውን ዳገት መውጣት ነው። ያን ሲመለከት ለጊዜው ፍርሃት ተሰማው፤ የአኔት አባት ከኋላው ደርሰው እንዲይዙትም ተመኘ። ግን አሳቡን ከአእምሮው በመከላከል ጉዞውን በድፍረት ቀጠለ።

ሸለቆው መንገድ ላይ ያለው በረዶ አስቸጋሪ ስለአልሆነ፥ ሉሲየን የበረዶ መንሸራተቻውን ትከሻው ላይ አድርጎ በእግሩ ለመራመድ ይችላል። ወጨፎአማው በረዶም ጋብ አለ።

እንደገና ሌላ ጫካ ከፊቱ ገጠመው። ደክሞታል፤ ፍርሃትም ይሰማዋል። ጫካው በቂ ብርሃን የሌለው፤ ዛፎቹም ለየት ያሉ ናቸው። ሉሲየን አካባቢውን ስለማያውቀው ትክክለኛ የጉዞ አቅጣጫውን ስለ መጓዙ እንኳን እርግጠኛ አልሆነም። ካላወቀው፤ መንገዱ ወደ ገደል የሚያመራው ሊሆን ይችላል። የንፋሱ ፉጨትና የወንዞች ፉፉቴ ድምፅ ይሰማዋል፤ የበረዶው መንሸራተቻውም ይከብደው ጀመር።

የጫካው ውስጥ ዳገታማ መንገድ ሦስት ሰዓት አስጓዘው። በጉዞው ወቅት አዕምሮው ሊገጥሙት በሚችሉ ማናቸውም አስፈሪ ነገሮች ፍርሃት ተሞልቶ ነበር። ናዳና የበረዶ ጎርፍ ድንገት ከላይ ይመጣበት ይሆናል። የጠፉ ሰዎችን ስለሚፈልጉ ውሾች አስታወሰ። ጉዞው ካልተሳካለት ግን ወደ መጣበት መመለሱ አያቅተውም።

የመመለሱ አሳብ ቀደም ሲል ለምን እንዳልመጣለት እያሰበ ለጥቂት ጊዜ ቆም አለ። አስቦበት ቢሆን ኖሮ ቁልቁለቱን በበረዶ መንሸራተቻው ጋልቦ በአንድ አፍታ ቤቱ ይደርስ ነበር።

«የሚቻለኝን ባደርግም፥ ወደምፈልግበት ለመድረስ አልቻልኩም» ሊላቸው ይችል ነበር። የአኔት ቤተሰቦችም ይህን ጉዞ መሞከሩ እንኳ የጀግንነት ሥራ እንደሆነ ይገነዘቡ ነበር።

ነፋሱ በጣም ይነፍስ ጀመር። ዛፎቹ ቅርንጫፎቻቸውን እያወራጩ የሚያለቅሱ መሰሉ። ሉሲየን በዚህ ጫካውን አቋርጦ ተራራው ላይ ደረሰ። ያ ስፍራ በተራራዎች መካከል አለው መተላለፊያ አቅራቢያ ስለሆነ ኃይለኛው ንፋስ ምናልባት ገፍትሮ ወደ ገደል ይጥለው ይሆናል። ከቅዝቃዜው የተነሣ ጥርሶቹ ይንገጫገጩበት ጀመር።

«አሁንስ በጣም ፈራሁ። በዚህ ሁኔታ ውደ ፊት ለመሄድ አልችልም። ተራራዎቹ መተላለፊያ ላይ ስደርስ እንደምሞት አውቃለሁ። የአኔት አባት በደረሱልኝ» አለ።

እንዲህ እያለ እግሮቹን በረዶ መንሸራተቻው ዘለበት ውስጥ ሲያጠልቅ እነ አኔት ቤት ውስጥ ሞቃቱ ምድጃ ዳር ተቀምጦ ሴት አያቷ እንዲህ ሲሉ ስለ ፍርሃት የተናገሩትን ቃል አስታወሰ።

«ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል። ኢየሱስ እንደሚወደን በእርግጥ ካመንን፥ የሚያስፈራን ነገር አይኖርም። እርሱ ከወደደንም ምንም የሚጎዳን ነገር እንዲደርስብን አይፈቅድም።»

ብቻውን ያለመሆኑን ሉሲየን ተረዳ። ኢየሱስ እንደሚወደው የአኔት ሴት አያት ነግረውታል። ኢየሱስ እንዲያ የሚያፈቅር ከሆነ፥ የሚወደውን ልጅ ጨለማና አደጋ ውስጥ ብቻውን አይተወውም። ወዲያው ከምሽቱ፥ ከንፋሱ፥ ከፍርሃቱና ከጨለማው የሚበረታ አንድ ሰው መጥቶ እጁን በመያዝ «ጉዞህን ቀጥል» በሚል አኳኋን ወደ ተራራው ጫፍ ያሳየው መሰለው።

ጉዞውን ለመቀጠል ወሰነ።

«ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል፥» እያለ በተደጋጋሚ ለራሱ ተናገረ። እውነት ነው። ብቻውን እንዳልሆነ ስለ አመነ፥ ፍርሃቱ ተወው።

ጫካውን አቋርጦ ገላጣው ስፍራ ደረሰ። አሁን ጉዞውን ስለሚቀጥልበት ሁኔታ እንጂ ስለ ሌላ ነገር ለማሰብ አይችልም።

በጣም ዝግ እያለና እርምጃውን እየቆጠረ ተጓዘ። ቀዝቃዛው ንፋስ ፊት ፊቱን ስለሚገርፈው በጣም አጎንብሶ ነበር የሚራመደው። አንዳንድ ጊዜ የበረዶው ጥልቀት እስከ ጉልበቱ ቢደርስም፥ ጉዞው አልተገታም። አንድ የበረዶ ቋጥኝ ከላይ ተንከባልሎ መጣና ጣለው። ከወደቀበት ለመነሣት የማይችል መስሎት ፈርቶ ነበር። እንደ ምንም ታግሎ ተነሣ። በመጨረሻም መንገዱ ቀስ በቀስ ቁልቁለት መሆን ሲጀምር፥ በተራራዎች መካከል ያለውን መተላለፊያ ማቋረጡን ተረዳ።

ብዙም ሳይቆይ አንድ ጫካ ውስጥ ገባ፤ ንፋሱም ቀመለተ። ንፋሱ አደንዝዞታል። ቢሆንም አቅጣጫውን ባለመሳቱ እግዚአብሔርን አመሰገነ። እርሱ ነበር የሚመራው።



በበረዶ መንሸራተቻው አማካይነት በጫካው ውስጥ መንገድ ይሽሎከሎክ ጀመር። ተስፋ ሊያስቆርጠው የነበረ ቀዝቃዛ ንፋስ ስለ ቀመለተ ደስ ብሎታል።

በበረዶ መንሸራተቻው አማካይነት ቁልቁል ተፈተለከ። ወደ ሸለቆው በወረደ ቁጥር፥ በንፋሱ ይገፋ የነበረው ጫካም ጸጥ ይል ጀመር። በመጨረሻ ጫካውን አቋርጦ ወደ ገላጣው ስፍራ ወጣ። በረዶ የረጋበት ሜዳ በጨረቃይቱ ብርሃን ብርማ ሆኖ በጸጥታ ተዘርግቷል። ከዚያ በኋላ ነው ጨለማ እዋጠው ከተማ የሚደርሰው። ከግማሽ ሰዓት በኋላ እዚያ ደርሶ የትልቁን ሆቴል በር ያንኳኳል። ከዚያም. . .

«ኢየሱስ በእርግጥ የሚወደኝ ከሆነ፥ ይህን ሁሉ ልፋቴን ከንቱ አያደርገውም፥» አለ ለራሱ ሜዳውን አቋርጦ ወደ ከተማው እየተጓዘ።

# ምዕራፍ ሃያ ሁለት
# ሉሲየን ዶክተሩን አገኛቸው



ዶክተሩ በሌሊት ነው የነቁት። ወጨፎአማው በረዶ እንደ ቆመና ሸለቆው ጸጥ እንዲልላቸው ነው የመጀመሪያ አሳባቸው። ቀጥሎ ትዝ ያላቸው ዛሬ ወደ ቤታቸው የሚሄዱ መሆኑ ነው።

ወደ ቤታቸው የመመለሳቸው ነገር አስደስቶአቸዋል። ስለ አመማቸው ነው ነፋሻ አየር ለመፈለግና ለአንድ ሳምንት እረፍት ወደ ተራራማው አካባቢ የመጡት። ስለ ተሻላቸው ወደ ቤታቸው ተመልሰው ሥራቸውን ለመቀጠል ተዘጋጅተዋል። በመሆኑም ዛሬ ጠዋት በሚመጣው ባቡር በመሳፈር፣ ከእኩለ ቀን በፊት ሐይቁ ዳር አለው ቤታቸው ይደርሳሉ። ቤተሰቦቻቸው እንዴት ባለ ደስታ ይቀበሉአቸው!

የልጆቹ የደስታ ጫጫታ ታሰባቸውና ፈገግ አሉ። ሁለት ሴቶችና ሁለት ወንዶች ልጆች ናቸው ያሉአቸው። እናታቸውን በጣም በጣም ስለሚያስቸግሯቸው ልጆቹን በመጠበቅ የሚረዳቸው ሰው ቢያገኙላቸው ተመኙ።

ዶክተሩ ከመኝታቸው ተነሥተው እያፍዋጩ ፂማቸውን ተላጩ። መላጨታቸውን እንዳበቁ ነበር በሩ የተንኳኳው።

«ይግቡ፣» አሉ ዶክተሩ ያዘዙት ቁርስ በዚያ ፍጥነት መድረሱ እያስገረማቸው። ገና ከማለዳው አሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ነው። በሩ ተከፈተና የሌሊቱ ዘበኛ ገባ። ምሥጢራዊ ዜና የያዘ ይመስል።



«ይቅርታ፣ ጌታዬ፣ ይመጣል ብለው የሚያስቡት ሰው አለ እንዴ?» አለ እራሱን አከክ እያደረገ።

«የምጠብቀው ሰው? በዚህ ሰዓትና የአየር ሁኔታ? በፍጹም ሰው ይመጣል ብዬ አላሰብኩም፣» አሉ ዶክተሩ ከዘበኛው ይበልጥ እየተደነቁ።

«ነገሩ እንዲህ ነው። ከአርባ አምስት ደቂቃ በፊት በሩ በቀስታ ሲንኳኳ ሰምቼ ብከፍት በበረዶ መንሸራተቻው ላይ የቆመ አንድ ልጅ አየሁ። ዕድሜው አሥራ ሁለት ዓመት ቢሆን ነው። እንደ ጥጥ ነጥቷል፤ እንዳች ጣረሞት እንጂ፣ ሕይወት ያለው ልጅ አይመስልም። «ዶክተሩን ነው የምፈልገው» አለ። እንደምን አደርክ እንኳን አላለኝም። ከዚያም ደረጃው ላይ ቁጭ ብሎ እራሱን በሩ ላይ አስደገፈው።

«በዚህ ማለዳ ሰው ፍለጋ መምጣት አይፈቀድልህም። ዶክተሩ ተኝተዋል አልኩት። «እስኪነሡ እጠብቃለሁ» አለና እራሱን ጉልበቶቹ ውስጥ ቀበረ።

«ልጅ እንዲያ ሲሆን ማየቱ ደስ ስለማይለኝ፣ የበረዶ መንሸራተቻውን ተቀብዬ ወደ ውስጥ አስገባሁና ወንበር ላይ እንዲቀመጥ አደረግኩ። ከዚያም «ከየት ነው የመጣኸው?» ብዬ ጠየቅኩት። ‹ፕሬ ዶአሬ ከሚባል ስፍራ፣ አለ። ‹የማለዳው ባቡር ገና አልደረሰም፣ እንዴት መጣህ› አልኩት።

‹በተራራዎቹ መተላለፊያ በኩል ነው የመጣሁት› አለ። ጌታዬ የልጁን ሁኔታ ትኩር ብዬ ባየሁ መጠን አምነው ጀመር። አሁን አዳራሹ ውስጥ ተቀምጧል። በበርዎ ሳልፍ የክፍልዎ መብራት በርቶ ስለ አየሁ፣ ልጁን ሊያነጋግሩት ፈቃድዎ መሆን አለመሆኑን ልጠይቅ ብዬ ነው።»

«መጥቼ አነጋግረዋለሁ። የተራራዎቹን መተላለፊያ አቋርጦ መጣ የሚለውን ታሪክ ግን ላምን አልችልም። የተራራ አስጎብኚዎች እንኳን በትናንቱ ምሽት ያን ስፍራ ያቋርጡታል ብዬ አላምንም። ያ ስፍራ እጅግ አስቸጋሪ መሆን አለበት፣» አሉ ዶክተሩ።

በዘበኛው መሪነት አዳራሹ ውስጥ ሲገቡ፣ ሁለቱም ባዩት ነገር ተደናግጠው ወደፊት እሮጡ።

ሉሲየን ከነበረበት ወንበር ላይ ተንሸራትቶ በመውደቅ ሕሊናውን ስቶ ወለሉ ላይ ተዘርሯል። ፊቱ በጣም ገርጥቷል።

ዶክተሩ አቅፈው አነሡትና፥ «ወደ ክፍሌ እወስደዋለሁ። አንተ ደግሞ ሙቅ ውኃ በጠርሙስ፥ ብራንዲና ቡና አምጣልኝ። በጣም ፍጠን፥» አሉ።

ዶክተሩ ሉሲየንን ወደ ክፍላቸው ወስደው አልጋ ላይ አጋደሙት። ከዚያም ጫማና የእግር ሹራቡን አውልቀውለት የደነዘዘ እግሩን አሹት። እርጥብ ልብሶቹን አውልቀው በብርድ ልብስ ጠቀለሉት። በዚህ ጊዜ ዘበኛው በሰፊው እየተነፈሰ መጣ። ሙቅ ውኃ በጠርሙስ፥ ብራንዲና ትኩስ ቡና ይዟል።

ዶክተሩ ዘበኛው ያመጣቸውን ነገሮች ከተቀበሉ በኋላ፥ ከብራንዲው በማንኪያ ቀድተው ወደ ሉሲየን የደረቁ ከንፈሮች አቀረቡ። ሉሲየን ዓይኖቹን እንደ ከደነ በድካም ተነፈሰና ብራንዲውን ዋጠው።

«በጣም ጥሩ! አሁን በደንብ ትነቃለህ፥» አሉ ዶክተሩ።

ሉሲየን ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ነቅቶ ዐይኖቹን ሲከፍት የተመለከተው፥ ደግነት የሚታዩበት ፊት ነው። ያለበትን ለማስታወስ አልቻለም። ቢሆንም ሞቆታል፥ ተመችቶታል፥ እንቅልፍ ተጫጭኖታል። ዕድሜ ልኩን ከዚያ ባይንቀሳቀስ ደስ ይለው ነበር። ያ ፊት ለፊቱ ቆሞ በቅንነት የሚመለከተውን ሰውዬ ማን መሆኑን ለማወቅ ፈለገና፥

«እርስዎ ማን ነዎት?» አለ።

ዶክተሩ ለሉሲየን ጥያቄ ቶሎ መልስ አልሰጡም። ሉሲየንን ቀና አድርገው ትኩሱን ቡና አጠጡት። በዚያ ሁኔታው መዋጡ ያስቸግረው ስለ ነበር ቀስ እያለ ነው ሉሲየን ቡናውን የሚጠጣው። ቡናውን እንደ ጨረሰ፦

«እርስዎ ማን ነዎት? የት ነው ያለሁት?» አለ።

«ዶክተር ጊቬት እባላለሁ። እኔ አላውቅህም። የፈለግኸኝ መሆንህን ግን ተረድቻለሁ፥» አሉ ዶክተሩ።

ሉሲየን ዶክተሩን ትኩር ብሎ ተመለከታቸው። ወደዚያ የሄደበትን ምክንያት እስኪረሳ ድረስ በጣም ደክሞት ነበር። በኋላ ግን ያገኘው ሙቀትና ምግብ ረድቶት አእምሮው በትክክል ስለ ሠራለት፥

«ታላቁ፥ ኀበዙና ዝነኛው ዶክተር እርስዎ ነዎት?» አለ።



«ያልከውን ሁሉ ሳልሆን ዶክተር ብቻ ነኝ።»

«ሽባ ሕፃናት እንዲራመዱ ለማድረግ ይችላሉ?»

«ለመራመድ መቻላቸው ለሕመማቸው ምክንያት እንደሆነው ነገር መክበድና መቅለል ይለያያል። አዎ፥ አንዳንዴ ሽባዎች ድነው እንዲራመዱ ለማድረግ እችላለሁ።»

«ከገደል ላይ በመውደቁ ነው ሽባ የሆነው። ክራንች ተመርኩዞና ትልቅ ጫማ አድርጎ ነው የሚራመደው።»

«ማን ነው እርሱ፥ እንዲህ የሆነው?» አሉ ዶክተሩ።

«ትንሹ ዳኒ ይባላል። ስድስት ዓመቱ ነው፤ ጎረቤቴ ነው። ለዚህ ነው ያድኑት እንደሆን ልጠይቅዎት የመጣሁት። የምከፍልዎት ብዙ ገንዘብ አለኝ።»

«ማን ነው ስለ እኔ የነገረህ?»

«እኅቴ ናት ትላንት ማታ የነገረችኝ። እዚህ ሆቴል ውስጥ አስተናጋጅ ናት።»

«እንዲህ ባለው መጥፎ የአየር ሁኔታ ውስጥ እንዴት ወዲህ መጣህ?»

«በበረዶ መንሸራተቻዬ አማካይነት በተራራዎቹ መካከል ያለውን መተላለፊያ አቋርጬ ነው።»

«እንደዚያ ልታደርግማ አትችልም። ያውም በወጨፎአማው በረዶ ውስጥ።»

«ሌላ የመምጫ መንገድ ስለሌለ በዚያው ነው የመጣሁት።»

እውነት ነው፥ ሌላ መንገድ አልነበረም። ዶክተሩ ቁጭ ብለው ሉሲየንን ይመለከቱት ጀመር። ከሌላ ዓለም የመጣ ሰው መሰላቸው። ዶክተሩ እንዲህ ሲመለከቱት ሳለ፥ ሉሲየን እጁን ወደ ሸሚዙ ውስጥ በመላክ ገንዘብ ያለበትን የእግር ሹራብ አውጥቶ ወደ ዶክተሩ እየዘረጋ «ዶክተር፥ ዳኒን ለማከሚያ ይህ ገንዘብ ይበቃል?» አለ።

ዶክተሩ እግር ሹራቡ ውስጥ የነበረውን ገንዘብ አውጥተው ከተመለከቱና የድንጋጤ ዓይነት ድምፅ ካሰሙ በኋላ፥

«ምንም ማድረግ ከመጀመራችን በፊት ይህን ገንዘብ ከየት እንዳመጣኸው ልትነግረኝ ይገባል። ስንት እንደሆነ ታውቃለህ?» አሉ ዝግና ጠንከር ባለ አነጋገር።

«ስንት እንደሆነ አላውቅም። እኅቴ ግን እርስዎ ብዙ ገንዘብ እንደሚጠይቁ ነግራኛለች። አይበቃም?»

«ክሊኒኬን እንዳለ ለመግዛት ካልፈለግክ በስተቀር፥ ለሕክምና ከበቂ በላይ ነው። ከየት ነው ያመጣኸው?»

«ጓደኛዬ የሆኑ አንድ ሽማግሌ ናቸው የሰጡኝ። መልእክትም ልከውኛል። የብድር ክፍያ ስለሆነ ሁሉንም ውሰዱት ብሎዎታል» አለ ሉሲየን ዐይኖቹን እንደገና እየጨፈነ።

«ማን ነው ሽማግሌው? ይህን ብቻ ንገረኝና ታንቀላፋለህ። ማን ይባላል?» አሉ ዶክተሩ።

«ስማቸውን አላውቀውም፥ እባክዎ ዶክተር።»

«የት ነው የሚኖረው?»

«መኖሪያቸውን እንዳልነግርዎት ቃል አስገብተውኛል፥» ብሎ እራሱን ወደ ጎን ዘንበል አደረገና አንቀላፋ።

ዶክተሩ ግራ ተጋቡ። የሚጓዙበት ባቡር ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይንቀሳቀሳል። ይህ አሁን የተኛው ልጅ ደግሞ እዚያ የደረሰው ሕይወቱን ለአደጋ አጋልጦ ነው። የሚደረገው ነገር ሁሉ የሚያስገኘው ጥቅም አይኖር ይሆናል። ቢሆንም ሽባ የሆነውን ሕፃን አላክምም ብለው ጠንካራውን ልጅ ሉሲየንን ሊያሳዝኑት አይገባም። ሉሲየን ግን ለረጅም ሰዓት የሚያንቀላፋ ይመስላል።

ዶክተሩ ቀስ ብለው ከክፍሉ ወጡና ለሚስታቸው ስልክ ደወሉ።

«እንደምን ነሽ ማርታ? እስከ ነገ እዚሁ መቆየቴ ነው። አንድ የሚገርም ሁኔታ ገጥሞኛል...» እያሉ ስለ ሉሲየን ነገሯቸው።

ከስልክ መደወያው ቢሮ ሲወጡ ከአንዲት ወጣት ጋር ሊጋጩ ነበር። ዐይኖቿ ቀልተው ፊቷ ገርጥቷል። በመጣጠን አኳኋን እጃቸውን ያዝ አደረገችና፥

«ትንሹን ወንድሜን ክፍልዎ ውስጥ በደህና ያስተኙት መሆኑን ዘበኛው ነገረኝ። ጎርፍ የወሰደው መስሎን እኔና እናቴ በጣም ደንግጠን



ነበር። በፍጥነት ወደ ቤት ሄጄ ሉሲየን እዚህ መኖሩን ለእናቴ መንገር አለብኝ» አለች።

ዶክተሩ አብረዋት ቁጭ ብለው አንዳንድ ማብራሪያዎችን እንድትሰጣቸው ይጠይቋት ጀመር። እናቷና እርሷ ስለ አሳለፉት አስጨናቂ ሌሊት ከመግለጽ ያለፈ ዝርዝር ነገር ልትነግራቸው አልቻለችም።

የአኔት አባት ሌሊቱን በሙሉ ሉሲየንን ሲፈልጉ አድረው ምንም ሳይዙ ነው የተመለሱት።

ማሪዬ ስለ ዳኒ ለዶክተሩ የነገረቻቸው በጣም ትንሽ ነው። ከሥራዋ በጣም ብትዘገይም፥ ሉሲየን በሕይወት መኖሩን ስለአወቀች ወደ ቤት ልትወስደው ቸኩላለች። ወደ ፖስታ ቤቱ ኃላፊ ብትደውል፥ የሉሲየንን በደህና መገኘት ዜና ለእናቷ የሚያደርስ አንድ ልጅ ወደዚያ ሊልክላት ይችላል።

ዶክተሩ ሉሲየን አሁኑኑ ወደ ቤቱ እንዲመለስ አልፈለጉም። ማሪዬ ብቻዋን ወደ ቤቷ ትሄድና፥ ሉሲየን በነቃ ጊዜ ዶክተሩ በባቡር አሳፍረው ይወስዱታል። ስለዚህ ማሪዬ ባቡር ጣቢያው ድረስ ጋሪ የሚያመጣለት ሰው መፈለግ አለባት። በቅዝቃዜው ምክንያት ምናልባት የሉሲየን ሰውነት አይታዘዝለት ይሆናል።

ማሪዬ በአሳቧ ጸንታ በፍጥነት ስትወጣ፥ ዶክተሩ ወደ ክፍላቸው ሄዱ። ሉሲየን እንደ ቀድሞው እጁን እንደ ተንተራሰ ተኝቷል። ቢሆንም ከቀድሞው ይልቅ የተሻለው መሆኑ ትንሽ ፈገግ ካለው ፊቱ ይታወቃል። ዶክተሩ ሉሲየን አጠገብ ቁጭ ብለው፥ ልጁ ያን ሁሉ ገንዘብ እንዴት አገኘው? የሚለውን አሳብ ያሰላስሉ ጀመር። እንዲህ ያለውን ያልተለመደ መልእክት የላከ ሽማግሌ ማን ነው?

«የብድር ክፍያ!» የሚለውን መልእክት በጥልቀት ለመመርመር ወሰኑ።

እኩለ ቀን ላይ ነው ሉሲየን ከእንቅልፉ የነቃው። የነበረበትን ቦታ ማስታወስ አቅቶት እንደገና ለረጅም ጊዜ ቆየ። ሁለመናውን ሕመም ስለሚሰማው ለመንቀሳቀስ አልፈለገም። ዶክተሩ ትንሽ እንቅስቃሴ ስለ ሰሙ ጠጋ ብለው አዩትና፥

«እሺ፥ እንዴት ነህ?» አሉት።

«ደህና ነኝ፥ በጣም አመሰግናለሁ፥» አለ ሉሲየን።

አንቀላፍቶ እንደ ነበር እያስታወሰ። ቀጠል አደረገና ደግሞ፥ «እባክዎ፥ የነገርኩዎትን ልጅ ለመጎብኘት ጊዜ ይኖርዎታል?» አለ።

«አዎ፥ ይኖረኛል፥» አሉ ዶክተሩ ሉሲየን አጠገብ እየተቀመጡ፥ «ከምሳ በኋላ እንሄዳለን። ምሳችንን እዚሁ እንዲያመጡልን ለሆቴሉ ሠራተኞች እነግራቸዋለሁ። ምሳችንን እየተመገብን ስለ ትንሹ ልጅና ገንዘቡን ላከ ስለ አልከው ሽማግሌ ትነግረኛለህ።»

«ስለ ሽማግሌው ልነግርዎ አልችልም። ምክንያቱም ላለመናገር ቃል ገብቼላቸዋለሁ። ምሥጢራዊ ሰው ናቸው፤ ከእኔ ሌላ የሚጎበኛቸው የለም። ገንዘቡ የብድር ክፍያ መሆኑን እንድነግርዎ ብቻ ነው ያዘዙኝ። ብዙ ውለታ ስለ ዋሉልኝ የገባሁላቸውን ቃል ልጥሰው አልፈልግም።»

«መልካም፤ ቃልህን መጣስ የለብህም። ሁለተኛ ስለ ሽማግሌው አልጠይቅህም። ስለ ትንሹ ሽባ ልጅ ግን ንገረኝ፥ መቼና እንዴት ነው አደጋው የደረሰበት?»

በዚህ ጊዜ የሉሲየን ፊት በጣም ሲቀላ ዶክተሩ ተመለከቱ። ለጥያቄው መልስ ሳይሰጥ ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ። ታሪኩን ለአዲሱ ጓደኛው ሊነግራቸው አልፈለገም ነበር። ነገር ግን ዶክተሩ ከዳኒ ቤተሰቦች መስማታቸው ስለማይቀር፥ መጀመሪያ ልንገራቸው ብሎ፥ «በእኔ ጥፋት ነው ልጁ አደጋ የደረሰበት። ባለፈው ፀደይ ነው ይህ የሆነው። ለቀልድ ያህል ድመቱን ወደ ገደል የጣልኩበት በማስመሰል ሳስፈራራው፥ እውነትም ድመቷ ከእጄ አምልጣ ወደ ገደሉ ወደቀች። ያን ጊዜ ዳኒ ድመቱን ለማውጣት ሲሞክር ወደቀና እግሩ ተጎዳ። ከዚያ ወዲህ ቀጥ ብሎ ለመራመድ አይችልም። ቢሞክርም በክራንች ብቻ ነው። ለዚህ ነው ምናልባት...» እያለ ሲናገር ከንፈሮቹ ተንቀጠቀጡበት፤ ድምፁም ወደ ሹክሹክታ ተለወጠ። ቢሆንም ማለት የሚገባውን ተናግሯል። ዶክተሩ የሕፃናትን ሁኔታ የሚረዱና የሚወዱቸውም ስለሆኑ፥ በእነዚያ በተሰባበሩና ጥቂት ቃላት አማካይነት ታሪኩን በሙሉ ተረዱ። አጠገባቸው የተኛው ይህ ትንሽ ልጅ በፈጸመው ጥፋት በጣም በመቀጣት ላይ መሆኑንም ተገነዘቡ።

«ልጁን አብረን እንሄድና እናየዋለን፥ ሉሲየን። ምናልባት እግዚአብሔር የልጁ መፈወሻ መንገድ ያደርግህ ይሆናል። አየህ ሉሲየን፥ እግዚአብሔርን ልታመሰግንበት የሚገባህ ብዙ ነገር አለ።



ትናንት ሌሊት በጣም በተለየ ሁኔታ ይጠብቅህ እንደነበር እገምታለሁ። እንዲያ ባይሆን ኖሮ በተራራዎቹ መካከል ያለውን መተላለፊያ አቋርጠህ በሕይወት ልትመጣ አትችልም ነበር።

«አዎ፥ አውቃለሁ። አዩ ዶክተር፥ እግዚአብሔር ዳኒን እንዲያድነው የጸለይኩት ገና ትናንት ነው። ስለ እርስዎ ስሰማ ጸሎቴ ተሰማ ብዬ አሰብኩ። በጉዞዬ ላይ ጫካው ውስጥ ስገባ ግን ፈርቼ ወደ ቤቴ ልመለስ ነበር። ነገር ግን አንድ ቀን የገና ዕለት የሰማሁት ነገር ትዝ አለኝና ጉዞዬን ለመቀጠል ወሰንኩ።»

«ምንድን ነው ትዝ ያለህ?» አሉ ዶክተሩ ዝግ ባለ አነጋገር።


«የዳኒ ሴት አያት ያነበቡልን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ነበሩ ትዝ ያሉኝ። ሁሉንም አላስታውስም፥ ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን ያስወግዳል የሚለው ቃል ግን ትዝ ይለኛል። የኢየሱስ ፍቅር ፍጹም መሆኑን የዳኒ ሴት አያት ነገሩኝ። ስለዚህ ሳልፈራ ጉዞዬን ቀጠልኩ። ስለ ጉዞዬ ብዙ ባላስታውስም፥ በደህና እዚህ ደርሻለሁ።»

«አዎ፥ ሌላ ሳይሆን የኢየሱስ ፍቅር ብቻ ነው ከዚያ አስከፊ የበረዶ ማዕበል የከለለህ፥ በትክክለኛው አቅጣጫ የመራህና ጉዞህን እንዳትቀጥል ከሚያደርግ ከባድ ፍርሃት የጠበቀህ እርሱ ነው። ጌታ በጣም መልካም ነገር ነው ያደረገልህ፥ ሉሲየን። ምሳችን ከመምጣቱ በፊት እግዚአብሔርን እናመስግነው።»

ሉሲየን ለጸሎት ፊቱን ትራሱ ውስጥ ቀበረ። ዶክተሩ ደግሞ አልጋው አጠገብ ተንበረከኩና ጸለዩ። ከአውሎ ንፋሱ ወይም ከማዕበል በላይ ስለሆነው ፍጹም ፍቅሩ እግዚአብሔርን አመሰገኑ። ያ ፍቅር ነው በጨለማው ውስጥ የሉሲየንን እርምጃ የጠበቀ፥ እንዲሁም ከሞትና ከፍርሃት ያዳነው። ከዚያ በኋላ ለትንሹ ዳኒ ጸለዩለት። የልጁን ሽባ እግር ለማዳን የሚያስችል ጥበብ እንዲሰጣቸውም ጸለዩ።

ሉሲየንም ድምፁ አይሰማ እንጂ በነበረበት ሆኖ እንዲህ በማለት ጸለየ፡- «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ በተራራዎች ላይ ስጓዝ እጎኔ ስለ ነበርክ አልፈራሁም። እባክህ ትተኸኝ አትሂድ፤ እንደ አኔት እኔም የልቤን በር ልከፍትልህ እፈልጋለሁ። እባክህ ግባ።»

# ምዕራፍ ሃያ ሦስት
## ዳኒ ከዶክተሩ ጋር ተገናኘ



የዳኒ አባት የራሳቸውን ጋሪ ይዘው በመምጣት ዶክተሩንና ሉሲየንን ወደ ቤታቸው ይዘዋቸው ሄዱ። የሆነው ነገር በአካባቢው ስለ ተሰማ፥ የመንደሪቱ ሰዎች ዝነኛው ዶክተር ሲያልፉ ለማየት በየበራቸው ላይ ቆመው ነበር። ሰው ሁሉ የሚያወራው ስለ ሉሲየን ነበር። በተራራዎቹ መካከል ያለውን አስቸጋሪ መተላለፊያ በማቋረጡ እንደ ታላቅ ጀግና ቆጥረውታል።

የዳኒ አባት ስለ ገጠማቸው ሁኔታ ምን እንደሚያስቡ ቸግሮአቸው ዝም ብለው ጋሪው ላይ ተቀምጠዋል። እርሳቸውን የመሰለ ዝነኛ ሰው በጋሪ ማጓጓዙ ከባድ ኃላፊነት አለበት። ሁልጊዜ እንደሚሆነው ጋሪው መንገዱን ስቶ እንደማይገለበጥ ተስፋ ያደርጉ ነበር የዳኒ አባት።

ለዶክተሩ ስለሚከፈለው ገንዘብም ያስቡ ነበር። ዳኒ ተፈውሶ ለማየት ግን ያላቸውን ሁሉ ከመስጠት አይቆጠቡም። ነገር ግን ብዙ ገንዘብ አልነበራቸውም፤ ለዶክተሩ ክፍያ ካልበቃስ? ምናልባት ዶክተሩ በገንዘብ ፈንታ አንድ ኮርማ በሬ ይቀበሉ ይሆናል።

ያለምንም ችግር ነው እነዳኒ ቤት የደረሱት። የዳኒ አባት ዶክተሩ ከጋሪው ላይ እንዲወርዱ ከረዱቸው በኋላ፥ መለስ ብለው በጠንካራ እጆቻቸው ሉሲየንን ብድግ አድርገው በመሸከም የፎቁን ደረጃዎች አውጥተው ፊት ለፊት አለው ክፍል ውስጥ በሚገኘው ምንጣፍ ላይ



አስተኙት። ሉሲየን በደህና በመገኘቱ እርሱም ደስ ብሎታል። ሌሊቱን ሙሉ በወጨፎአማው አየር ውስጥ እየተንገላቱ ሲፈልጉት ነበር ያደሩት።

የዳኒ ሴት አያት፥ አኔትና ዳኒ ፎቶግራፍ ለመነሣት የተዘጋጁ ይመስላሉ። የክት ልብሶቻቸውን እየለበሱ ሻል ባሉ ወንበሮች ላይ ተቀምጠዋል። ዝነኛውን ሰውዬ በመጠበቅ ለረጅም ጊዜ የተቀመጡ ይመስላሉ። ዶክተሩ ሲገቡ አኔትና ዳኒ ሴት አያታቸውን አየት አደረጉና በትሕትና ብድግ አሉ።

ዳኒ ዶክተሩ በተረት ውስጥ የሰማው ዝነኛ ሰውዬ የለበሰው ዓይነት ቀይ ልብስ ይለብሳሉ ብሎ ጠብቆ ነበር። እንደዚህ ስለአልሆነለት ቅር አለው። አባቱን ተከትለው የመጡት እኚህ እንግዳ ከሌሎች የተለዩ አልነበሩም።

ዶክተሩ ራቅ ብለው ተቀመጡና እያዩዋቸው ፈገግ አሉ። ፈገግታቸው ደስ ስለሚል ዳኒ ቅሬታውን እረሳና አጸፋውን መለሰላቸው።

«ከረሜላ ትወዳለህ፥ ዳኒ?» አሉ ዶክተሩ ከኪሳቸው ያወጡትን ጣፋጭ ወደ ልጁ እየዘረጉ። ዳኒ ፈገግ ብሎ እራሱን በደስታ ነቀነቀ።

«ናና ውሰድ፥» አሉ ዶክተሩ። ዳኒ ከክፍሉ አቋርጦ ወደ እርሳቸው ሲመጣ ዶክተሩ እንቅስቃሴውን በጥንቃቄ ተመለከቱ። አጠገባቸው ሲደርስ፥ አቅፈው ጉልበታቸው ላይ አስቀመጡትና ከረሜላውን አጎረሱት።

ዶክተሩ ያን ቤተሰብ ወድደውታል። በተለይ ሳቂታውን፥ ተግባቢውንና ባለ ሰማያዊ ብሉኑን ዳኒን አፈቀሩት። ዶክተሩ ጉልበት ላይ ተቀምጦ እየሳቀ ከረሜላውን ይመጥጣል። የዳኒ እናት የምትሆን ሴት አለመኖሯን ዶክተሩ ገምተው ቤቱን እንዲያ በንጽሕናና በሥርዓት የያዘችው አሮጊቷ ወይስ አኔት ናት? በማለት አሰቡ።

«እግርህን ያምሃል?» አሉ ዶክተሩ ዳኒን እያዩ።

«አያመኝም፥» አለ ዳኒ።

«ኧረ ያመዋል፥ ዶክተር፥» ሲሉ የዳኒ ሴት አያት የዳኒን ስሕተት አረሙ።

«አንዳንድ ጊዜ ክራንቼን ሳልይዝ ስራመድ ብቻ ነው የሚያመኝ። ክራንቾቼ የድብ እራስ ቅርጽ አለባቸው። ላሳይዎት? አለ ዳኒ ዶክተሩን እያየ።

«አዎ፥ አሳየኝ፥» አሉ ዶክተሩ። ዳኒ ክራንቾቹን ሊያመጣ ሲሄድ እንደገና ትኩር ብለው አዩት።

«ክራንቼን ስይዝ በትልቁ ልራመድ እችላለሁ፤ ላሳይዎት?» አለ ዳኒ።

«አዎ፥ አሳየኝ፥» አሉ ዶክተሩ እንደገና።

«ወንበሮቹ እንዳይገጩህ ተጠንቀቅ፥ ዳኒ» አሉ ሴት አያቱ ፈጠን ብለው። ቤት ውስጥ በጣም እንዳይዘል ሁልጊዜ ይከታተሉታል። አኔት ብድግ ብላ ሁለቱን የድመት ግልገሎች ከነበሩበት አነሣቻቸው። ዳኒ ክራንቹን ይዞ በረጅሙ መወርወር ከጀመረ እላያቸው ላይ ያርፍ ይሆናል ብላ ስለ ፈራች ነው፥ ድመቶቹን ያነሣቻቸው።

«በጣም ጥሩ! እንደ ካንጋሮ ነው የዘለልከው!» አሉ ዶክተሩ ዳኒ እንደ ተናገረው በረጅሙ ስለ ዘለለ በአድናቆት እያጨበጨቡለት። ቀጠል አደረጉና፥ «አሁን ደግሞ ክራንቾችህን አስቀምጥና ወደ እኔ ተራመድ» አሉ።

ዳኒ ፈገግ እያለና እያነከሰ ወደ ዶክተሩ ተጠጋ። ፈገግ ይበል እንጂ ሽባ እግሩን እየጎተተ ሲሄድ ሕመሙ በጣም ይሰማው ነበር። ዶክተሩ ፈገግ እያሉ ዳኒን አንሥተው ጉልበታቸው ላይ በማስቀመጥ ሌላ ከረሜላ ሰጡት።

የእነ ዳኒ ሴት አያት የሚደረገውን ነገር ሁሉ በጥንቃቄ ሲመለከቱ ቆይተው ወደ አኔት ዘወር አሉና፥

«አኔት፥ ሻይ አፍዪና ከብስኩት ጋር አቅርቢ፥» አሉ። አኔት ሻይ እስከታፈላ ድረስ ዶክተሩ ዳኒን ጠረጴዛ ላይ አስተኝተው እግሩን እጥፍ ዘርጋ፥ ጠምዘዝ እያደረጉ ለረጅም ጊዜ መረመሩት። ሻዩ ከፈላ በኋላ ቁጭ ብለው ከእነርሱ ጋር እንዲጠጡ አሮጊቷ እስኪጠይቋቸው ድረስ ይመረምሩት ነበር። በጣም የሚያሰላስሉ ይመስላል።

«እሺ፥ ልታደርግለት የምትችለው ነገር አለ?» አሉ የዳኒ ሴት አያት በመጨረሻ ዶክተሩን እያዩ።



ቤቱ ውስጥ ያሉት ሁሉ ለጥያቄው የሚሰጠውን መልስ ለመስማት በመጓጓት ወደ ዶክተሩ አፈጠጡ፤ ከዳኒ በቀር። ወደ ብስኩቶቹ ነበር እርሱ የሚመለከተው። ስለረሱት አልሰጡትም። ብድግ ብሎ ቢወስድ ደግሞ ሴት አያቱ ይቆጡታል። ብስኩቶቹ ሲታዩ ደስ የሚሉና ሲበሉ የሚጣፍጡ ናቸው። ሴት አያቱ ናቸው ጥሩ አድርገው በወር አንድ ጊዜ የሚጋግሯቸው።

ዶክተሩ ለሴቲቱ ጥያቄ ወዲያውኑ መልስ አልሰጡም። ወደ ዳኒ ዘወር ብለው፥ «ዳኒ፥ እንደ ሌሎቹ ትንንሽ ልጆች ለመሮጥ ብትችል ደስ ይልሃል?» አሉ።

ዳኒ አመነታ። ስለ መፈለጉ እርግጠኛ አልነበረም። ከመንደሩ ልጆች ሁሉ የድብ ቅርጽ ያለበት ክራንች ያለው እርሱ ብቻ በመሆኑ፥ የተለየ ሰው አድርጎታል። ወዲያው አንድ ነገር ትዝ አለው። የፀደይ ወቅት በመቃረብ ላይ ነው። እንደ ልቡ ለመሮጥ ካልቻለ፥ ባለፈው ዓመት እንዳደረገው ሜዳው ላይ የፍየል ግልገሎችን እያባረረ ሊጫወት አይችልም። በጣም ደስ የሚል ጫወታ ነው። ይህን አስቦ፥ «አዎ፥ እፈልጋለሁ» ካለ በኋላ ወደ ሴት አያቱ ዘወር ብሎ፥ «እባክሽ ብስኩት ስጪኝ» አለ።

ለኋለኛው ጥያቄ መልስ የሰጠው የለም። ሉሲየንና አኔት የሻይ ኩባያዎቻቸውን እንደያዙ ዐይኖቻቸውን ወደፊት ቡዝዝ አድርገዋል። ሁሉም የዶክተሩን መልስ በመጠባበቅ ላይ ናቸው።

«ያቺ ቆንጆ ድመት ወዴት ሄደች፥ ዳኒ?» አሉ ዶክተሩ በድንገት።

«ወደ እንጨት ማከማቻው ሄዳለች። ሊያዩዋት ይፈልጋሉ? ሦስት ግልገሎች አሏት፥» አለ ዳኒ።

«አዎ፥ ባያት ደስ ይለኛል፥» አሉ ዶክተሩ። ዳኒ ብድግ ብሎ ድመቲቱን ሊያመጣ ሄደ። እግረ መንገዱን ከጠረጴዛው ላይ ሁለት ብስኩቶች አነሣ። ልብ ብሎ ያየው ሰው አልነበረም።

ዳኒ ከቤት ወጥቶ በሩ ከኋላው እንደ ተዘጋ፥ ዶክተሩ ወደ ዳኒ አባት ዘወር አሉና።

«በራጅ ተመርምሮ ውጤቱን ባላየውና በእርግጠኛነት ባልናገርም፤ ልረዳህ የምችል ይመስለኛል። አጥንቱ ትክክለኛው ቦታ ላይ ያለ አይመስለኝም። አለአግባብ የተገጣጠመ ይመስላል። እንዲያ ከሆነ፥ እንደገና የቀዶ ጥገና ሕክምና (ኦፕራሲዮን) አድርጌና አሳስቤ

ላስተካክለው እችላለሁ። ኦፕራሲዮን ይሁን ስል ሆስፒታል ውስጥ ለረጅም ጊዜ መቆየት ያስፈልገዋል ማለቴ ነው። ወደ ሆስፒታል እንዲሄድ ትፈቅዳለህ?» አሉ።

የዳኒ አባት በጭንቀት እጆቻቸውን አሻሹና መጀመሪያ የኤኔትን ሴት አያት ከዚያም ኤኔትን አዩዋቸው። ስለ ኦፕራሲዮኑ ምንም ስለማያውቁ ቃሉ አስፈራቸው። በሌላም በኩል ኦፕራሲዮኑ ያለበት ሕክምና ዋጋ በጣም ውድ እንደሚሆን ሰምተዋል። ያን ያህል ገንዘብ ለመክፈል አይችሉም።

«የሕክምናው ዋጋ ምን ያህል ይሆናል?» አሉ እራሳቸውን እያከኩ።

«ምንም አትከፍልም። አስፈላጊውን ገንዘብ ሉሲየን ከፍሏል። ገንዘቡን ከየት አመጣው? ለሚለው ጥያቄ አሁን መልስ ልሰጥ አልችልም። ዳኒ አሁን ይመጣል! ከመመለሱ በፊት መወሰን አለብን። ወደ ሆስፒታል እንድወስደው ትፈቅድልኛለህ?» አሉ ዶክተሩ።

«አዎ፥» አሉ የኤኔት ሴት አያት፥ ሳይጠየቁ።

«መቼ?» አለች ኤኔት።

«ነገ ጠዋት፥ በመጀመሪያው ባቡር ስለምሳፈር፥ ዳኒን ይዤው እሄዳለሁ፥» አሉ ዶክተሩ።

«ወዴት ነው በባቡሩ የሚሄደው?» አለ አንድ ድምፅ፥ ዳኒ ማንም ሳያየው ድምፁን አጥፍቶ በኋላው በር ገብቷል። የድመት ግልገሎች አቅፎ ፈገግ እያለ ዶክተሩ አጠገብ ቆመ።

በሕይወት ዘመኑ በባቡር የተጓዘው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ያውም ለአሥር ደቂቃ። ቢሆንም ጉዞውን ሁልጊዜ ያስታውሰዋል።

ለዳኒ ጥያቄ ማንም መልስ አልሰጠም። ሁሉም ዶክተሩ ላይ አፍጥጠዋል።

«ወዴት ነው የምሄደው አያቴ?» አለ ዳኒ።

ዶክተሩ ወደ እርሱ ዞወር አሉና፥

«ዳኒ አብረኸኝ ወደ ሐይቁ ዳርቻ ትሄድና ከእኔ ጋር ትንሽ ትቆያለህ። እግርህን ከአሁኑ የተሻለ አድርጌ ላክምህ ተስፋ አደርጋለሁ። እንዲያ እንዲደረግልህ ትወዳለህ?» አሉት።

ዳኒ በቀረበለት ጥያቄ ትንሽ ግር ከተሰኘ በኋላ፥



«ኤኔትም? ሴት አያቴም? አባዬም? ድመቶቼም? አዎ፥ አባባ ሁላችንም መሄድ እንፈልጋለን፥» አለ ዳኒ ጠንከር ባለ አነጋገር።

«አይደለም፥ ዳኒ» አለች ኤኔት፥ «ሁላችን ልንሄድ አንችልም። ጥሩ ልጅ መሆንና ብቻህን መሄድ አለብህ ዶክተር ጊቤት እንክብካቤ ያደርጉልህና ቶሎ ትመለሳለህ፥» እንዲያ ትበል እንጂ ልቅሶ ቃጥቷት ነበር።

እነዚህ ቃላት የፈጠሩት ስሜት አስከፊ ሆነ። ዳኒ እራሱን፥ ድመቶቹንና ሁለመናውን ኤኔት እቅፍ ውስጥ ጥሎ ድምፁን ከፍ በማድረግ ያለቅስ ጀመር። እንዲያ ያለ ለቅሶ ሰምተው አያውቁም። ኤኔት እቅፉ ሳመችው። ሴት አያቱ ሊያባብሉት ሞከሩ። አባቱ ብስኩት እያስጨበጡ አባበሉት። ሙከራው ሁሉ አልጠቀመም። ቤተሰቦቹ ግራ በመጋባት ተያዩ።

ዶክተሩ በፍጥነት ሌላ መላ መፈለግ ያለባቸው መሆኑን ተረዱ፥ ወደ ኤኔት ሴት አያት ዞወር አሉና፥

«ይህች ልጅ ሕፃናትን መጠበቅ ትችላለች?» አሉ። ጎላ ባለ ድምፅ ነው የተናገሩት።

«ዳኒን ያሳደገችው እርሷ ናት፥» አሉ የኤኔት ሴት አያት እንደ ዶክተሩ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው።

«እንዲያ ከሆነ ከዳኒ ጋር ብትልኳት መልካም ነው። እቤቴ ሆና ከሚስቴ ጋር ለዳኒ አንዳንድ ነገር ልታደርግለት ትችላለች፥» አሉ ዶክተሩ።

«ዳኒ!» አለች ኤኔት እንዲያዳምጣት እየነቀነቀችው፥ «እኔም ከአንተ ጋር እሄዳለሁ!»

ዳኒ ወዲያውኑ ማልቀሱን ተወ። ከጉሮሮው ላይ የሚተናነቀውን ሳግ ካስታገሠ በኋላ ፈገግ አለ። ዶክተሩ ግን ኮስተር እንዳሉ ነው።

ብድግ ብለው ዳኒን አቅፈው አነሡትና፥ ኮስተር ብለው እንዲህ አሉ፥

«ምልቃቃ ልጅ ነህ መሰለኝ፥ ዳኒ። ወደ ሆስፒታሉ ስትሄድ፥ የምትታዘዘውን ሁሉ ሳታስቸግርና ሳታለቅስ መፈጸም ይኖርብሃል፥» ብለው ከእቅፋቸው አወረዱትና «የበረዶ ጋሪ ብትሰጡኝ ሉሲየንን ወደ ቤቱ እወስደዋለሁ» አሉ። ከዚያም «ለአሁኑ እሰናበታችኋለሁ።

አኔትንና ዳኒን ነገ ጠዋት በሁለት ሰዓት ተኩል ባቡር ጣቢያው እጠብቃቸዋለሁ። ለሚቀጥለው ሁለት ወይም ሦስት ወራት የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ይያዙ። አኔት ከቀትር በፊት ሚስቴን ሥራ ትረዳትና ማታ ማታ ትማራለች። ከቀትር በኋላ ከዳኒ ጋር ትሆናለች» አሉ።

የዳኒ አባት ዶክተሩን በትሕትና ጨበጧቸውና ዓይኖቻቸውን ጠራረጉ። ነገሮች ሁሉ በፍጥነት በመለዋወጣቸው ወደ ኋላ የቀሩ መስሎ ተሰማቸው። ለሚቀጥሉት ሁለት ወይም ሦስት ወራት ከዳኒና ከአኔት ተለይተው መኖር ያለባቸው መሆኑን ገና ተረዱ። ከነገ ጀምሮ ጸጥታ በሰፈነበት ቤታቸው ውስጥ ያለ እነርሱ መኖር ይጀምራሉ። ወተት እያለቡ ስለ ነገሩ ለማሰላሰል ብድግ አሉና ወደ ከብቶቹ በረት ሄዱ።

የአኔት ሴት አያት ዶክተሩን በር ድረስ ከሸኟቸው በኋላ፥ እጆቹን ያዝ አድርገው «ደግ ሰው ነህ! እግዚአብሔር ብድርህን ይክፈልህ፥» አሉ።

ዶክተሩ ጠንካራይቱን አሮጊት ትኩር ብለው አዩዋቸው። ከደስተኛዎቹና ጤናማዎቹ የልጅ ልጆቻቸው ጋር፥ እንዲሁም በእርሳቸው ተቆጣጣሪነት ከሚተዳደረው ሰላማዊና ጽዱ ቤት ጋር ተመለከቷቸው። ይበረታቱ የነበረው በፍቅርና በድፍረት መሆኑን ተረድተው ልዩ ሴት መሆናቸውን ተገነዘቡና፥

«አንቺም ጥሩና ደግ ሰው ስለሆንሽ፥ የበጎ ምግባርሽን ብድራት እንደምትቀበዪ እርግጠኛ ነኝ፥» አሉ።

ከዚያም ሉሲየንን በረዶ መንሸራተቻ ጋሪ ላይ ጭነው ወደ እናቱ ወሰዱት። እናቱ ሉሲየንን በጣም የተቀየሙት መስለው ታዩ። በመጣ ጊዜ፥ ዶክተሩን ረድተው ወደ ፎቁ እያወጡት፥

«አንተ መጥፎ ልጅ፥ ለማንም ሳትነግር ሄደህ እንዲህ ታስደነግጠን? እንዴት እንዲህ ታደርጋለህ? መገረፍ አለብህ...» ብለው አሉት። ከዚያም ደረጃዎቹን አስወጥተው አልጋ ላይ ያስተኙትም እርሳቸው ነበሩ። ያን ካደረጉ በኋላ ቁጭ ብለው ጥቁር ሻርፓቸውን ፊታቸው ላይ ጣል በማድረግ ማልቀስ ጀመሩ።

«በጣም ጎበዝ ልጅ ነው ያለዎት፥» አሉ ዶክተሩ የሉሲየንን እናት እየተመለከቱ።



«አይረባም፥» አሉ የሉሲየን እናት በቁጣ። በፈጸመው ነገር በጣም የኮሩና በደህና በመገኘቱ የተደሰቱ ቢሆንም፥ ከመቼውም ይበልጥ አለቀሱ።

ከሉሲየን እኅት ከማሪዬ ጋር ከጠዋት ጀምረው ሉሲየን የሚወደውን ኬክ ሲጋግሩ ነበር የቆዩት። ቤቱ በጥሩ መዓዛ ታውዷል። እምቢ አሏቸው እንጂ ዶክተሩ ከእነርሱ ጋር እንዲበሉ ጋብዘዋቸው ነበር። በአስቸኳይ የሚፈጽሟቸው ጉዳዮች ስለአሏቸው ቶሎ መሄድ ያለባቸው መሆኑን ገለጡላቸው። በመጨረሻም፥

«ሉሲየን የሚያውቀው አንድ ሽማግሌ በዚህ አካባቢ መኖሩን አምናለሁ። የት እንደሚኖር ልትነግሪኝ ትችያለሽ?» አሉ።

«አንድ ሽማግሌ?» አሀ፥ አዎ ሉሲየንን የእንጨት ቅርጻ ቅርጽ መሥራት ያስተማሩት ሰውዬ ናቸው። ተራራው ላይ ነው የሚኖሩት። ለብዙ ጊዜ አብረው ይቆያሉ። ሉሲየን ሽማግሌው ውስጥ ምን እንዳየ አልገባኝም፤ እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚያውቀው። ብዙ ሰዎች ሽማግሌው የአዕምሮ ሕመምተኛ ናቸው ይላሉ።

«ወደ ቤቱ የሚወስደውን አቅጣጫ ልትነግሪኝ ትችያለሽ?» ሲሉ ጠየቁ ዶክተሩ።

«አዎ፥ በጫካው ውስጥ የሚያቋርጠው ቀጥታ መንገድ ወደዚያ ነው የሚወስደው። እኔ እርስዎን ብሆን ግን ወደዚያ አልሄድም። ይህ ሁሉ በረዶ ከዘነበ በኋላ መንገዱ በጣም ይበላሻል፥» አለች ማሪዬ በዶክተሩ ጥያቄ እየተገረመች።

«ከእርሱ ጋር ጉዳይ አለኝ፥» እዚህ በር ላይ ቆመሽ የመንገዱን አቅጣጫ ልታመለክቺኝ ትችያለሽ። ስመለስ ወዲህ ጎራ ብዬ ሉሲየንን እሰናበተዋለሁ።»

ያን ዕለት ከቀትር በኋላ ዶክተሩ ወደ ሽማግሌው ቤት የተጓዙት፥ የጫካውን ውበት እያደነቁ ነበር። ሽማግሌው ምን ዓይነት ሰው ቢሆን ነው እዚህ ጭር ባለና ጸጥታ በሰፈነበት ስፍራ ብቻውን ተቀምጦ የጫካውን ምሥጢር የሚካፈለው? ሊያዩት ቸኮሉ፥ ልባቸውም ከቀድሞው ይልቅ በፍጥነት ይመታ ጀመር።

ጫካውን እንዳቋረጡ፥ የሽማግሌውን ቤት እልፍ ብሎ ሜዳው ላይ አዩት። የቤቱ ግድግዳ አጋማሹ ድረስ በበረዶ ተውጧል። ሽማግሌው ከቤቱ እስከ ጫካው ድረስ መተላለፊያ መንገድ አዘጋጅተዋል። «ጎብኚ እንግዳ ይጠብቁ ይመስል» አሉ ዶክተሩ የመንገዱን አቅጣጫ እየያዙ።

በሩን እንኳኩና የሚከፍትላቸው ሰው ሳይጠብቁ መዝጊያውን ገፋ አድርገው ወደ ውስጥ ገቡ። ሽማግሌው ምድጃው ዳር አጎንብሰው እንደ ተቀመጡ ሲጃራቸውን እያጨሱ እንጨት ይፍቃሉ። ውሻቸውና ፍየላቸው ከግራና ከቀኛቸው ተቀምጠዋል። ዶክተሩ ሽማግሌው ፊት ለፊት ያለው ወንበር ላይ ተቀመጡ።

«እሺ፣» አሉ ሽማግሌው እንዳቀረቀሩ፣ «በሰላም ደርሰህ ተመለስህ ሉሲየን?»

«ሉሲየን አይደለሁም፣» አሉ ዶክተሩ በቀስታ። ይሄኔ ሽማግሌው በፍጥነት ቀና አሉ። ሁለቱም ጣረ ሞት የተመለከቱ ይመስል ተፋጠጡ።

«ይህን ገንዘብ ልመልስልህ ነው የመጣሁት። ያን ሕፃን ለማዳን ገንዘብ አልፈልግም። በማንኛውም ሁኔታ የሚሳካ ከሆነ በነፃ ነው የማደርገው፣» አሉ ዶክተሩ።

«ልጁ የገባውን ቃል አላከበረም ማለት ነው፣» አሉና አጉረመረሙ ሽማግሌው። ከዚያም በያዙት ዱላ መሰል እንጨት ላይ አገጫቸውን አስደግፈው ለረጅም ጊዜ በዝምታ ወደፊት አፈጠጡ።

«ቃሉን አልሻረም። ገንዘቡ የዕዳ ክፍያ ከመሆኑና ከአንድ ሽማግሌ የተሰጠው ከመሆኑ በቀር የነገረኝ ነገር የለም። እኔ ግን የገንዘባቸው አመጣጥ በትክክል መሆኑን ካላረጋገጥሁ ከገበሬዎች ልጆች ብዙ ገንዘብ አልቀበልም። ያንተን ማንነትና የምትኖርበትን ስፍራ ከሌሎች ሰዎች ጠይቆ መረዳቱ አላስቸገረኝም።»

እንደገና ለረጅም ጊዜ በመካከላቸው ፀጥታ ከሰፈነ በኋላ፣

«ይህን ብቻ ልትነግረኝ ነው የመጣኸው?» አሉ ሽማግሌው በመጨረሻ። ድምጻቸው በቅጽበት ተለውጦ በጣም የአረጀ፣ ተስፋ የቆረጠና የደከመ ሰው ድምጽ ሆነ።

ዶክተሩ ፈጠን ብለው በመነሣት እጎበጠው ሽማግሌ አጠገብ በመንበርከክ፣

«ማስመሰሉ አይበቃንም? ማን መሆንህን አላጣሁትም። አንተም አውቀኸኛል። የመጣሁት ከእኛ መለየትህ በጣም ስለ ጎዳን ስንፈልግህ እንደ ኖርን ልነግርህና ወደ ቤታችን ልወስድህ ነው።»



## ምዕራፍ ሃያ አራት
## የኢየሱስ ፍቅር ሰዎችን ይለውጣል



አኔት ወደ ሉሲየን ሄዳ አጠገቡ ወንበር ላይ ተቀምጣለች። እርሱ አልጋው ላይ ተቀምጧል። አሁንም መገርጣትና ድካም ቢታይበትም፣ ተሽሎታል፣ ደስተኛ ነው።

«እስቲ የሆነውን ነገር ሁሉ ንገረኝ። ሰው ሁሉ ጎበዝ ልጅ ነው ይልሃል። ከመጀመሪያው እንሥተህ ታሪኩን ንገረኝ እስቲ ሉሲየን። የተራራው እራስ ምን ይመስላል?» አለች አኔት ዐይኖቿን በመገረምና በአድናቆት በሰፊው ገልጣ።

ጎበዝ ተብሎ መጠራት ደስ ስለሚያሰኝ ሉሲየን ታሪኩን ጥሩ አድርጎ ሊያወራላት ይችል ነበር። ነገር ግን የሆነው ሁሉ ልክ እንደ ህልም ያለፈና የራቀ መስሎ ተሰማው።

«መጀመሪያ ወደ ሽማግሌው ሄድኩና ትንሽ ገንዘብ እንዲሰጡኝ ጠየቅሁዋቸው። ከዚያም በበረዶ መንሸራተቻዩ አማካይነት ቁልቁል ወደ ሸለቆው ወረድኩ። ሜካውን አቋርጬ ወንዙን ከተሻገርኩ በኋላ ጉዞዩን ቀጠልኩ፣» አለ ሉሲየን።

«አዎ፣ እንዳልከው አድርገሃል፣ ወይም እዚያ አልደረስክም። እስቲ እስቲ በደንብ ንገረኝ ሉሲየን። ምን ተሰማህ? የሚፈታተን ነገር ገጥሞህ ነበር? ፈርተሃል? ለሞት የሚያደርስ ነገር ገጥሞህ ነበር? ተራራ ጫፍ ላይ መሆን ምን ስሜት ይፈጥራል?» ስትል አኔት አቋረጠችው።

ሉሲየን ለጥቂት ጊዜ ዝም አለ። ያን ዕለት ከሰዓት በኋላ ያስብ የነበረው፥ ከአኔት ጋር ተገናኝቶ ያጋጠመውን ሁሉ እንዴት እንደሚነግራት ነበር። አሁን ዕድሉን አግኝቷል፤ እንዴት እንደሚጀምረው ግን አላወቀም።

«አዎ፥» አለ፥ በመጨረሻ ዝግ እያለ፥ «ተራራው ጫፍ ላይ ለመድረስ ትንሽ ሲቀረኝ ፈርቼ ነበር። ወደ ኋላ ልመለስም ነበር። በጣም ትጠይኝ እንደነበር የነገርሽኝን ታስታውሻለሽ አኔት? ኢየሱስን እንዴት ወደ ልብሽ እንደ ጋበዝሽና በጥላቻ ፈንታ እንደ ወደድሽኝ ትረሻለሽ?»

«አዎ፥ በደንብ አስታውሳለሁ። ለምን አነሣኸው ሉሲየን?» አለች በጉጉት። «ምክንያቱም በፈራሁ ጊዜ ያን የመሰለ አንዳች ነገር በሕይወቴ ስለ ተፈጸመ ነው። ሴት አያትሽ ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን እንደሚያስወግድ ያስተማሩንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አስታወስኩና ኢየሱስ ያን ፍርሃቴን እንዲወስድልኝ ጠየቅኩት። ያን ባደረግሁ ጊዜ በጣም ያስጨንቀኝ የነበረው ፍርሃት ወዲያው ተወኝ።»

«እውነትከን ነው? እንዲያ ከሆነማ በእኔ እንዳደረገው፥ ኢየሱስ ወደ ልብህ ገብቷል ማለት ነው። እኔ በአንተ ላይ የነበረኝ ጥላቻ እንደ ተወኝ፥ ፍርሀትህም ትቶህ መሄድ ነበረበት። በሁሉም ላይ ነገሩ ተመሳሳይ ይመስለኛል፥ ሉሲየን። ፍርሃት ቢኖርብህ፥ ሰው የምትጠላ አታላይ፥ ውሸታም፥ ሰነፍ፥ ቁጡ... ብትሆን፥ ኢየሱስ ወደ ልብህ ሲመጣ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ስፍራ አይኖራቸውም።» አለች አኔት፥ በጣም በመመሰጥ።

«አዎ፥» አለ ሉሲየን በአሳቧ በመስማማት፥ ለረጅም ጊዜ ቁጭ ብለው በዚሁ ጉዳይ ላይ ተነጋገሩ።

አኔት በረዶ በሸፈነው መንገድ ላይ እየተጓዘች፥ ቤቷ ውስጥ ብታመሽ የመጨረሻም እንደሆነና ለረጅም ጊዜ እርቃ የምትሄድ መሆኗን ስትገነዘብ በጣም አዘነች። ፍጥነቷን ጨምራ እሮጠች።

አባቷ ከብቶች በረት ውስጥ ናቸው። ሴት አያቷ አኔት ቀሚስ ላይ ቁልፎችን ይሰፋሉ። የአኔትና የዳኒ ልብሶች በሚገባ ተስተካክለውና ተጠቅልለው ለጠዋት ጉዞ ተዘጋጅተዋል። ዳኒ ድመቶቹ ለመጨረሻ ጊዜ እላዩ ላይ ሆነው አልጋው ላይ አንቀላፍቷል።



አኔት «አያቴ!» ብላ ከተጣራች በኋላ ተንደርድራ ሴት አያቷን በማቀፍ ታለቅስ ጀመር።

ሴት አያቷ ለጥቂት ጊዜ እንድታለቅስ ዝም አሏት። ከዚያም ወንበር ሳብ አድርገው አጠገባቸው አስቀመጧት። አኔት እራሷን አያቷ ጉልበት ላይ አስደገፈች። አያቷ ቀስ እያሉ ይነግሯት ጀመር። አኔት ስለምትሄድበት ቤት ሁኔታ፥ እዚያ ስለምታከናውነው ሥራ እና ዳኒ ድኖ ማየቱ በጣም መልካም ስለ መሆኑ ነገሯት። የሴት አያቷ ንግግር ብርታትን የሚገልጥ ይሁን እንጂ፥ ከጥልቅ አሳባቸው የሚያወጣው ያ ንግግር፥ «ነገና ከዚያ በኋላ በሚኖሩት ምሽቶች አጠገቤ ያሉት ወንበሮች የሚቀመጥባቸው ሲታጣ፥ እንዲሁም በሕፃኑ መኝታ ላይ የሚተኛ ልጅ ሳይኖር ሲቀር ምን ይውጠኛል?» እያሉ ያሰላስላሉ።

ስለ መሸና በማለዳ መነሣት ስለ አለባቸው፥ አኔት ሁልጊዜ በመኝታ ሰዓት እንደምታደርገው ድምጽዋን ከፍ አድርጋ ለሴት አያቷ ልታነብላቸው ትልቁን የመጽሐፍ ቅዱስ ከመደርደሪያው ላይ አመጣች።

«ዛሬ አንደኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ አሥራ ሦስትን ነው የምናነበው። ርቀሽ በምትቆዪበት ጊዜ ሁሉ እንድታስታውሺው የምፈልገው ምዕራፍ ነው፥» አሉ ሴት አያቷ አኔት ትልቁን መጽሐፍ ጉልበቷ ላይ ስታደርገው እያዩ።

አኔት የተነገራትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብባ እንደ ጨረሰች ሴት አያቷ፥ «በደንብ እንድታስታውሺው የምፈልገው «ፍቅር ይታገሳል፥ ፍቅር አይቀናም፥ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም» የሚል ቃል ያለበትን ቁጥር አራትን ነው።

«እንግዲህ፥» አሉ ሴት አያቷ፥ በመነጽራቸው አናት አኔትን እያዩ፥ «ኢየሱስ ወደ ልብሽ እንዲገባ እንደ ጠየቅሽውና እርሱም ፍቅሩን ይዞ ወደ ልብሽ እንደ ገባ ነግረሽኛል። ያ ፍቅር አሁን ያነበብነውን ፍቅር ይመስላል። አሁን የምትሄጂው ሕፃናትን ልትጠብቂ ነው፤ ከልጆቹ ጋር ብዙ ጊዜ የማትስማሚበት ሁኔታ ይፈጠር ይሆናል። መጥፎዎች ሲሆኑብሽና ስትናደጂ፥ ትዕግሥትሽም ሲያልቅ፥ እንዲረዳሽ ኢየሱስን ጠይቂው።

የምትሄጂው ወደ ትልቅ ቤት ነው፥ አኔት ምን ጊዜም እንዲኖሩሽ ልታደርጊያቸው የማይቻልሽ ነገሮችን ትመለከቺ ይሆናል። በእነዚያ

ነገሮች ትቀኚና ያንቺ ባለመሆናቸው ይከፋሽ ይሆናል። ነገር ግን አትርሺ፥ ልብሽ በፍቅር ከተሞላ ለቅናት ስፍራ አይኖረውም።

ሥራ በጣም እሚበዛበት ቤት ውስጥ ትንሽ ሠራተኛ ልትሆኚ ነው። ብዙ የሚያቀርብሽ ሰው ይኖራል ብዬ አልጠብቅም። ውስጥሽ ያለው የኢየሱስ ፍቅር ልታይ፥ ልታወቅ የሚል አለመሆኑን ግን ማስታወስ አለብሽ። ሰው ቢያይሽም ባያይሽም የክርስቶስ ፍቅር ሥራሽን በጸጥታና በፍቅር እንድታከናውኚ ያደርግሻል። ኢየሱስ ጌታሽ መሆኑንና የምትሠሪው እርሱን ለማስደሰት መሆኑን አስታውሺ።»

«እሺ አያቴ፥ ለማስታወስ እሞክራለሁ፥» አለች አኔት በጥልቅ እያሰላሰለች። ከዚያም ሴት አያቷን ሳመቻቸውና ለመኝታ የቀራትን የግማሽ ሰዓት ጊዜ ከአባቷ ጋር ለማሳለፍ ወደ ከብቶቹ በረት ሮጠች።

በማግስቱ ማለዳ ቤተሰቡ ሁሉ በጋሪ ተሳፍረው ወደ ባቡሩ ጣቢያ ተጓዙ። ባቡሩ ያመልጠናል ብለው ስለ ፈሩ፥ ከጊዜው ግማሽ ሰዓት ቀድመው ነበር ስፍራው የደረሱት። ተጓዦች መቆያ ስፍራ ላይ ሆነው ዶክተሩን ይጠብቁ ጀመር። ብዙም ሳይቆይ ነው ዶክተሩ የመጡት፥ ቡናማ ቀለም ባለው ወረቀት የተጠቀለለውን ሻንጣቸውን የተሸከሙትው አኔት ናት። ያን እንደ`ተሸከመች የአባቷን እጅ ጥብቅ አድርጋ ይዛለች።

ዳኒ ካፖርቱን ለብሶ ቆቡን እንዳደረገ በጣም የፈራና የአፈረ መስሎ ተቀምጧል። ድንግርግር ስለአለው የመጨረሻው መሰነባበቻ ወቅት በደረሰ ጊዜ ሰው አቅፎ እንዲሰናበተው አልፈለገም። ባቡሩ ገና ሸለቆው አካባቢ እንደ ደረሰ ነው ዳኒ እንዲያ የሆነበትን ምክንያት አኔት የተገነዘበችው። ስግ የሚለው ይመስል የለበሰው ካፖርት ይንጥራል።

«ካፖርትህ ሥር ያለው ምንድን ነው ዳኒ?» አለች አኔት በመደነቅ ዐይኖቿን አፍጥጣ።

ፊቱ በፍርሃት ቀላ። «አንድ ብቻ ነው፥ አኔት» አለ በፍርሃት።

«አንድ ምን?» አለች አኔት፥ በስጋት ወደ ዶክተሩ እየተመለከተች። ዶክተሩ ግን መጽሐፍ ያነቡ ስለነበር የተናገረችውን አልሰሙም።


«እርሱ ብቻ ነው፥» እያለ የካፖርቱን ቁልፍ ሲፈታ፥ አንድ ነጭ ድመት ፊትና ሪዙን ብቅ አደረገና ወደ ውስጥ ተመለሰ።



«ዳኒ!» አለች አኔት በድንጋጤ፥ «በጣም፥ በጣም መጥፎ ልጅ ነህ! ሆስፒታል ውስጥ ድመት ይዘህ ለመግባት እንደማትችል ሴት አያታችን ነግራሃለች። አሁን ምን እናደርገዋለን?»

ዳኒ በመስኮት ወደ ውጭ እየተመለከተ ዝም አለ። ስለፈጸመው ጥፋት ምን ሰበብ ሊያቀርብ እንደሚችል ሊያስብ አልቻለም። ድመቱን ግን ማንም ሳያየው ወደ ውስጥ ጫን አደረገው። ድመቱም ሞቃት ገላውን ዳኒ ሰውነት ላይ ጥምጥም አደረገና የማጉረምረም ድምፅ አሰማ። ዳኒም ሆነ ድመቱ ስለሆነው ነገር ቅንጣት ታህል ኀዘኔታ አልተሰማቸውም።

## ምዕራፍ ሃያ አምስት
## ዳኒ ተሻለው



ከተማው ውስጥ እንደ ደረሱ ነው ዳኒ አልጋ የያዘው። እንደ እርሱው ሽባ የሆኑ ልጆች ወደሞሉበትና ድካም የተሰማት ነርስ ወደምትቆጣጠረው ክፍል ተወሰደ። ሁሉንም አንዴ ተመልክቶ መዝናናት እንደሚያስፈልጋቸው ተረዳና በክራንቹ አማካይነት እንደ ካንጋሮ እየዘለለ መደዳውን አለፈ። ያሰበው ተሳካለትና በአንድ ሰዓት ውስጥ ከሁሉም ጋር ተግባባ። ነጭ ድመቱ ወጥ ቤቱ ውስጥ ቅርጫት ተዘጋጀለት። በሐኪሞች ጉብኝት ጊዜ እዚያ ይቆያል።

አኔት በጣም ደስ አላላትም። የዶክተሩ ሚስት በጥሩ ሁኔታ ነው የተቀበለቻት። ሴትዮይቱ ወጣት፥ ቆንጆና ቀልደኛ ናት። አኔትን በቤቱ የመጨረሻ ፎቅ ላይ ወደ ተዘጋጀላት ስፍራ ወሰደቻት። አኔት ብቻዋን ስትሆን ወደ መስኮቱ ሮጥ ብላ ወደ ውጭ ተመለከተች። ቤቶች፥ መንገዶች ላይ የረጋ በረዶና ቅርብ የሚመስል ግራጫ ሰማይ ታያት። ለጥቂት ጊዜ ከተመለከተች በኋላ መለስ ብላ እተዘጋጀለት አልጋ ላይ በመጋደም ትታው ስለመጣችው ቤት ታለቅስ ጀመር።

የዶክተሩ ሚስት ከግማሽ ሰዓት በኋላ ልታያት ስትመጣ አልጋው ላይ እንደ ነበረች ነው ያገኘቻት። ምንም አልተናገረችም። ተመልሳ ሄደችና ክሌይር የምትባል ሕፃን አምጥታ አልጋው ላይ አኔት ጎን አጋደመቻት። ያ ብቻ ነበር ልታደርገው የምትችለው። ከአምስት ደቂቃ



በኋላ አኔት ነቅታ ሕፃኗን በማቀፍ ታፋዋ ላይ እያዘለለች አብራት ትስቅ ጀመር።

ዶክተሩ ቤት ውስጥ ደስተኛና ሥራ የሚበዛባት ሰው ሆነች። ከቀትር በፊት ባለው ጊዜ የዶክተሩን ሚስት ሥራ እየረዳች ሕፃናትን ትጠብቃለች። ከቀትር በኋላ ያለውን ጊዜ ከዳኒ ጋር ታሳልፍና ማታ ትምህርቷን ታጠናለች። ሕፃናቱ አንዳንድ ጊዜ ያስቸግሯታል። በመጀመሪያው አካባቢ ብዙውን ጊዜ የዶክተሩ ሚስት እየመጣች ነበር የምታስማማቸው። አኔት አንዳንድ ጊዜ በሕፃናቱ ድርጊት የምትቆጣና ትዕግሥቷ የሚያልቅባት ቢሆንም፥ በሴት አያቷ ምክር ለመመራት ብዙ ሞከረች። ውስጧ ያለው የኢየሱስ ፍቅር ቀስ በቀስ ታጋሽ፥ ደግና ሰው አፍቃሪ ያደርጋት ጀመር። በመጨረሻም በቀስታ የምትናገርና ቁጣዋን የምትቆጣጠር ልጅ ሆነች።

ዳኒ እግሩ ኦፕራሲዮን ከመሆኑ በፊት ለአንድ ሳምንት ሆስፒታል ውስጥ ቆየ። ወደ ኦፕራሲዮኑ ክፍል ሲወሰድ ደስተኛ ነበር። ከሰዓታት በኋላ ከኦፕራሲዮን ሸለብታው ሲነቃ ግን አልጋው ከግርጌ ከፍ ብሎ በማየቱ ተበሳጨ። እግሩ ላይ የታሠረው ከባድ ብረት የሕመም ሥቃይ አሳድሮበታል። ትኩሳትና ሕመም ስለ ተሰማው አኔትን ይጣራ ነበር።

ብረቱ እግሩ ላይ እንደ ተንጠለጠለ አንድ ሳምንት ሙሉ በጀርባው ተኛ። ትኩሳትና የሕመም ሥቃይ ይሰማው ነበር። አኔት በየቀኑ እየመጣች ታሪክ በማንበብና በቃልዋም በመንገር የሕመሙን ሥቃይ እንዲረሳ ለማድረግ ትሞክር ነበር። አረንጓዴ ውኃ ባለው ሐይቅ ላይ ጭጋጋማ ደመና አንዣቦበታል። ዳኒ ለመንቀሳቀስና ጠንካራ ልጅ ለመሆን ሞክሮ ነበር፤ አልቻለም።

በዚያ ረጅም ጊዜ ዳኒን ያጽናናው አንድ ነገር ነው። ሊያነበው ያልቻለው ጽሑፍ ከግርጌው የተጻፈበት አንድ ሥዕል ፊት ለፊቱ አለው ግድግዳ ላይ ተሰቅሏል። ሕመሙ፥ አኔት የምትነግረው ታሪክ፥ ጭጋግ የሸፈነው ባሕር እና ከሌሎች ሕፃናት ጋር መሆኑ ሲሰለቸው ወደ ሥዕሉ ይመለከታል። እርሱን ማየቱ አይሰለቸውም።

ኢየሱስ ክርስቶስ አበባ በበዛበት ሜዳ ውስጥ ቁጭ ብሎ የሚታይበት ሥዕል ነው። የዓለም ሕፃናት ዙሪያው ቆመው የኢየሱስ ክርስቶስን ፊት ሲመለከቱ ይታያሉ። ኢየሱስ እግር ሥር፥ ሣሩ ላይ አንድ ጥቁር ልጅ ተቀምጧል፤ ጉልበቱ ላይ ደግሞ አንድ ሕንዳዊ ሕፃን። የኢየሱስ እጆች አረንጓዴ ቀሚስ እለበሰች አንዲት ልጅ ላይ አርፈዋል። የቻይናና የደቡብ ባሕር አካባቢ ልጆች ደግሞ ተደግፈውት ሽቅብ ይመለከቱታል።

ዳኒ ኦፕራሲዮን ከሆነ ከሳምንት በኋላ ነበር ከአኔት ጋር ስለ ሥዕሉ መነጋገር የጀመሩት። ዳኒ የተኛበት ክፍል መብራት በርቷል። አብዛኛዎቹ ልጆች እንቅልፍ ወስዷቸዋል! አኔት ግን ዳኒ አጠገብ ተቀምጣለች። በጊዜ ስትሄድበት ስለሚበሳጭ፥ ማምሸት ጀምራለች።

አሁን እጆቹን ተንተርሶ ተጋድሟል።

ዐይኖቹ ብሩህ ሆነዋል። በጣም ስለ ደከመው እንቅልፍ፥ እንቅልፍ ቢለውም፥ የእግሩ ሕመም እንቅልፍ ከልክሎታል። በመሆኑም ጽሑፍ ያለበትን ሥዕል ለመመልከት ዘወር አለና፥

«ያ ጽሑፍ ምንድን ነው የሚለው፥ አኔት?» አለ። «ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ፥ አትከልክሏቸው» ነው የሚለው አለች። እርሷም የደከማት ትመስላለች።

«ያን ታሪክ አውቀዋለሁ! ሴት አያቴ ነግራኛለች። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ሕፃናት ናቸው?» አለ በደካማ ድምፅ።

«የለም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት ሕፃናት አይደሉም ዳኒ። ከዓለም ዙሪያ የተሰበሰቡ ሌሎች ልጆች ናቸው። ከሕንድ፥ ከአፍሪካና እንደሚመስለኝ አረንጓዴ ቀሚስ የለበሰችው ልጅ ከስዊዘርላንድ ናት።»

«ለምን?» ሲል ጠየቀ ዳኒ።

«መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ብቻ ሳይሆኑ ሕፃናት ሁሉ ወደ ኢየሱስ ለመምጣት የሚችሉ መሆናቸውን ለማሳየት ይመስለኛል።»

«እንዴት?» አለ ዳኒ።

«እንዴት እንደምገልጠው አላውቅም። ወደ ኢየሱስ ለመምጣት የምትፈልግ መሆንህን ብቻ ከገለጽህ፥ እዚያ ትሆናለህ። ልታየው ባትችልም እንኳን፥ ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳሉት ልጆች ያቅፍሀል።»

«አሀ፥ ገባኝ አኔት። እግሬን በጣም አሞኛል። እንቅልፍ በወሰደኝ።» አለ ዳኒ።

ያቃስትና እጆቹን ያወራጭ ጀመር። አኔት ትራሱን ከፍ አድርጋለት የሚጠጣ ነገር ሰጠችው። ከዚያ በኋላ ነው ሕመሙ ቀለል ያለለት።

«ዘምሪልኝ፥» አላት በትእዛዝ አነጋገር። ነርሷ እንዳትሰማ ድምጽዋን ዝቅ አድርጋ ዘመረችለት።

መዝሙሩን እያደመጠ ዐይኖቹን ከደነ። ከዚያ ጥቂት ሰኮንዶች ቀደም ብሎ ግን ሥዕሉን እንደገና ያየ መሰለው። ኢየሱስ ጉልበት ላይ



በተቀመጠው ሕንዳዊ ሕፃን ምትክ እራሱን አሰበ። የሚሞረኮዛቸው ክራንቾች እግሩ ሥር ሣር ላይ ተጋድመው በአሳቡ ታዩት።

«እኔ ነኝ፥» ብሎ ለእራሱ ነገረና በደስታ ከባድ እንቅልፍ ወሰደው።

እንቅልፍ እንደ ወሰደው ዶክተሩ መጥተው ከከባዶቹ ብረቶች አንዱን ከእግሩ ላይ ስለ አነሡለት ትኩሳቱ ተወው። ሲነቃ በአንዳች ሁኔታ አዲስ ዓለም ውስጥ ያለ ያህል ተሰማውና ስለዚያ እያሰበ ለረጅም ጊዜ በጸጥታ ተኛ። ትኩሳቱ በርዶለታል፥ ምቾት ይሰማዋል፥ የእግሩ ሕመምም ትቶታል። የክፍሉ ትልቅ የመስታወት በሮች በሰፊው ተከፈቱ። ዳንኤል በተከፈቱት በሮች በኩል ለመጀመሪያ ጊዜ የጠራ ውኃ፥ በሐይቁ ሌላ አቅጣጫ ደግሞ ጭጋጋማ ሰማያዊ ተራራዎችና ብሩህ ሰማይ ተመለከተ።

«ልድን ነው፥» አለ ለራሱ። አኔት ከንፋሱ በመከለሷ ሙቀት እየተሰማት ዳኒ ወደ አለበት ክፍል መጣች። ለወትሮው ሁኔታውን የምትመለከተው ከቁርስ በኋላ ሽሽግ ብላ ነበር።

«ጥሩ ቀን አይደለም፥ ዳኒ? ሐይቁንና ተራራዎቹን፥ እንዲሁም ሐይቁ ላይ የሚንሳፈፉትን ትንንሽ መርከቦች እስቲ ተመልከታቸው፥» አለች በአድናቆት።

ፊቱን ኮስተር አድርጎ ወደ እርሷ ዘወር አለና፥ «ክራንቾቼ የት ነው ያሉት?» አላት።

«እዚሁ፥ ከኋላህ አለው ዕቃ ማስቀመጫ ውስጥ ናቸው። ለምን ፈለግካቸው?»

«እዚያ ጥግ የተኛውን ልጅ ታውቂው የለም? ያስፈልጉት ይሆናል! ስጪው።»

«ለምን ዳኒ? በጣም ትወዳቸው የለም እንዴ?»

«አዎ፥ ከእንግዲህ ግን አያስፈልጉኝም። ልድንና ማንኛውንም ጫማ አድርጌ ልሯሯጥ ነው።»

እውነቱን ነበር ዳኒ። ክራንቾቹ ከእንግዲህ አያስፈልጉትም። ሙሉ በሙሉ ድኗል።

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት
# አዲስ ጅማሬ



ሳምንታት በሸለቆው አካባቢ እንደ አለፉ ሁሉ በተራራውም አካባቢ አለፉ። በረዶው መሟሟት ስለ ጀመረ፥ ትንንሽ ምንጮች ወራጅ ወንዝ ሆኑ። በወንዙ አካባቢ የሜዳ አበባዎች ብቅ፥ ብቅ ይሉ ጀመር። በየበረቱ ተዘግተውባቸው የሰነበቱት ከብቶችና ፍየሎች ወደ ውጭ አውጡን በሚል ጥሪ ጮሁ፥ ተቅበጠበጡ። የፀደይ መምጣት ብሥራት በተራራዎች አናት ላይ ታየ።

የእነ አኔት ሴት አያት ለፀደይ ወራት መቃረብ ዝግጅት አካባቢያቸውን በማጽዳት ሥራ ተጠምደዋል። የዳኒ አባት ደግሞ አዲስ የተወለዱ ጥጃዎችን በመንከባከብ ላይ ናቸው። ይህ ሁኔታ ለሁለቱም ጥሩ ነው፤ ምክንያቱም በሥራ ሲጠመዱ በዳኒና በአኔት ናፍቆት አይቸገሩም። በጣም ያረጁትና አካባቢውን ለማጽዳት የዐይኖቻቸው ብርሃን ደካማነት የማይፈቅድላቸው የእነ አኔት ሴት አያት፥ አንዳንዴ ቁጭ ይሉና በክራንችና በአንድ እግር እርምጃ ወደ ፎቁ የሚወጣ ሰው እንቅስቃሴ የሰሙ አስመስለው ያስባሉ፤ በተሰባበረ ድምፅ የሚዘምር የትንሽ ልጅ ድምፅ የሰሙም ይመስላቸዋል። ሴት አያታቸውና አባታቸው እነዳኒን በጣም ናፍቀዋቸዋል!

ሉሲየንም ናፍቋቸዋል። ከሌሎቹ ልጆች ሁሉ ወደ ተራራው እርቆ ስለሚኖር፥ ከትምህርት ቤቱ በተመለሰ ቁጥር አኔት አብራው እንድትገኝ ያልተመኘበት ጊዜ አልነበረም። ትምህርት ቤቱ ውስጥ ግን



እንደ ቀድሞው ብቸኛ አልነበረም። ተራራዎችን አቋርጦ ባደረገው ጉዞ ለፈጸመው በደል መጸጸቱን ስለ አረጋገጠ ልጆቹ ሁሉ አቅርበውታል።

ሉሲየን እራሱም ተለውጧል። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልቡ እንዲገባ ከጠየቀበት ምሽት አንሥቶ ባሕርይው የተለወጠ መሆኑን ተገንዝቧል። የቀድሞ ቁጡነቱ፥ ስንፍናና ኀዘን ለክርስቶስ ፍቅር እተከፈተ ልብ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ሊቆዩ አይችሉም። ሉሲየን ቀስ በቀስ ይህን ይገነዘብ ጀመር። በየቀኑ መጽሐፍ ቅዱሱን በማንበብና በጸሎት ወደ ኢየሱስ በቀረበ መጠን ከቁጣና ከስንፍና የጠነከረ ፍቅር ስለአደረበት በጣም ጥሩ ልጅ ሆነ።

ከትምህርት ቤት መልስ ሁልጊዜ ወደ እነ አኔት ቤት በመሄድ በጽዳት ሥራ ሴት አያታቸውን ያግዛቸዋል። አሁን በጣም ተዋደዋል። የአኔት ሴት አያት የሉሲየን እርዳታ በጣም የሚያስፈልጋቸዋል ሆነዋል። እንጨት የሚፈልጥላቸው፥ ወደ መደብር በመላክ የሚፈልጉትን የሚገዛላቸውና ወደ መንደሪቱ እየሄደ ደብዳቤ የሚያመጣላቸው እርሱ ሆኗል። ደብዳቤዎቹ ብዙውን ጊዜ የሚላኩት ከአኔት ስለሆነ ያን ማምጣቱን ወዶታል። ደብዳቤዎቹን ይዞ ሲመጣ የአኔት አያት ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲያነብ ይጠይቁታል። አንዳንዴም ዳኒ የሚሠራቸው ሥዕሎች ስለሚላኩ ሴት አያታቸው መጽሐፍ ቅዱሳቸው ውስጥ ያጠራቅሟቸውና አልፎ አልፎ እያወጡ ያዩዋቸዋል። እስከ ጥር ወር መጨረሻ ብዙ ሥዕሎች አጠራቀሙ። «አልጋ ውስጥ ሆኜ»፥ «ፍየሎችን ሳባርር»፥ «መድኃኒት ስወስድ»፥ «እኔና ነርሷ»፥ «እኔና ድመቷ»፥ የሚሉ አርዕስት የተሰጧቸው ሥዕሎችም ነበሩ። ሴት አያታቸው ሁሉንም በቆንጆነታቸው አድንቀዋቸዋል።

አሁን ደግሞ ሉሲየንን ያሳዘነ ሌላ ነገር ተፈጠረ። የእንጨት ቅርጻ ቅርጽ የሚሠሩት ሽማግሌ ጓደኛው ከተራራ አካባቢ መኖሪያቸው ለቅቀው ወደ ሐይቁ አካባቢ ሊሄዱ ነው። ልጃቸው ከሆነው ዶክተርና ከቤተሰቡ ጋር እንዲኖሩ ተወሰነ። ይህ የተወሰነው ዶክተሩና ሽማግሌው ተገናኝተው አንደኛው ሌላውን ባስታወሱበት ዕለት ነበር።

መሄድ የነበረባቸው ሉሲየን ዕቃቸውን ለጉዞ በማዘጋጀት ሊረዳቸው በሄደበት ዕለት ነበር። ፍየላቸውን፥ ድመታቸውንና ዶሮዎቻቸውን ለሰዎች ሰጥተው ከቅርጻ ቅርጽ ሥራዎቻቸው አብዛኛዎቹን ሸጠዋቸው ነበር። ቤቱን ግን አልሸጡትም፤ እስኪመለሱ ድረስ ዘግተው ሊያቆዩት ፈልገዋል።

«ብዙ ጊዜ ወደዚህ እመጣለሁ ሉሲየን። ከተራራው እርቄ ለብዙ ጊዜ ልቆይ አልችም። ሐይቁ አካባቢ ትንሽ ቆይቼ ተራራዎች ሲጠሩኝ ስለምመለስ የበዓላት ቀናትን ለማሳለፍ ያህል እመጣለሁ፥» ብለው ነበር ሽማግሌው።

እያሰላሰሉ ወደ ሸለቆው ከተመለከቱ በኋላ፥ ጎጆው ውስጥ ያሉትን ባዶ መደርደሪያዎች ቃኟቸውና፥

«ለሕፃናት ለመስጠት ከቅርጻ ቅርጽ ሥራዎች ጥቂቱን ይዤ ሄዳለሁ። ይወዱቸው ይሆናል። አንዱን ላንተ ነው ያስቀመጥኩልህ። አንድ ቀን ምሽት ላይ ስመራርጥ ነው ያገኘሁት። እንዲለየኝ የማልፈልገው ሥራ ነበር። ከፈለግከው ብትወስደው ደስ ይለኛል፥» አሉ።

«ብወስደው ደስ ይለኛል። እርስዎን ያስታውሰኛል። እርሱኑ አስመስዬ ልሠራ እችልም ይሆናል፥» አለ ሉሲየን በጉጉት እየተመለከታቸው።

ሽማግሌው ወደ ቁም ሣጥኑ ሄዱና ለሉሲየን ለይተው ያስቀመጡትን ስጦታ አምጥተው ሰጡት። ሉሲየን ስጦታውን እያገላበጠ ሲያይ ሽማግሌው ትኩር ብለው ይመለከቱት ነበር።

ስጦታው ላይ ላዩን ሲታይ አልባሌ ሥራ ይመስል ነበር። ከሁለት ያልለሰለሱ እንጨቶች የተሠራ መስቀል ነው። ቋሚውና አግዳሚው እንጨቶች የተጋጠሙት ግን በጥሩ የገመድ ቋጠሮ ነበር። ሉሲየን በሚያምር ሁኔታ የተስተካከለውን ቋጠሮ በጣቶቹ ከዳሰሰ በኋላ ቀና ብሎ ሽማግሌውን ተመለከተና፥

«በጣም ያምራል! እንጨቱ ሳይሰበር ገመዱን የቋጠሩበት አሠራር ይገርማል። ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ነው፤ አይደለም እንዴ?» አለ እንደ ማፈር እያለ።

«አዎ ነው። መምህሬ በሞተበት ምሽት ነው የሠራሁት። በዚያው ምሽት ነበር ስለ እግዚአብሔር ፍቅርና ምሕረት የነገረኝ። የበደል ይቅርታ እንደማገኝ በዚያው ምሽት አመንኩ። እኔና አንተ ስለ ፍቅር አንድ ጊዜ ተነጋግረናል፤ ፍቅርን በፍጹምነቱ የምናየው መስቀል ላይ ነው።»

«ፍጹም ፍቅር! የአኔት አያት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ክፍል የሚናገረው ስለዚሁ ነው። በተደጋጋሚ ሰማሁት። በመሄጃዋ ዋዜማ



ምሽት እኔና አኔት የተነጋገርነው ስለ ፍጹም ፍቅር ነበር፥» አለ ሉሲየን ፈጠን ብሎ።

«አዎ፥ ሁልጊዜ ትሰማዋለህ! ፍጹም ፍቅር ማለት ምንም እስከማይቀር ድረስ መልካም ማድረግ፥ እስከ መጨረሻው ሥቃይ ድረስ መሠቃየት። ለዚህ ነው ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ላይ በሰቀሉት ጊዜ፥ ‹ተፈጸመ› ያለው። ኢየሱስ ሲሞት ይቅር ያልተባለ ኃጢአት፥ ያልዳነ ኃጢአተኛ አልነበረም። በፍጹም ፍቅር ነበር የወደደን።»

ሽማግሌው ይህን በሚናገሩበት ጊዜ ሉሲየን አጠገባቸው መኖሩን ረስተው ለራሳቸው የሚያወሩ ይመስል ነበር። ሉሲየን ግን እያዳመጣቸው ነበር። በመጨረሻ ከሽማግሌው ጓደኛው ተሰናብቶና በሚቀጥለው ማለዳ በመምጣት ወደ ትምህርት ቤት ሲሄድ እግረ መንገዱን ዕቃቸውን እስከ ባቡር ጣቢያ እንደሚወስድላቸው ቃል ገብቶላቸው ወደ ቤቱ ሮጠ። ሽማግሌው ይዘውለት ይሄዱ ዘንድ ለአኔት ደብዳቤ ለመጻፍ ቸኩሏል። በቅድሚያ ያደረገው ነገር ግን፥ ሽማግሌው የሰጡትን ትንሽ የእንጨት መስቀል ከአልጋው በላይ ግድግዳ ላይ መስቀል ነበር። ከዚያም ወረቀትና እስክሪብቶ ፍለጋ ወደ ወጥ ቤት ሮጠ።

የወጥ ቤቱ ዕቃ ዝብርቅርቅ ብኋል። እናቱ ከላሞቻቸው ጋር ስለነበሩ ዕቃዎቹን ለማጠብና ለማደራጀት አልቻሉም። ሉሲየን ለወትሮው ዕቃዎቹን በማጠብና በማደራጀት እናቱን ይረዳቸው ነበር። ዛሬ ግን ቸኩሏል። ቀስ ብሎ መኝታ ቤቱ ቢገባ፥ በፀጥታ ደብዳቤውን ሊጽፍ ይችላል። እናቱም መምጣቱን ስለማያውቁ ዕቃዎቹን ያዘጋጁቸዋል።

እየተጣደፈ መኝታ ቤቱ ገባና አልጋው ሥር ወለሉ ላይ ተቀመጠ። ልክ ደብዳቤውን ለመጻፍ ሲዘጋጅ ቀና ብሎ ግድግዳው ላይ የሰቀለውን መስቀል ተመለከተ።

በጣም እያሰላሰለ ትኩር ብሎ አየው። ምን ነበር ሽማግሌው ያሉት? «ፍጹም ፍቅር ምንም እስከማይቀር ድረስ መልካም ማድረግ።»

እርሱም እንደ አቅሙ እንደ ኢየሱስ ሊሆንና በፍጹም ፍቅር ሊወድ ፈለገ። እነዚያ የቆሸሹ ሳህኖች ወጥ ቤት ተቀምጠው የሚያጥባቸው ሰው ይጠብቃሉ።

ቀስ ብሎ ብድግ አለ። እናቱ ከግማሽ ሰዓት በኋላ ሲመጡ፥ ወጥ ቤቱ ጸድቶ፥ ሉሲየንም ልቡ በደስታ ተሞልቶ ደብዳቤ ሲጽፍ አገኙት።

በማግስቱ በጣም በማለዳ ነበር ወደ ሽማግሌው ቤት የሄደው። ባዶውን ቤት በመዝጋት አብረው ተመለሱ።

ሽማግሌው አኔትና ዳኒ በተጓዙበት ባቡር ተሳፍረው ጉዞ ሲጀምሩ ዐይኖቻቸው በኀዘን ተራራዎቹን ይመለከቱ ነበር።

«የፀደይ አበቦች መፍካት ሲጀምሩ እመለሳለሁ። ሸለቆው ውስጥ ሲፈኩ ጻፍና ንገረኝ። እንዲያ ካደረግህ አበቦቹ ተራራው ላይ ከመታየታቸው በፊት ለመመለስ በቂ ጊዜ ይኖረኛል። እንዳትረሳ ሉሲየን፥» አሉ ሽማግሌው የተሳፈሩበት ባቡር ሲንቀሳቀስ።

ይህ ከሆነ በኋላ ብዙም ሳይቆይ አንድ ቀን ሉሲየን ለአኔቴ ሴት አያት የመጣላቸውን ደብዳቤ ከፖስታ ቤት አውጥቶ ሊሰጣቸው ሮጠ። ደብዳቤው ከአኔት የተላከ መሆኑን ተረድቷል። የደብዳቤውን መምጣት መልካም ዜና እያበሰረ የፎቁን ደረጃዎች ሲወጣ፥ የአኔት ሴት አያት በታላቅ ጉጉት ብቅ አሉ።

«አንብብልኝ፥ ሉሲየን፥» ብለው ብደንብ ለማዳመጥ ይችሉ ዘንድ እጆቻቸውን አጣምረውና ዐይኖቻቸውን ከድነው የፀሐይ ብርሃን አለበት ስፍራ ተቀመጡ።

ደብዳቤው አጭር ስለነበር፥ ሉሲየን በአንድ ትንፋሽ አነበበው።

«ውድ አባቴ እና አያቴ፥ እኔና ዳኒ ከነገ ወዲያ እንመጣለን። ዳኒ በጣም ደህና ሆኗል። ልናያችሁ ጓግተናል። ልትቀበሉን ስትመጡ እባካችሁ ድመቴን፥ ክላውስን ይዛችሁ ኑ ብሏል ዳኒ። አፍቃሪ ልጃችሁ አኔት» ይላል ደብዳቤው።

ከዶክተሩ ሚስት የተጻፈ ደብዳቤም ነበር። የእነ አኔትን ትክክለኛ ጊዜ የሚገልጥና፥ «ወደ ቤቴ ስመለስ» በሚል ርእስ ዳኒ የሣለውን ሥዕል የያዘ ነው።

የአኔት ሴት አያት ለጥቂት ጊዜ አለቀሱ። ለቅሶአቸው ስቅታ ያለው አጭር የአሮጊት ለቅሶ ነበር። ይሁን እንጂ በሚንቀጠቀጡ እጆቻቸው እንባቸውን ጠራረጉና በጣም ጠንካራ መስለው ለመታየት ሞከሩ። ምክንያቱም ከእነ አኔት መምጣት ጋር ተያይዞ የሚከናወን ብዙ ሥራ አለ።



«ወደ ከብቶቹ በረት ሂድና ደብዳቤውን ለእነ ዳኒ አባት ስጠው፥ ሉሲየን። እና ቶሎ ተመልሰህ ሥራ እርዳኝ። ብዙ ሥራ አለብን። አልጋዎችን ወደ ውጭ አውጥተን እናናፍሳቸዋለን፥ ወንበሮች መጽዳት አለባቸው፤ ኬክ ይጋገራል። ሁሉንም ነገር በደንብ አሳምረን ነው ልጆቻችንን መቀበል ያለብን፥» አሉ ኮስተር ብለው።

የአኔት አባት ደብዳቤው ሲደርሳቸው በጣም ደንግጠው እራሳቸውን አከኩ። በሕይወታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ባልዲው ሳይሞላ ወተት ማለባቸውን አቆሙ። ጥቂት ቆይተው አካባቢያቸው ወደአለው ጫካ በመሄድ ሳይመለሱ ብዙ ቆዩ።

የሚቀጥለው ዕለት ማለዳ የጠራና ውብ ሆነ። ትምህርት የሌለበት ዕለት ነው። ሉሲየን በጠዋት ተነሥቶ አበባ ይቀነጥስ ጀመር። አበባውን በጥሩ ዕቃ አድርጎ በረዶው ላይ አለው ጠረጴዛ ላይ ካኖረው በኋላ ወደ ባቡር ጣቢያው ሄደ። አካሄዱ ዝግ ያለ ነበር። ምክንያቱም የእነ አኔት መድረሻ ገና ብዙ ጊዜ የሚቀረው ከመሆኑም በላይ የሚያስላስላቸው ጉዳዮችም ነበሩ። የእነ አኔት ሴት አያት፥ አባታቸውና ድመቲቱ ክላውስ በጋሪ ነው የተጓዙት።

ደስ የሚል የፀደይ ማለዳ ነው። ከአንድ ዓመት በፊት ዳኒ ከወደቀበት ዕለት እንደሚለይ ሉሲየን አስታወሰ። እንዴት ያለ አስከፊ ጨለማ ነበር ያ ዕለት? የዚያ ዕለት መጥፎ ትዝታ የደስታ አሳቡን በከለበት። እነዳኒ እርቀው እንዲሄዱ ምክንያት የሆነውና ጥፋተኛው እርሱ ነው። ሲያዩት ምናልባት ደስ አይላቸው ይሆናል። ዳኒ መዳኑን አኔት ብትገልጥም፥ ሉሲየን ማመኑ ቸግሮታል።

እየተጨነቀ ባቡር ጣቢያው ደረሰና እጆቹን ኪሱ ውስጥ በመክተት ከሌሎቹ ነጠል ብሎ ቆመ። እነአኔት ሲደርሱ በሰላምታ ሊቀበላቸው አልደፈረም፤ እንደውም ባልመጣሁ ብሎ ተመኘ።

የእነ ዳኒ አባት ባቡሩ ብቅ ሲል ወደሚታይበት ሸለቆ ይመለከታሉ። ሴት አያታቸው ተለቅቃ በባቡሩ ሃዲድ ላይ በመሄድ ብቻዋን እነ ዳኒን ለመቀበል የፈለገች ይመስል ከምትወራጨው ድመት ጋር ይታገላሉ።

«መጣ!» አሉ የእነ አኔት አባት ድምጻቸውን ከፍ አድርገው።

ሉሲየን ይህን ሲሰማ ከመቼውም ይልቅ ተሸማቀቀ።

ባቡሩ ተቃረበ፤ አኔትና ዳኒ መስኮቱ አጠገብ ተቀምጠዋል። ወርደው ከወላጆቻቸው ጋር ለመገናኘት መጓጓታቸው በቀላው ፊታቸው ያስታውቃል።

ዳኒ ሊቀበሉት የመጡ ዘመዶቹን ፊት አየት አደረገ። በዚያ አጭር ቅኝቱ ለብቻው የቆመውን ሉሲየንን አይቶ በድርጊቱ ተገረመ። አፍቃሪና ደስተኛይቱ ትንሽ ልቡ ሁሉንም ወደ ራሷ ለመሰብሰብ ፈለገች። ከባቡሩ ዘሎ እንደ ወረደ በቀጥታ የሮጠው ወደ ሉሲየን ነበር።

«እየው ሉሲየን፥ ለመራመድ ቻልኩ! ያገኘህልኝ ዶክተር አዳነኝ። ከገደል እንዳልወደቅሁ ሁሉ በደንብ ልሮጥ እችላለሁ። አያቴ አየሽ? ተመልከት አባዬ! ያለ ክራንቾች በመሮጥ ላይ ነኝ። አየሽ ክላውስ? ግልገልሽ ይሄውና። አላደገም አያቴ? ክላውስን ሊያክል እኮ ነው!» አለ እየተሯሯጠ።

ክላውስና ግልገሏ አልተፈላለጉም። በጥላቻ ተበጫጩሩ። ዳኒና አያቱ ሊገላግሏቸው ሲታገሉ፥ ሰው ሁሉ ሳቀባቸው። ባቡሩ ተሳፋሪዎቹን አውርዶ፥ ጉዞውን ለመቀጠል ተንቀሳቀሰ። አኔት ዳግመኛ ልትለቅቃቸው ያልፈለገች ይመስል አባቷን ጥብቅ አድርጋ ያዘቻቸው።

ሉሲየን ብቻ ነው ዐይኖቹ እንባ ስለአቀረሩበት ራቅ ብሎ የቆመው። ከማንም ይልቅ የከበረ ተግባር የፈጸመው እርሱ ነው። የሠራው በደል ለዘለዓለም ይቅር ተብሏል፥ ተረስቷል። ዳኒ ፍጹም ወድቆ የነበረ በማይመስል ሁኔታ ለመራመድ ችሏል።

ፀደይ መጥቷል – ክረምቱ አለፈ፥ ሄደ። እንደገና አበቦች ፈክተዋል፤ ወፎችም ይዘምራሉ። ደስታ ወደ ሁሉ ልብ ተመልሷል።